# ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የቀረበ አማራጭ መርኃ-እቅድ (ፖሊሲ) ሰነድ

I. መግቢያ ፡

II. ክፍል አንድ ፡-

1 አጣዳፊ የትኩረትና የፖሊሲ ለውጥ እርምጃዎች፤

1.1 የረሃብንና የድህነትን አዙሪት መስበር
1.2 የብሔራዊ ኢኮኖሚ ልማት መሠረት መዘርጋት
1.3 የአካባቢን የውድመት ሂደት መቀልበስ
1.4 ከአገር ውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን በአገር ግንባታው ጥረት ማሳተፍ
1.5 ማኅበራዊ ቀውሶችን መቋቋም

III. ክፍል ሁለት ፡-

2 ወደ ዴሞክራሲያዊና የተረጋጋ ኅብረተሰብ የሽግግር ሂደት ፤

2.1 የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ተግባራት
- ወደ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት ሂደታችን
- ዴሞክራሲን ለማስፈን ሕዝባዊ ተሳትፎን ማጎልበት
2.2 በብሔራዊ እርቅ ወደ ተረጋጋ ኅብረተሰብ

IV. ክፍል ሦስት፡-

3. ማጠቃለያ፤

አማራጭ ስንል ልዩነቱ ፤

# ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)

## ለኢትዮጵያ አገር ወዳዶችና ዴሞክራቶች የቀረበ የጋራ ትግል አማራጭ ሰነድ፤

## I. መግቢያ:

**እኛ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ኃይሎች፤**

. አገራችን ኢትዮጵያ በታሪኳ ዓይታም ሰምታም በማታውቀው ሁኔታ ኅልውናዋንና የሕዝባችንን ሰላምና ደኅንነት የሚፈታተኑ የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚ፥ የማኅበራዊ፥ የአካባቢ ውድመትና ሌሎች ከባድ ቀውሶች ውስጥ መሆኗን በመገንዘብ፤

. እነዚህ ቀውሶች ለዘመናት እየተጠራቀሙ የመጡ መሆናቸው ባይካድም በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት አንዳንዴም በቸልተኛነት ሌላ ጊዜ ደግሞ ሆን ብሎ በሚከተላቸው የተሳሳቱ ፖሊሲዎች የተነሣ አስደንጋጭ በሆነና ከዕለት ዕለት መመለሻ በሌለው ሁኔታ እየከፉና እየተባባሱ በመሄድ ላይ መሆናቸውን በማጤን፤

. አስቸኳይ የፖሊሲና የአቅጣጫ ለውጦች ካልተደረጉ ተጨማሪ ቀውሶች እየተፈለፈሉ አገራችን ከፍተኛ ፈተና ላይ ልትወድቅ የምትችልበት አደገኛ ሁኔታ መኖሩን በከፍተኛ ጭንቀት በመገንዘብ፤

. ዛሬ አገራችንና ሕዝባችን የተያያዙትን የአዘቅት ጉዞ ባስቸኳይ ገትቶ ማቆምና የገቡበትን የጥፋት አዙሪት መስበር የዚህ ወይም የዚያ ግለሰብ፥ ድርጅት ወይም ስብስብ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያዊ የጋራ የሆነ፥ ብሔራዊ፥ ሰብዓዊና የሞራል ግዴታና የትውልድ ተልዕኮ መሆኑን በመረዳት፤

. እነዚህን ቀውሶች ለመቋቋምና አጥፊውን ሂደት ለመቀልበስ የሚቻለው በሉዓላዊት አገሩ ሉዓላዊ የሆነ ሕዝብ መክሮና ዘክሮ መፍትሔ ለመሻት የሚችልበት ዴሞክራሲያዊ መድረክ ሲመቻችለት ብቻ በመሆኑ፥ ዛሬ የኢትዮጵያ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ተቀዳሚ ተግባር በጋራ ሰላማዊና ሕዝባዊ ትግል ይኸንን መድረክ የነፈገውን መንግሥትና መንግሥታዊ ሥርዓት አስወግዶ በሱ ቦታ በዴሞክራሲዊ ሥርዓት ክልል ውስጥ ጥረቱን የሚያግዝና የሚያስተባብር በሕዝብ ፊት ተጠያቂ የሆነ መንግሥት መመሥረት መሆኑን በመገንዘብ፤

. እዚህ ደረጃ ለመድረስ ለሕዝቡ ትግል ቅንብርና አቅጣጫ የሚሰጥ ግልጽ የሆነ አማራጭ ሰነድና የተደራጀ ኃይል አስፈላጊ መሆኑን በማመንና፥ ይኸ እስከሌለ ድረስ ሕዝባችን በግብታዊነት ተራ በተራ እየተነሣ ተራ በተራ እየተመታ የሚሄድበት ወይም ደግሞ ባልሆነ አቅጣጫና ባልሆነ ዘዴ እንዲታገል ለሚገፋፉት የተለያዩ ኃይሎች ሰለባ የሚሆንበት ሁኔታ እንዳለ በሥጋት በማጤን፤

. የአገራችንን ኅልውናና የሕዝባችንን ሰላምና ደኅንነት በተመለከተ ከፖለቲካ፥ ከብሔር/ብሔረሰብ/ጎሣ፥ ከርዕዮተ-ዓለም ልዩነቶች ባሻገር፥ ሁላችንም የምንቀበለውና በጋራ ልንዋደቅለት የሚገባን የጋራ አገራዊ ራዕይ እንዳለን በመገንዘባችንና ይኸንንም ለሕዝባችን በማካፈል ሁሉም ለዚህ ዓላማ በጋራ እንዲታገል ማነሣሣት የትውልድ አደራ ነው ብለን በማመን፤

. አገር-ወዳድና ዴሞክራት ነን የሚሉ ኃይሎች በሙሉ ለዚህ ዓላማ በቁርጠኝነት ከቆሙ፥ አገራችንና ሕዝባችን የገቡበትን አስከፊ አዙሪት ለመስበር የሚያስችሉ በርካታና ወሳኝ አገር -አድን አማራጮች እንዳሉና በነዚህ ላይ ተስማምተው በጋራ ለመታገል የማይነሱበት ምንም ምክንያት አይኖርም ከሚል ፅኑ እምነት በመነሣት፤

. በነሐሴ ወር 1996 ዓ.ም. በሮክቪል ሜሪላንድ ዩ.ኤስ.ኤ. በተካሄደው የኢዴኃጎ ብሔራዊ ሸንጎ አስቸኳይ ጉባዔ ላይ የፀደቀውን የጋራ ራዕያችንን ካካተተው መለስተኛ ፕሮግራም በተጨማሪ የመንግሥት ሥልጣን በመያዝም ሆነ ከዚያ በመለስ ባለው የትግል ወቅት ሕዝባችን የሚገኝበትን አጥፊ አዙሪት ለመስበር እነዚህን አማራጭ የፖሊሲ፥ የአቅጣጫና የጋራ ትግል መስኮች ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘተ፤

. የኅብረቱ ደጋፊዎችም ሆኑ በኅብረቱ ያልተካተቱ ሌሎች የአገራችን ዴሞክራቶች በሙሉ የጉዳዩ ዋና ባለቤት የሆነውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር ከጎናቸው በማሰለፍ ከኢሕአዴግ መንግሥት ጋር በሰላማዊ መንገድ ተፋልመው ኢትዮጵያ ካለችበት የቀውስ አዙሪት ወጥታ የዴሞክራሲና የልማት ጎዳናን እንድትይዝ ያስችላል በሚል ጽኑ እምነት ይኸንን አማራጭ የጋራ ትግል ሰነድ እናቀርባለን።

## II. <u>ክፍል አንድ ፥</u>

## 1. <u>አጣዳፊ የትኩረትና የፖሊሲ ለውጥ እርምጃዎች፤</u>

እነዚህን ትኩረትና አስቸኳይ መፍትሔ ይሰጣቸው የምንላቸውን ከባድና አደገኛ ቀውሶች ማለትም መናጢ ድህነትን፥ ረሃብን፥ ሥራ-አጥነትን፥ በሽታን፥ የአካባቢ ውድመትንና ሌሎች መቅሰፍቶችን እኛም ሆንን የቀውሱ ገፈት ቀማሽ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቀን እናውቃቸዋለን።

ሕዝባችንን ይዘን እንቋቋማቸው፥ እንጋፈጣቸው ስንል ከሁሉ በፊት እነዚህ ቀውሶች በሙሉ እዛው በዛው አንዱ የሌላው ምክንያትም መዘዝም እየሆኑ ተያይዘው የሚባባሱና የሕዝባችንንና የአገራችንን ከቀን ቀን እየከፋ በሚሄድ የጥፋት አዙሪት ውስጥ በመክተት ላይ ያሉ መሆናቸውን በደንብ መገንዘብ ያስፈልጋል።

አገራችን ባለችበት ዙሪያ ገጠም የቀውስ ጥምጥም ውስጥ እስካለን ድረስ ዛሬ ለአንዱ ችግር መፍትሔ አቅርበን፥ ነገ ሌላውን ቀውስ እንዳመጣጡ ተጋፍጠን፥ ከነገወዲያ ደግሞ በተራው

ያኛውን ችግር እንፈታለን ማለት ከአንድ ገደል ጫፍ ወደ ሌላ ገደል ጫፍ እያረፉ ለመዝለል እንደሞሞከር ያህል አደገኛ ህልም ነው። ጥረታችን ይኸንን የጥፋት አዙሪት ለመስበርና ለአንዱ ቀውስ የሚቀርበው መፍትሔ ሌላውንም ችግር ለመፍታት ሁኔታዎችን የሚያመቻችበት በጎ የእድገት እመርታ ለመቀስቀስ መሆን ይኖርበታል። ባጭሩ ኢትዮጵያችን ካለችበት ከባድ ቀውስ የምትወጣው ብሔራዊ ራዕይ ባነገበ አጠቃላይና ሁለ-ገብ ስትራቴጂ እነዚህን የተቆላለፉ ቀውሶች በሙሉ በአንድ ሂደት ግንባር ለግንባር ለመግጠም የሚያስችለን እንደ ችግራችን እሱም ሁለ-ገብና የተቀነባበረ ዕቅድ ስናቀርብና እኛም ሕዝባችንም ለዚህ እውንነት ስንታገል ብቻ ነው።

ሁለተኛውና መሠረታዊ እምነታችን አገራችን እነዚህን ከባድ ቀውሶች ተወጥታ የሰላም፥ የልማትና የብልጽግና ጎዳና ለመያዝ ይኸ ነው የማይባል የሰውና የተፈጥሮ ሀብት አላት የሚል እምነት ነው።

ከዓመት ዓመት በድርቅ ምክንያት ርሃብ የማይለያት አገራችን እዛው በዛው ባላት ይኸ ነው የማይባል የውሃ ሀብት የአፍሪቃ የውሃ ማማ ተብላ ትታወቃለች። ከዚች ከምድራችን በየዓመቱ 130 ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሃ በየአቅጣጫው ወደ ሌሎች አገሮች ይፈስሳል። የአገራችን ምሁራን ካካሄዷቸው በርካታና አሣማኝ ጥናቶች ስንነሣ ከዚህ ውሃ ሌላው ቀርቶ በየዓመቱ 2 ቢሊየን ብናስቀር ለአሥር ሚሊዮን ሕዝብ የሚበቃ እህል ማምረት እንችላለን። ከዚህ ውሃ 25 ቢሊዮን ብናስቀር ለ150 ሚሊዮን ሕዝብ የሚበቃ እህል ማምረት እንችላለን።

የመሬትና የማሣ ጥበት እያልን በምናማርርበት ምድር ለእርሻ ተስማሚ ተብሎ ከሚገመተው 114 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ዛሬ የሚታረሰው 16.5 ሚሊዮን ሄክታር ብቻ ነው። ለማገዶና ለሌላ ፍጆታ ደን እየተደመሰሰ ለከፍተኛ የአካባቢ ውድመት እየተጋለጠች በመሄድ ላይ ያለችው ኢትዮጵያ በአላት ገና ያልተነካ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጨት አቅም ከዛየር ቀጥሎ በአፍሪቃ ሁለተኛ ደረጃ የያዘች መሆኗንና በዚህ ከተጠቀመች ለአካባቢ የአፍሪቃ አገሮችና ለመካከለኛው ምሥራቅ የኤሌትሪክ መብራትና ኃይል ለማቅረብ እንደምትችል በርካታ ጥናቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው።

በቀንድ ከብት ሀብት ብዛት አገራችን ከመላው አፍሪቃ በአንደኛነት የምትጠራ ነች። ከዚህ ሁሉ በላይ በታታሪ፥ የሥራ ትጋትና ዲሲፕሊን ባለው ሕዝብ፥ ለዘመናት በዳበረና የተሰበጣጠረ አኩሪ ባሕል፥ በወጉ ባልተጠቀምንበት ይኸ ነው በማይባል የተማረ የሰው ኃይል፥ ለአገሩ በጎ በሚመኝና ያለ የሌለውን ከስክሶ ካለችበት ውድቀት ለማንሣት በጎ ሕልም ባለው አገር ወዳድና ዴሞክራት ኃይል የተትረፈረፈች አገር ናት። በአጭሩ ዛሬ የፖለቲካና የርዕዮተ-ዓለም ልዩነቶቻችንን ወደ ጎን ትተን ለጋራ ኢትዮጵያዊ ራዕይ በጋራ ተንቀሳቅሰን ከሕዝባችን ጋርና ጎን ተሰልፈን ያለንበትን አዙሪት ለመስበር እንነሣ ማለትን "የማይመስል" ጥሪ አድርገን አናየውም።

ሦስተኛ አገራችን ከዚህ ከባድ ቀውስ ውስጥ ለምን ገባች? ይኸን ሁሉ ፀጋ ታድላ ለምን የጥፋት ጎዳና ተያያዘች? የሚሉትን ጥያቄዎች ስናነሣ የዴሞክራሲ፥ የመንግሥት ተጠያቂነት፥ የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ የልማት አቅጣጫች መከተል፥ የተረጋጋ ኅብረተሰብና የሕዝብ ተሣትፎ ጉድለት የነዚህ ሁሉ ቀውስና የድህነታችን ዋና ዋና ምክንያቶች ሆነው እናገኛቸዋለን።

ዛሬ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና ከዓለም ባንክ አንስቶ ሌሎች ዓለም-አቀፍ ተቋማትም ድህነትን የሚገልጹበት መስፈርት ከቁሳቁሳዊ ማጣትና መራቆት አልፎ የመብትና የዴሞክራሲ ድህነትንም የሚያካትት እንደሆነ እናያለን። በኛም አገር የሕዝባችን ድህነት ቁሳዊ የማጣትና የመራቆት ጥያቄ ብቻ አይደለም። ከዚሁ ቁሳቁሳዊ መስፈርት በማይተናነስ ደረጃ የገዛ ዕድሉ ባለቤት የመሆን መብቱን መቀማቱ፥ ችግሮቹን መክሮና ዘክሮ ለመወጣት የሚያስችለውን ሥልጣን መገፈፉ የዚህ ድህነት የማይነጠሉ ገጽታዎች

ናቸው፡፡

ማንም ሕዝብ መቸምና የትም ቢሆን የመብት ድሃ ሆኖ እስከተያዘ ድረስ ከማጣትና ከመራቆት አይላቀቅም፡፡ ማንም ኅብረተሰብ ዕጣ ፋንታውን ለማቀድ፥ ለማለምና ለመቀየስ የሚያስፈልገውን ፋታና መረጋጋት ካላገኘ የልማት ጎዳናን በሙሉ ልብ ሊያያዝ አይችልም፡፡ ከዚህ ሃቅ ስንነሣ ይኸንን የመብት መራቆት ችግር ተወጥቶ የመፍትሄዎቹ አራማጅም ተጠቃሚም የሆነው ባለጉዳዩ ሕዝብ ራሱ ያገባኛል ብሎ ባልተንቀሳቀሰበት ኅብረተሰብ፥ የአገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ የፖለቲካ ኃይሎች፥ የሲቪኩ ማኅበረሰብ፥ የነፃ ጋዜጦች፥ የግሉ ኢኮኖሚ ዘርፍ፥ ምሁራን፥ የሙያ ማኅበራት፥ ሴቶች፥ ወጣቶችና ሌሎች ስብስቦች በሙሉ እጅ ለእጅ ተያይዘው ከዳር እስከዳር ባልተነሱበት ሁኔታ፥ ከነዚህ ሁሉ ኃይሎች እየመከረና እየዘከረ ይኸን ሁሉ ጥረት የሚያስተባብርና የሚያስተጋግዝ በሕዝብ ፊት ተጠያቂነት ያለው መንግሥት በሌለበት አገር ልማትና ብልጽግና የሚታለም አይደለም፡፡

ባለፉት 14 ዓመታት የኢሕአዴግ መንግሥት አንዴ የመዋቅር ማስተካከል፥ ሌላ ጊዜ ፕራይቬታይዜሽን፥ ቀጥሎ ደግሞ ድህነት ቅነሳ፥ ከዚያ ደግሞ እርሻ ልማት መር ኢንዳስትሪያላይዜሽን፥ ወዘተ... እያለ ኅብረተሰባችንን ያንከራተተበት የኪሳራ ጉዞ የሚያረጋግጥልን ዋና ነገር ዴሞክራሲ፥ የሕዝብ ተሳትፎና የተረጋጋ ኅብረተሰብ የሚሉትን ፀጋዎች ያልተላበሰ ሂደት የትም እንደማያደርስ ነው፡፡

ዛሬ በአገራችን ፊት የተደቀነው ዋና ፈተና ከነዚህ ሃቆች ተነስቶ በተቀነባበረና ቁርጠኝነት በተመላው ጥረት ይኸንን አጥፊ አዙሪት የሆነ ቦታ ላይ ሰብሮ ለዚህ ሕዝብና ለዚች አገር ያለንን በጎ ራዕይ እውን ለማድረግ የሚያስችለንን አዲስና በጎ የእድገት አዙሪት መቀስቀስ ነው፡፡ ይኸን ኃላፊነት ለመወጣት መጀመሪያ ካለንበት ከባድ ቀውስ ለመውጣት ያስችላሉ የምንላቸውን አማራጭ ፖሊሲዎችና ርምጃዎች ጠቁመን፥ ከዚህ በተጨማሪ እነዚህን ፖሊሲዎች እውን ለማድረግም ሆነ ወደምንመኘው ኅብረተሰብ ለመጓዝ እንደ ሕይወት እስትንፋስ የሚያስፈልጉንን ዴሞክራሲና የብሔራዊ እርቅ ለማስፈን መወሰድ ስላለባቸው ርምጃዎች ያለንን አሳብ እናቀርባለን፡፡

## 1.1 <u>የርሃብና የድህነት አዙሪትን መስበር፤</u>

የርሃብና የድህነት አዙሪት በሰፈነባት በገጠራቱ ኢትዮጵያ ያለውን ሥዕል ስንመለከት ሁለት የተያያዙ ችግሮች እናያለን፡፡ በአንድ በኩል እየጨመረ በሚሄደው የሕዝብ ቁጥር የተነሣ ከዓመት ዓመት እያነሰችና እየመከነች በምትሄድ ማሳ ላይ በነባርና ባረጁ ባፈጁ እንዲሁም በጥናትና ምርምር ባልተደገፉ የአስተራረስ ዘዴዎች እየተጠቀሙ ከእጅ ወደ አፍ የማያልፍ ምርት እያመረቱ የሚኖሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የገበሬ ቤተሰቦች አሉ፡፡ ለዚያውም ደግሞ የእርሻ ሥራቸው በአብዛኛው የሚተማመነው በዝናብ ላይ በመሆኑ፥ ድርቅ ለአንዲት ዓመትም ሆነ ለተከታታይ ዓመታት ከተከሰተ ይችውም ከእጅ ወደ አፍ ኑሮ ተናግታ ለረሃብ የሚዳረጉበት ሁኔታ ውስጥ ነን፡፡

በሌላ በኩል በገጠራቱ ኢትዮጵያ ያለው ከባድ ቀውስ ገፅታ ከዓመት ዓመት ከቁጥጥር ውጭ በሆነ ሁኔታ እየጨመረ የሚሄደው በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ለመቦዘን የተገደደ (በዚህም የተነሣ ለመናጢ ድህነትና ለተመጽዋችነት የተጋለጠ) የሰው ኃይል ክምችት መኖሩ ነው፡፡ አሁን በተያያዝነው አደገኛ ሂደት ከቀጠልን በመጭዎቹ ዓመታት የዚህ ለመቦዘን የተገደደ የሰው ኃይል ቁጥር በግብርናው ክፍለ-ቀጠና ሊሰማራ ከሚችለውም ሆነ ከተሰማራው ገበሬ የሚበልጥበት ሁኔታ እንዳለ ግልጽ ነው፡፡ በዚህ መልክ የተመጽዋቹ ቁጥር ከእጅ ወደ አፍ አምራቹ በልጦ ሲገኝ ይኸ ሁኔታ ሊያስከትለው የሚችለውን የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ አለመረጋጋት መዘዝ ምን ሊሆን እንደሚችል መረዳት አዳጋች አይመስለንም፡፡ ከፍ ብለን አገራችን የገባችበትን የቀውስ አዙሪት ለመስበር ዋና ዋና የሆኑትንና እየተጋገዙ

የሚባባሱትን ቀውሶች ተራ በተራ እንወጣዋለን ማለት አደገኛ የዋህነት ነው ስንል ለነዚህ ችግሮቻችን የምናቀርባቸው መፍትሄዎች እየተጋገዙ በጎ አዙሪት የሚፈጥሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እንሥራ ለማለት ነው። ይኸ ማለት የርሃብና ድህነትን አዙሪት ለመስበር ከተነሣን ማንኛውንም ስትራቴጂ ይኸንን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የተከሰተ ቀውስ ጥንድ ገፅታ በማጤን <u>ሁለቱንም ችግሮች በአንድ ሂደት ለመፍታት መሥራት ማለት ነው።</u>

"ገጠር-ተኮርና ግብርና ልማት መር ኢንዱስትሪያላይዜሽን (አድሊ)" የተባለው የኢሕአዴግ መንግሥት ፖሊሲ በተለያዩ የፖለቲካ፥ የርዕዮተ-ዓለምና ዓለም-አቀፋዊ ምክንያቶች “የመሬትን ብሎም የገበሬውን ምርታማነት አሳድጋለሁ” ብሎ ሲግደረደር ይኸንን ያለንበትን አዙሪት አንድ ሌላ ገጽታ በቸልታ የሚያልፍ፥ እስካሁን የትም ያላደረሰ ወደፊትም የትም የማያደርስ <u>ግንጥል ስትራቴጂ</u> ነው።
በመሆኑም ይኸ ፖሊሲ ለአገራችን ልማትን ለማምጣትና የሥራ-አጥነት /ድህነት ሰንሰለትን ለመስበር ቁልፍ የሆነውን የቦዘነ የሰው ኃይል ክምችት ዕጣ ፈንታ ከቁጥር አይጥፍም።
ይኸ የእርሻ ልማት መር ኢንዱስትሪያላይዜሽን የተባለው ፖሊሲ በዚህ መናጢ ድህነት ባጠቃው ኅብረተሰባችን የምርታማነት ማደግ ከግብርና ክፍለ-ቀጠና (ሴክተር) ውጭ በሚዳብር የመግዛት ኃይል ካልታገዘ፥ የእርሻ ምርትና ምርታማነት ማደግ ከዚህ ክፍለ-ቀጠና ውጭ በኅብረተሰቡ ውስጥ ከሚጎለብት የአምራች/ሸማች የዕድገት ሂደት ጋር ካልተቆራኘ፥ አገራችን ካለችበት የድህነት አዙሪት እንደማትወጣ የተገነዘበ ስትራቴጂ አይደለም።
ገበሬው ጥሮ ግሮ አምርቶ ምርቱን በተመጣጣኝ ዋጋ የሚገበየው (የሚገዛለት) ኃይል ከሌለ ውጤቱ ምንድን ነው? ደርግ ለዚህ ዓይነቱ ቀውስ አገኘሁ ይል የነበረው መፍትሔ “የልፋቴን ዋጋ ካላገኘሁ ምርቴን አላወጣም” ያለውን አራሽ *'የገበሬ ካፒታሊስት' 'የገበሬ ግለሰበኛ'* እያለ ፈርጆ መጨፍጨፍና ምርቱን በግድ ለመቀማት በእህል ቦርድና በኮታ፥ በኅብረት እርሻና በመንደር ምሥረታ ስም አገሪቱን ማተራመስ ነበር።

ዛሬ “የነፃ ገበያ” ተብየው ኢኮኖሚ ስላለ ገበሬው ከልፋቱ በሚመጥን ዋጋ ለመሸጥ ሸማች ቢያጣም እንኳን ለማዳበሪያና ለሌሎች ግብዓቶች የተበደረውን ዕዳ ከነአራጣውና ምንም ፋታ በማይሰጥ ሁኔታ መልሶ ለመክፈል ስለሚገደድ ምርቱን የግዱን ያወጣል። ከሁለት ዓመት በፊት ተከስቶ የነበረው የዋጋ ማሽቆልቆል የዚህ ቀውስ ነፀብራቅ ሲሆን፥ ድሃው ገበሬ "ወይኖ አረሰው ወይኖ ጎረሰው" እንደተባለው የማዳበሪያ ዕዳ ለመክፈል ምርቱን በአልባሌ ዋጋ ሸጦ ሲቸገርና ለቀጣዩ አዝመራ አቅሙም ቅስሙም ተሰብሮ ከባድ ችግር ውስጥ ሲወድቅ ታዝበናል።
<u>እንዲህ ዓይነቱን አንዱ በተፈጥሮ ሌላው በአስተዳደር ድርቅ ለርሃብና ለችጋር የሚዳረግበትን አዙሪት ለመስበር እኛ የምናቀርበው መፍትሄ በዚያው በአገራችን ውስጥ አምራችና ሸማች ተያይዘው የሚያድጉበትን ሂደት እንቀስቅስ የሚል ስትራቴጂ ነው።</u>

የኢሕአዴግ መሪዎች አካሄድ እዛው በዛው አስገራሚም አሳዛኝም ነው። በመስከረም ወር 1994 ዓ.ም. በ4ኛ ጠቅላላ ጉባዔአቸው የግብርና ልማት ስትራቴጂያችን “በተለይ በዓለም ገበያ የሚመራና በዚሁ የተቃኘ እንዲሆን ማድረግ” እንደሆነ በግልጽ ነግረውናል። በዚህ አስተሳሰብ መሠረት በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ለግድ መቦዘን፥ ለርሃብና ለተመጽዋችነት ውርደት ተጋልጦ የመሸመት አቅም ስለሌለው ከነፃ ተብየው ኢኮኖሚ አንፃር እንደ ደረቅ ጣቢያ ይቆጠራል ማለት ነው። በመሆኑም የኢሕአዴግ ፀረ-አገር፥ ፀረ-ሕዝብና ዞሮ ዞሮ ደግሞ በኢሰብዓዊነቱ የሚዘገንን ስትራቴጂ በዚሁ በአገራችን ውስጥ አምራችና ሸማች ኃይል ከመፍጠር ይልቅ እህል ጭኖ ዓለም ገበያ ሸማች ፍለጋ መዞር ማለት ነው።
በኛ እምነት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ለሚደረገው የርሃብንና የድህነትን አዙሪት የመስበር ጥረት ሁሉም ተያይዞ የሚያድግበት፥ መሪና ተመሪ የማይኖረው ሂደት ነው።
በአንድ በኩል የእርሻ ምርታማነትን ለማሳደግ እዛው ደግሞ በሚሊዮን የሚቆጠረውን የቦዘነ የሰው ኃይል ክምችት በግብርና ነክም ሆነ ከዚያ ውጭ ባሉ የምርት ሥራዎች አሠማርቶ የአምራች/ሸማች፥ የልማት ዕመርታና የዕድገት በጎ አዙሪት ለመቀስቀስ የሚያስችለን ጥንድ

ስትራቴጂ መሆን ስላለበት ይኸንን በተግባር ለመተርጎም የሚያስችሉ አማራጮች በመንግሥትና በግል ባለ ሀብቶች የተቀናጀ ጥረት መሰናዳት ይኖርባቸዋል እንላለን፡፡

እነዚህ የአራሹን ምርት ከማሳደግ ጥረት ጋር በተጓዳኝነት የምንሰማራባቸው የአማራጭ ሥራ ዘርፎችም፡-

አንደኛ በቀጥታ የራሱን የእርሻውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት የሚያግዙ፥
ሁለተኛ የግብርና ምርቶችን መሠረት በሚያደርጉ የትናንሽና የጎጆ ኢንዱስትሪዎች፥
ሦስተኛ እንደየአካባቢው የጥሬ ዕቃም ሆነ ሌላ ተፈጥሮአዊና የሰው ሀብትና ችሎታ ለአምራቹ ገበሬም ሆነ ለጠቅላላው ኅብረተሰብ መሠረታዊ ፍላጎትና ፍጆታ የሚመጥኑ የፋብሪካ፥ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት የሥራ መስኮችን በተቀነባበረ ጥረት መስፋፋት መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

በዚህ ስንሄድ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች (ኢዴኃን) ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸውና በሥራ ላይ ከዋሉ ያለንበትን አጥፊ አዙሪት ሰብረው የአገራችንን አዲስ የዕድገት ዕመርታ ጎዳና ያስይዟታል ብሎ የሚያምንባቸው ፖሊሲዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 1.1.1 <u>እርሻ ምርትንና ምርታማነትን ማሳደግ፤</u>

#### 1.1.1.1 <u>የትናንሽ የቤተሰብ አራሾች ምርትና ምርታማነት፤</u>

1.1.1.1 የአገራችን ገበሬዎች በተረጋጋ ሁኔታ ጉልበታቸውንና ገንዘባቸውን አፍስሰው በማሣቸው ምርታማነትና እንክብካቤ ላይ በሙሉ ልብ እንዲያተኩሩ ከመሸጥና ከመለወጥ በመለስ የመሬት ባለቤትነት መብታቸው ሙሉ በሙሉ እንዲረጋገጥ፥ ገበሬው ከያዘው ማሣ በምንም ምክንያት እንዳይነቀልና ለልጆቹ የማውረስ መብቱ ሙሉ በሙሉ ታውቆለት ወቅታዊ የመሬት ክፍፍል ጨርሶ እንዲቋረጥ ማድረግና አሁን በአንዳንድ አካባቢዎች የተጀመረው የይዞታ ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ዕደላ ፖሊሲ በዚህ መንፈስ ተቃኝቶ በአንድ በኩል በአገሪቱ በሙሉ እንዲሠራበት፥ በሌላ በኩል ደግሞ ይኸ ፖሊሲ ያለው መንግሥት የፖለቲካ አጀንዳ ማራመጃ መሣሪያ እንዳይሆን በራሱ በየአካባቢው ባለጉዳይ በሆነው ገበሬ ተመራጮች ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካኝነት እንዲከናወን ጥረት ማድረግ፡፡ ከዚህ አልፎ መሬትን መሸጥና መለወጥን ያካተተ መብት የመረጋገጡ ጉዳይ በተረጋጋና በዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ራሱ ዋና ባለጉዳይ የሆነው ገበሬ በሚሳተፍበት ሰፊ ብሔራዊ ውይይት ወደፊት እንዲወሰን ማድረግ፤

1.1.1.1.2 አሁን ባለውና እየተባባሰ በሚሄደው የመሬት መጣበብና የማሣዎች እያነሱና እየመከኑ መሄድ የተነሣ ምርት ሊያድግ የሚችለው ማዳበሪያ፥ ምርጥ ዘር፥ ፀረ-ተባይና ፀረ-አረም ግብዓቶችን በጥንቃቄና በሰፊው በመጠቀም ስለሆነ፥ እነዚህ ግብዓቶች ለየመሬቱ ባሕሪና አቀማመጥ ይስማሙ አይስማሙ እንደሆነ ጥናት እየተደረገ ተስማሚነታቸው ከተረጋገጠ በኋላ አጠቃቀምን በሚመለከት ለገበሬው በቅድሚያ አስፈላጊው ትምሕርት እየተሰጠ ግብዓቶችን የመጠቀም ፖሊሲ መቀየስ፤

1.1.1.1.3 ስግብግብ የገዥው ፓርቲ የንግድ ድርጅቶች በጭፍን በሚያካሂዱት የትርፍ ማካበት ርምጃ ማዳበሪያ ከመሬቱ ጠባይ መስማማቱ አለመስማማቱ ሳይረጋገጥ፥ አንዳንዴም አስፈላጊነታቸው የሚያጠራጥር ግብዓቶችን እየሸጡ ገበሬው ገንዘቡንም፥ ምርቱንም፥ መሬቱንም እያጣ በመሄድ ላይ ስለሆነ ይኸ አሠራር ባስቸኳይ እንዲቆም፤ ምንም ዓይነት ማዳበሪያ ወይም ፀረ-ተባይ ኬሚካል ለተባለው አካባቢ መስማማቱ አለመስማማቱ ሳይረጋገጥ በዘፈቀደ የማሰራጨተብቸኛ ፍጹም ቁጥጥር (ሞኖፖሊ) ተላቆ ሌሎችም

እንዲገቡበት ማድረግ፤

1.1.1.1.4 በዱቤና በአራጣ ወለድ የሚገዛቸው ግብዓቶች በድርቅም ሆነ በሌላ ምክንያት አዝመራም በማይዝበት ወቅት ገበሬውን የማይወጣው ዕዳ ውስጥ ይጨምሩታል። አንዳንዴ ደግሞ ምርት ሲይዝ በሚከሰተው የዋጋ ማሽቆልቆል የተነሣ ያፈሰሰውን ጉልበትና የገባውን ዕዳ እንኳን ለማስመለስ በማይችልበት አልባሌ ዋጋ ሽጦ ዕዳውን ለመክፈል ሲገደድ ታይቷል። አመረተም አላመረተ ዕዳ መክፈል ካልቻለ ከነጋዴዎቹ ትስስር ያለው የወያኔ/ኢሕአዴግ ፖሊስ እስር ቤት ሲከተው፥ ከዚህ ለማምለጥ በሬውን አንዳንዴ ጣራውን እየነቀለ ለመሸጥ ሲገደድና ለቀጣዩ አዝመራ አቅሙም ቅስሙም እየተሰበረ አንዳንዴም ሁሉን እርግፍ አርጎ ትቶ ወደ ከተሞች ሲሰደድ ተስተውሏል። ይኽንን ሁኔታ ለመቋቋም እንዲቻል፦

1.1.1.1.4.1 በድርቅ ወይም በሌላ ከገበሬው ቁጥጥር ውጭ በሆነ ምክንያት አዝመራ ሳይዝ ሲቀርና ገበሬው ብድሩን መክፈል የማይችልበት ሁኔታ ሲከሰት በአንድ በኩል የገባውን ዕዳ ፋታ ተሰጥቶት ቀስ በቀስ (በኢንስቶልመንት መልክ) የሚከፍልበት ሁኔታ እንዲመቻችና በብድሩ ላይ የሚጨመረው አራጣዊ ወለድ ጨርሶ እንዲሰረዝ ማድረግ፤

1.1.1.1.4.2 በገበሬው ላይ የተጫነው በሬውን ሸጦ ዕዳ የመክፈል ግዴታ እንዲቀርና ማንም አራሽ በማዳበሪያ ወይም በሌላ ዕዳ መነሾ ለእስር መዳረግ ፈጽሞ እንዲወገድ፤

1.1.1.1.4.3 ገበሬው የሚያስፈልገውን ማዳበሪያም ሆነ ሌሎች ግብዓቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ለመግዛት የሚችልበትና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እነዚህ ግብዓቶች በመንግሥት በተደጎመ ዋጋ ለአራሹ እንዲደርሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

1.1.1.1.4.4 ዛሬ ባለው ሁኔታ ገበሬው ግብርም ሆነ ዕዳ እንዲከፍል የሚጠየቀው በምርት ወቅት በጥድፊያና በወከባ በመሆኑ አሠራሩ ምርቱን በገፍና በተሰበረ ዋጋ በአንድ ጊዜ ገበያ ላይ ማፍሰስ ስለሚያስገድደው ከፍተኛ ምሬት እየፈጠረ ያለ ክስተት ነው። ይኽንን ሁኔታ ለመቋቋም የምርት ግብይት ወቅትና ሁኔታ፥ ከግብርናና ከዕዳ መክፈያ ወቅት ጋር ተምታትቶ ገበሬውን ችግር ላይ የሚጥለው ስለሆነ ሁኔታው ለገበሬው ፋታ በሚሰጠውና በሚጠቅም መልክ እንዲስተካከል ማድረግ፤

1.1.1.1.5 የተለያዩ የግብርና ግብዓቶች በኬሚካል ይዘታቸውና በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች ለምርቱ ማደግ ምንም አዎንታዊ አስተዋጽዖ ሳያደርጉ፥ ይብሱን መሬቱንም መርዘውና አምክነው በገበሬውና በቤተሰቡ ጤና የተለያዩ አሉታዊ ተጽዕኖዎች የሚያደርሱበት ሁኔታ በየአካባቢው ስለተስተዋለ፥ እነዚህና በተለይ ደግሞ በራሳቸው በአምራቾቹ አገሮች የተከለከሉ ግብዓቶች በድንበር ዘለል ኩባንያዎችና በአገር በቀል ስግብግብ ነጋዴዎች ትብብር ወደ አገር እንዳይገቡ ፈጽሞ መከልከልና ከዚህ ውጭ ሲሠሩ በተገኙ አስመጭዎችም ሆነ አከፋፋዮች ላይ ጥብቅ የቁጥጥርና የቅጣት እርምጃ የሚወሰድበትን ሕጋዊ መድረክ ማመቻቸት፤

1.1.1.1.6 የማዳበሪያም ሆነ የሌሎች ግብዓቶችን ችግር ለማቃለል ለየአካባቢው የሚስማሙ ተፈጥሮአዊ ግብዓቶች በአገሪቱ ውስጥ እየተመረቱ ለአራሹ ገበሬ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲሰራጩ የምርምር ሥራዎችን ማገዝ፤

1.1.1.1.7 በአሁኑ ወቅት የገበሬውን ምርታማነት ለማሳደግ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አቅርቦትና ዘመናዊ የእርሻ ዘዴዎች በገበሬው መካከል እንዲሰርፁ ማስቻል ወሳኝ ሆኖ ሳለ፥ በገጠሩ የሚሰማሩት የልማት ሠራተኞችና የኤክስቴንሽን ወኪሎች የሚያገኙት ሥልጠና ቁንጽል፥ በሚገባ ያልተቀናጀ፥ ከአገሪቱ ሁኔታ ጋር ያልተያያዘና ተከታታይነት የሌለው በመሆኑ ለዚህ ጉዳይ የቅድሚያ ቅድሚያ ተሰጥቶት በየአካባቢው የሥራ ጫናን

የሚያቃልሉና ምርታማነትን የሚያጎለብቱ የአዳዲስ ቴክኖሎጂ አቅርቦትና ሥርፀት ዕውን እንዲሆኑ በየደረጃው የማሰልጠኛ ተቋማት መክፈት፥ የምርምር ጥረቶችን የማበረታታት ፖሊሲ በሥራ ላይ ማዋል፤

1.1.1.1.8 በኢሕአዴግ መንግሥት እየተመለመሉ በገበሬው መካከል ከፍ ብለው የተጠቀሱትን ተግባራት ያከናውናሉ የሚባሉት ሠራተኞች ከመደበኛ ተልዕኳቸው ይልቅ በግብር ሰብሳቢነትና ከዚያም አልፈው በፖለቲካ ካድሬነት ለገዥው ፓርቲ ድጋፍ የመሰብሰብ ተልዕኮ ስለሚያራምዱና በዚህም የተነሣ በገበሬው ዘንድ ተኣማኒነት የሌላቸው ስለሆኑ፥ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ለሚለው ዓላማ የሚያደርጉት አስተዋጽዖ የለም፡፡ ይኸ ከባድ ኃላፊነት ከፖለቲካ ካድሬነት መንፈስና ዓላማ ውጭ መከናወን ያለበት ተግባር በመሆኑ በገበሬው መሃል ለዚህ ተግባር የሚሠማሩት ዜጎች በመንግሥት የተመለመሉ ሳይሆኑ በራሱ በገበሬው እየተመረጡ እንዲሰለጥኑና ተመልሰውም በሱው መካከል እንዲሠሩ የሚያስችል ፖሊሲ ቀይሶ በተግባር ማዋል፤

1.1.1.1.9 ግለሰብ አርሶ አደሮች የእርሻ መሬት ይዞታቸውን፥ መሣሪዎቻቸውንና ግብዓቶችን በማቀናጀት በፈቃደኝነት እንደ ደቦ በመሳሰሉ ትናንሽ ቡድኖች እየተደራጁና አስተባባሪዎችን በመምረጥ እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚችሉበት ሕጋዊ እውቅና በመስጠትና የሙያ (የቴክኒክ)፥ የቁሳቁስ፥ የብድር ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

1.1.1.2 <u>ዘመናዊ ሰፋፊ እርሻዎችን ማስፋፋት፤</u>

1.1.1.2.1 በአገራችን ለተለያዩ የእርሻ ሥራዎች ሊውል ከሚችለው 114 ሚሊዮን ሄክታር በሥራ ላይ የሚውለው 16 ሚሊዮን ሄክታር እንደመሆኑ መጠን ዜጎች ገንዘባቸውን፥ እውቀታቸውንና ጉልበታቸውን አቀናጅተው በዚህ ያልተነካ የአቅም ይዞታ እየተጠቀሙ ምርት እንዲያድግና የሥራ መስክ እንዲፈጠር ዘመናዊ ሰፋፊ የግል እርሻዎችን በሰፊው እንዲቋቋሙ ማድረግ፤

1.1.1.2.2 በዚህ ሰፊ መስክ ለመሠማራት የሚሹ ዜጎችን ለማበረታታትና እገዛ ለማድረግ አግባብ ካላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፥ ከተለያዩ የግል ይዞታው ቀጠና ተጠሪዎች፥ ከእርሻ ምርምር ተቋማት የተውጣጣ አንድ <u>የሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎች ማእከል (ተቋም)</u> እንዲቋቋም ማድረግ፤

1.1.1.2.3 ማእከሉ ለነዚህ ዜጎች የሙያ (ቴክኒክ) ምክር የመለገስ፥ የኢንቬስትሜንት መስኮች የመጠቆም፥ የቢሮክራሲ ውጣ ውረዶችን የማስወገድ፥ የብድር ሁኔታዎችን የማመቻቸትና ለዚህ ክፍል መጎልበት አስፈላጊ ስለሆኑት የፖሊሲ እገዛዎችና የአውታሮች (ኢንፍራስትራክቸር) ግንባታዎች ለመንግሥት ሀሳብ የማቅረብ ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

1.1.1.3 <u>ከብት እርባታ ላይ የተሰማሩ ዜገችን ማገዝ፤</u>

1.1.1.3.1 በልዩ ልዩ የአገራችን ክፍሎች የሚገኙ በከብት እርባታ ላይ የሚተዳደሩ (አርብቶ-አደር) ዜጎች ባህላቸውንና አኗኗራቸውን ግንዛቤ ውስጥ ባስገባና ከነሱም ጋር በመምከር ዘመናዊ የከብት እርባታዎችን ማቋቋምና በተጓዳኝ በአካባቢያቸው እርሻና ልዩ ልዩ ከእርሻ ጋር የተያያዙ እንቅስቃሴዎች እንዲኖሩ አስፈላጊው ሁሉ መበረታታትና ልዩ ድጋፍ እንዲሰጣቸው ማድረግ፤

1.1.1.3.2 ለከብቶቻቸው የግጦሽ አገልግሎት የሚሆን መሬት የማኅበረሰቡ የወል ይዞታና ንብረት እንደሚሆን ማረጋገጥ፤

1.1.1.3.3 እነዚህ አርብቶ-አደር ዜጎች የትምሕርትና የጤና ማእከሎችና አገልግሎቶች እንዲኖሯቸውና እንዲያገኙ፥ በተለይም መሠረታዊ የጤናና የፅዳት አጠባበቅ ትምሕርት እንዲደርሳቸው ማድረግ፤

*(*** የመሬት ፖሊሲን በሚመለከት የሚኖሩትን አማራጮች በአባሪ አንድ ሰነድ ላይ ይመለከቷል።)*

## 1.1.2 የ<u>ሥራ-አጥነትንና የድህነት አዙሪትን መስበር፤</u>

### 1.1.2.1 <u>የውሀ ሀብትን በወጉ መጠቀምና የመስኖ ሥራን ማስፋፋት፤</u>

1.1.2.1.1 በአገራችን የእርሻ ሥራ አንዱና ዋናው ችግር በዝናብ ላይ የተማመነ መሆኑ ነው። ከዓመት ዓመት በድርቅ ምክንያት ርሃብ የማይለያት አገራችን እዛው በዛው ይኸ ነው የማይባል የውሃ ሀብት እንዳላት ከፍ ብለን ጠቁመናል። ያለንን የውሃ ሀብት ባግባቡ መጠቀም የገበሬውን ምርታማነት ለማሳደግም ሆነ ከግብርናው ክፍለ-ቀጠና ውጭ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የመስኖ ግንባታና ሌላ የውሃ ሀብት አጠቃቀም ፖሊሲ መንደፍ ለአገራችን ዕድገት ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ግልጽ ነው።
ኢሕአዴግ በዚህ በኩል የሚከተለው ፖሊሲ በዘፈቀደ የሚነደፍ፥ ልክ እንደ ደርግ ዘመን መንደር ምሥረታ በመዕከላዊነትና በሰበር ውሳኔነት፥ የአካባቢውን የተለያዩ ተጨባጭ ሁኔታዎች ሳያገናዝብ ከመሃል ለሁሉም በተመሳሳይነት የሚጫን፥ ኅብረተሰቡን ሳያሳትፍ፥ ባሕላዊና ዘመናዊ የአሠራር ዘዴዎችን ሳያጣጥምና የተለያዩ አግሮ-ኤኮሎጂ ጎኖችን ልዩ ባሕርያት ግምት ውስጥ ሳያስገባ የተነደፈ ፖሊሲ በመሆኑ የሕዝብን አመኔታ ያላገኘ፥ ከፍተኛ ጊዜ፥ ገንዘብና የሰው ጉልበት ከፈሰሰባቸው በኋላ ብዙ ውጥኖችና እቅዶች (ፕሮጀክቶች) በኪሳራ ተደምድመዋል። በመሆኑም እነዚህን ችግሮች አስወግዶ እዛው በዛው የሥራ-አጥነትን ችግር ለመቅረፍና የውሃ ሀብታችን ለአገር ጥቅም የሚውልበትንና ልማት የሚያግዝበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

1.1.2.1.2 ችግሮቹን ሁሉ አገናዝቦ በዚህ በኩል አገሪቱ መከተል ያለባትን አቅጣጫ ለማመልከት ባስቸኳይ አንድ <u>'ብሔራዊ የውሃ ሀብት አጠቃቀም ዕቅድ'</u> የሚነድፍ ከማዕከላዊ መንግሥት፥ ከአካባቢ ባለሥልጣናት፥ ከሲቪክ ማኅበራት፥ ከግሉ የኢኮኖሚ ዘርፍ ተወካዮችና አግባብ ካላቸው ምሁራንና ባለሙያዎች የተውጣጣ አንድ <u>አካል (ኮሚሽን) ማቋቋም፤</u>

1.1.2.1.3 ኮሚሽኑ በአገራችን የመስኖ እርሻ ስለሚስፋፋበት፥ ንጹሕ ውሃ ለሕዝብ ስለሚቀርብበት፥ የኃይል ማመንጫ የግድብ ሥራዎች ስለሚስፋፉበት በአንድ በኩል ከሌሎች አገሮች ምንም ድርድር የማያስፈልጋቸው የሥምሪት መስኮችን ለይቶ በዚህ በኩል ሥራዎች የሚስፋፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

1.1.2.1.4 እንደ ዓባይ ዓይነቶች ከአገር ውጭ በሚፈስሱ ወንዞች ጉዳይ ከተፋሰስ አገሮች ጋር የሁሉንም ተገቢ ጥቅም የሚያስከብር ውይይት ስለሚደረግበት ሁኔታ እስካሁን ካለው ተመክሮ በመነሣት ዕቅድ በማውጣት ይኸንን ለመንግሥት አቅርቦ ይሁንታ ሲያገኝ ተግባራዊነቱን መከታተል።

### 1.1.2.2 የመሠረተ ልማት አውታሮች ግንባታን በማስፋፋት ሥራን መፍጠር፤

1.1.2.2.1 የገበሬውን ምርትና የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል መጋቢ መንገዶች፥ ትናንሽ ግድቦችና የውሃ ኩሬዎች፥ የመስኖ ሥራዎች፥ ትምሕርት ቤቶች፥ የጤና ጣቢያዎች፥ መኖሪያ ቤቶችና የመሳሰሉ የመሠረተ ልማት አውታሮችን ለመገንባት መንግሥት ከግሉ የኢኮኖሚ ክፍል፥ ከገጠሬው ሕዝብ ተወካዮችና ከሲቪኩ ማኅበረሰብ ስብስቦች ጋር በመተባበር አንድ በተለይ በገጠር የተከማቸውን የቦዘነ የሰው ኃይል በሥራ ለማሰማራቱ ጥረት ትኩረት የሚሰጥ 'ብሔራዊ የኢንፍራስትራክቸር እቅድ (ፕላን)' ነድፎ በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፤

1.1.2.2.2 ይኸንኑ በገጠር የተከማቸ በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ለመቦዘን የተገደደው የሰው ኃይል ከግብርናው ውጭ ባሉ በሌሎች የእንቅስቃሴ ክፍሎችና ንዑስ ክፍሎች መሰማራቱ የግድ ስለሆነና በመንግሥትና በግል ባለሀብቶች አማራጭ የሥራ መስኮች መክፈት ስለሚያስፈልግ በያለበት በገበሬው ምርትና በሌሎች በየአካባቢው በሚገኙ ጥሬ ዕቃዎችና ግብዓቶች ላይ የተመሠረተ ለገበሬው፥ ለቤተሰቡና በጠቅላላው ለኅብረተሰቡ መሠረታዊ የዕለት ከዕለት ፍጆታ አስፈላጊ የሆነውን ምርት ለማቅረብ የሚሠሩ ትናንሽ፥ መካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች፥ የአገልግሎት እንቅስቃሴዎች እንዲስፋፉ አስፈላጊውን የፖሊሲ እገዛ ማድረግ፤

1.1.2.2.3 እነዚህን ተግባራት ለማከናወን የግብርና ልማትም (አግሮ ኢንዱስትሪ) ሆነ ሌላ የማምረትና የሥራ መስክ ፈጠራ እንቅስቃሴ እንዲዳብር፥ መንግሥት ለግል ጥሪት አፍሳሾች (ኢንቬስተሮች) የተመቻቸ ሁኔታ ከመፍጠር አልፎ በመሬት ጥበት ለመቦዘን የተገደዱ አርሶ አደሮች በተለይም ወጣቶች አሳብና ጉልበታቸውን አስተባብረው የሥራ መስክ ለመክፈት ዕቅድ እንዲነድፉ ማበረታታትና የዚህ ዕቅድ አሳማኝነት ጠቃሚነት ብቻ እንደዋስትና (ኮላቴራል) ተቆጥሮ በተመጣጣኝ ወለድ ብድር አግኝተው ሥራ የሚፈጥሩበትን መንገድ ማመቻቸት፤

## 1.2 የብሔራዊ ኤኮኖሚ ልማት መሠረት መዘርጋት፤

አገራችንን ካለችበት ቀውስ ለማውጣትና የብሔራዊ ኢኮኖሚ ልማትና የኢንዱስትሪያላይዜሽን ፈር እንድትይዝ ሁለት መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ::

በአንድ በኩል ዜጎች ሀብታቸውን፥ እውቀታቸውንና ጉልበታቸውን በሥራ ላይ እያዋሉ በአገር ግንባታ ተግባር በሙሉ ልብ እንዲሳተፉ ማበረታታት ያስፈልጋል:: ለዚህ ደግሞ በተረጋጋና ዴሞክራሲ በሰፈነበት ሥርዓት፥ ከሙሰኝነት ርቆና ግልጽነት ባለው ሕጋዊና የአስተዳደር አካባቢ ለሁሉም እኩል በሚሠራ መልክ የተደላደለ ብሔራዊ መድረክና ሁኔታ (ለቨል ፕሌይንግ ፊልድ) መፍጠርን ይጠይቃል::

ሁለተኛ የኢኮኖሚና የኢንዱስትሪ የልማት ፖሊሲያችን በእርሻ ውጤት ላይ ብቻ ሳይሆን፥ በአገሪቱ እጅግ የተሰበጣጠረ ሀብት ላይ በመመርኮዝ በአገር ውስጥ ምርት፥ በአገር ውስጥ ገበያ፥ በአገር ውስጥ ፍጆታ ላይ ያተኮረና አምራችነትና ሸማችነት ተያይዘው የሚያድጉበት ዕመርታን የሚፈጥር ፖሊሲ መሆን ይኖርበታል::
ከዚህ አንፃር ሲታይ የኢሕአዴግ መንግሥት ብሔራዊ የኢኮኖሚ ልማትና የኢንዱስትሪላይዜሽን ስትራቴጂ ሦስት መሠረታዊና የተያያዙ ጉድለቶች አሉት::

በመጀመሪያ ገዥው ፓርቲ "ብሔራዊ" ሊባል የሚችል የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ የለውም:: የኢሕአዴግ ፖሊሲ በአንድ በኩል እጅግ ጠቦ በጎጠኝነትና በጠባብ ወገናዊነት

ተበክሎ አንዱን እያገዘ ሌላውን ለማቆርቆዝ ሆን ብሎ የሚሠራ ፀረ-ብሔራዊ የጋራ ጥቅም ፖሊሲ ነው፡፡ ይኸን ዓይነት አሠራሩን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያውቀውና ነጋ ጠባ የሚያማርርበት ስለሆነ ብዙም ዝርዝር ውስጥ መግባት አያስፈልግም፡፡

ሆኖም ገዥው ፓርቲ እዛው በዛው ነጋዴም፥ ኢንቬስተርም ሆኖ የግል ክፍለ-ኢኮኖሚውን (ሴክተር) ለመቆጣጠር የሚከተለውን ስትራቴጂ ከስምንት ዓመታት በፊት ለካድሬዎቹ ባሰራጨው የምስጢር ሰነድ ስለ “አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ኢንቬስተሮች”ና ስለተቀሩት ዜጎች ያስቀመጠውን ፖሊሲ መጥቀሱ ሁኔታውን በይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል ብለን እናምናለን፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በወቅቱ “ኢትዮጵያን ሬጂስተር” በተባለው መጽሔት እ.ኤ.አ. ጁን 1996 እትም በተጋለጠው ሰነድ ወያኔ “አብዮታዊ ዴሞክራሲዊ” በሚላቸው ወገኖቹና ከነሱ ውጭ ባለው የግሉ ኢኮኖሚ ቀጠና መደረግ ስላለበት አድልዖ ሲያትት በአንድ በኩል ተፈላጊ የሆኑት የኢኮኖሚ ኃይሎች እንዲያብቡ ጥረት እየተደረገ “ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋር የማይጣጣም ዓላማ ያላቸውን ኃይሎች ለመደምሰስ” መሥራት እንደሚያስፈልግ ከጠቆመ በኋላ ይኸን ተግባራዊ ለማድረግ ሰነዱ ከሚጠቁማቸው በርካታ እርምጃዎች አንዱ “የምንደግፋቸው ኃይሎች እንዲያብቡ ግብር የመቀነስ ወይም ጨርሶ የመማር ፖሊሲ እየተከተልን በማንደግፋቸው ኃይሎች ላይ ደግሞ የታክሱን ቀንበር ለመቆለል እንሠራለን” የሚል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ሁለተኛ ይኸው ጠባብና ብሔራዊ ራዕይ-አልባ የሆነ መርኃ-እቅድ (ፖሊሲ) ብሔራዊ ልማት ላይ ሳይሆን እነዚሁ ጥቂቶች በተቻለ ፍጥነት የተቻለውን ያህል ሀብት ለመዝረፍና ለማካበት ባላቸው ሕልም ላይ የተገነባ ፖሊሲ ነው፡፡

በዚህም የተነሣ ከገበያ ኢኮኖሚ ተብየው አንፃር ፋይዳ ቢስ የሆነውን ድህ ኅብረተሰብና ኢትዮጵያን ዘሎ በዓለም የገበያ ኢኮኖሚ ውስጥ በተዝረከረከ ሁኔታ ገብቶ ለመዘፈቅ ይንጠራራል፡፡

ልክ በእርሻ ልማት ተብየው ስትራቴጂ እንዳየነው የኢንዱስትሪው ፖሊሲም አገራችን “በዓለም-አቀፋዊው የኢኮኖሚ ትስስር ውስጥ” ገብታ በምታደርገው የልማት ጥረት “በዓለም ገበያ በዋጋና በጥራት ተወዳዳሪ የሆኑ ሸቀጦችን በማምረትና ኤክስፖርት በማስፋፋት ላይ ያተኮረ” እንደሚሆን በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ይኸ የኢትዮጵያንም ሆነ የአፍሪቃን የልማት ችግር የነዚህ አገሮች በዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ “በቅጡ አለመተሳሰር” አድርጎ የሚቆጥረው “የልማት እስትራቴጂ” ስለ አፍሪቃ ከዓለም ገበያ መገለል ወይም “ማርጅናላይዝድ” መሆን ሲያላዝን ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን ይረሳል፡፡

በአንድ በኩል የኛም ሆነ የአህጉራችን ችግር ምን ዓይነት ትስስር? የሚለው ጥያቄ እንጂ ከዓለም ኢኮኖሚ ጋር “ያለመተሳሰር” ችግር አይደለም፡፡ አህጉራችን ከባርያ ንግድ ጀምሮ እስከዛሬ ሳትወድ በግድና ጥቅሟን በማታገኝበት መልክ ከዓለም ኢኮኖሚ “በመተሳሰር” ስም እጅ እግሯን የታሰረች የደቀቀችና በመድቀቅ ላይ ያለች አህጉር ነች፡፡

ሁለተኛ የኢሕአዴግ ስትራቴጂ በዚህ ለድሀ አገሮች በማይመች የዓለም ገበያ ውስጥ እያለን ዕድገቴን “ኤክስፖርት በማስፋፋት ላይ እንዲያተኩር አደርጋለሁ” ሲል ዛሬ በለጸጉ ከሚባሉት ዋና ዋና አገሮች ማናቸውም ቢሆኑ በአገራቸው ምርትና ገበያ ተያይዞ ማደግ ላይ እንጂ የዕድገታቸውን አቅጣጫ “በኤክስፖርት ማስፋፋት ላይ ያተኮረ” ብለው እንዳልቀየሱ ሆን ብሎ የሚረሳ አስተሳሰብ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡

ሦስተኛ የኢሕአዴግ መሪዎች ስትራቴጂ ከዚህ እዛው በዛው እጅግ በጠበበና እጅግ በሰፋ “ራዕይ” ላይ የተገነባ ስለሆነ ለውጭ ገበያ እናቀርባለን የሚሉት ሸቀጥ አገሪቱ በዓለም ገበያ ያላት የሚመስላቸውን አንጻራዊ ጥቅም (“ኮምፓራቲቭ አድቫንቴጅ”) እጠቀማለሁ እያለ የሚግደረደር ስለሆነ “እናስፋፋለን” የሚሉት ንግድና ኢንዱስትሪ “በግብርናው ዕድገት ላይ የተመሠረተና ከግብርናው ኢኮኖሚያችን ጋር በጥብቅ የተያያዘ” እንደሚሆን ይነግሩናል፡፡ በግብርና ውጤት ላይ የሚመሠረተው የኢንዱስትሪያላይዜሽን ጥረት ከጠቅላላው የልማት ጥረት አንድ ዘርፍ ብቻ እንደሆነ፥ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት እንቅስቃሴ የግድ በእርሻ

ውጤት ዕጣ ፈንታ ላይ ሳይንጠለጠል "ራሱን ችሎ" ከግብርና ውጤት ጋር ምንም ግንኙነት በሌላቸው ግብዓቶች እየተጠቀመ መቀስቀስና ማደግ ያለበት ሰፊ ዘርፍ እንደሆነና ለምሳሌ ለሕዝባችን ኑሮ መደላደል ቤትና የጤና ጣቢያ (ክሊኒክ) ለመገንባት የስሚንቶና የጡብ ፋብሪካዎች ማቋቋም ከእርሻ ምርት የሚጠብቀው ግብዓት እንደሌለው ያልተገነዘበ <u>ግንጥል ስትራቴጂ ነው።</u>

<u>ከዚህ በመነሣት ዛሬ በአገራችን የኢንዱስትሪም ሆነ ሌላ የልማት ዘርፎች ወገናዊ የሆነ፥ ኢትዮጵያን የሚረሳና ምንም ብሔራዊነት የሌለውና የአገሪቱን ሰብዓዊና እጅግ የተሰበጣጠረ የተፈጥሮ ሀብት ተጠቅሞ ለኅብረተሰቡ ፍላጎትና ፍጆታ በማምረት ላይ ያልተቃኘ የልማት ተብየ አቅጣጫ ለውጦ ያለንበትን የድህነትና የመራቆት አዙሪት ለመስበር የሚከተሉትን ፖሊሲዎች ማራመድ ያስፈልጋል፤</u>

1.2.1 ከፍ ብለን በጠቀስነው መልክ መንግሥት የግሉ ክፍለ-ይዞታ (ሴክተር) በማይገባባቸው ለአውታሮች (ኢንፍራስትራክቸር)ና ለሌሎች ተቋማት ግንባታ ጥሪት እያፈሰሰ (ኢንቬስት እያደረገ) በሌላ በኩል ደግሞ የግል ክፍለ-ይዞታው በሙሉ ልብ በተለያዩ በኢንዱስትሪ፥ በሆቴል፥ በቱሪዝም፥ በማመላለሻ፥ በከብትና ዶሮ እርባታ፥ በኮንስትራክሽንና በመሳሰሉት የምርት የንግድና የአገልግሎት ቀጠናዎች እንዲሰማራ ሁኔታዎችን ለማደላደል ከፍተኛ ጥረት ማድረግ፤

1.2.2 ይኸንን እውን ለማድረግ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ከሁሉ አስቀድሞ የተረጋጋና ከሁሉምና ከምንም በላይ ደግሞ በታወቁ፥ በፀኑ፥ ግልጽነት ባላቸውና ሁሉም በእኩል በሚያከብራቸው ከሙሰኝነት በፀዳ ሁኔታ ያለአንዳች አድልዖ ለሁሉም እኩል በሚሠሩ ሕግጋት የሚገዛ ሥርዓት፥ በውጭ ብቻ ሳይሆን በኅብረተሰቡም ውስጥ ተኣማኒነት ያለው መንግሥት የልማት እንቅስቃሴ መሠረታዊ ዋስትና ስለሆነ፥ ይኸንን ዴሞክራሲያዊና የተረጋጋ ሥርዓት ባልተቋረጠ ሁኔታ እያጎለበቱ ለመሄድ ጥረት ማድረግ፤

1.2.3 የግል ይዞታው ክፍለ-ኢኮኖሚ ለአገራችን ልማት ቁልፍ ሚና ያለውን ያህል፥ በአሁኑ ወቅት ያለው ገዥ ፓርቲ ራሱ እንደ ነጋዴም፥ እንደ ኢንቬስተርም ሆኖ ጥቅም ማካበት ብቻ ሳይሆን፥ የፖለቲካ ይዞታውንም ዘላቂነት ለማረጋገጥ ይኸ ክፍል ከሱ ቁጥጥር ውጭ ባሉ ኃይሎች እንዳያድግ፥ እንዳይጠናከርና እንዳይዳብር በመፍራቱ የታመቀና የቀጨጨ ኃይል ለመሆን ስለበቃ፥ ኅብረቱ አገራችንን ከዚህ ሁኔታ ለማውጣት በሦስት አቅጣጫ መንቀሳቀስ እንደሚያስፈልግ ያምናል፤

1.2.3.1 በመጀመሪያ በአሁኑ ወቅት የኢሕአዴግ አገዛዝ የሚደነቅራቸውን የፖሊሲ ጋሬጣዎች እየታገሉ በአገሪቱ ልማት ለመሳተፍ በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ አምራቾችና ጥሪት-አፍሳሾች (ኢንቬስተሮች) የሚያጋጥሟቸውን እንቅፋቶች ለማስወገድ መንቀሳቀስ።

ለዚህም ፤-

1.2.3.1.1 የአገር ውስጥ ምርት ዕድገትን አንቆ የያዘውን የፋይናንስ ችግር ማስወገድ። በዚህ በኩል የኢሕአዴግ ኩባንያዎች በመንግሥታዊ ጡንቻ በመጠቀም ሥራ ለመጀመርም ሆነ ለማስፋፋት ብድር የማግኘት ችግር እንደሌለባቸው ሲታወቅ በአንጻሩ ሌሎች ዜጎች ይኸ ዕድል የላቸውም። በመሆኑም ይኸንን አድልዖኣዊ አሠራር ለማስወገድ የብድር አሰጣጥ ዘዴ ከማንኛውም አድልዖና ሙሰኝነት ነፃ የሆነ፥ የአበዳሪና የተበዳሪ መብቶችና ግዴታዎች በግልጽ የተቀመጡበትና ከሁሉም በላይ ደግሞ ለሁሉም ዜጎች በእኩል እንዲሠሩ የሚያደርግ ሕግና ይኸንን የሚቆጣጠር መንግሥታዊ ልዩ ኮሚሽን ይፈጠራል፤

1.2.3.1.2 የአገር ውስጥ አምራቾችን የሚያቆረቍዘውን የውጭ ምርት አቅርቦት መቋቋም። የአገራችንን የሰውና የተፈጥሮ ሀብት ግብዓትነት በተገቢ ተጠቅሞ ለኅብረተሰቡ

ፍጆታ የሚውል ቁሳቁስ በማምረት ላይ የተመሠረተ የንግድና የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ ካልን፥ በአንድ በኩል የአገራችን የማምረት ሂደት በተቻለ መጠን ከውጭ የሚመጡ ቁሳቁሶችን በመተካት ፖሊሲ ላይ የተገነባ ሲሆን፥ በሌላ በኩል ደግሞ ይኸ ብሔራዊ የልማት ጥረት እንዲሳካ ከውጭ ያለ ገደብ ወደ አገር ውስጥ እየገቡና ገበያውን እያጥለቀለቁ በማቆጥቆጥ ላይ ያለውን ብሔራዊ አምራች እያከሰሙ ያሉበት ሂደት የግድ መገታት ይኖርበታል። ይኸንን በልማት ጥረታችን ላይ ያንዣበበ ትልቅ አደጋ ለመቋቋም፤

1.2.3.1.2.1 ወደ አገር የሚገቡና በአልባሌ ዋጋ ገበያውን የሚያጥለቀልቁ (እንደ ጨርቃጨርቅ፥ ጫማ ወዘተ) ዓይነት ቁሳቁሶች የአገር ውስጥ ምርቶችን ለመፎካከር የቻሉት እነኝህን የማያመርቱ ተቋሞች (ድርጅቶች) ከየመንግሥታቸው በሚደረግ ስውርም ሆነ ግልጽ ልዩ ልዩ እርዳታና የገንዘብ ድጎማ ስለሆነ ይኸ ሆኖ ሲገኝ እነዚህ ቁሳቁሶች ወደ አገር እንዳይገቡ ማገድ፤

1.2.3.1.2.2 ወደ አገር እየገቡ ብሔራዊውን አምራች በማቆርቆዝ ላይ ካሉት ሸቀጦች አንዳንዶቹ በአልባሌ ዋጋ ለገበያ የሚቀርቡት ደረጃቸውን በአግባቡ የጠበቁ ባለመሆናቸው እንደሆነ ግልጽ ነው። ጫማ ተገዝቶ በማግሥቱ ይበተናል። የጨርቃ ጨርቅም ነገር እንደዚሁ ነው። ይባስ ብሎ አንዳንዶቹ ሸቀጦች ምንጫቸው እንኳን የትና ምን እንደሆነ አይታወቅም።
የኢትዮጵያ ደረጃዎች ጥራት ተብሎ የተቋቋመው መሥሪያ ቤት በኢሕአዴግ አቀባባዮች ጫና ወደ አገር በሚገቡት ምርቶች ትክክለኛና ተገቢ ቁጥጥር አድርጎ ጥራት የሌላቸውን ለማገድ የሚችልበት ሁኔታ ላይ ስላይደለ ይኸ መሥሪያ ቤት በሙያው ብቃት ባላቸውና የአገር ጥቅምን በሚያስቀድሙ ዜጎች አመራር ሥር እንዲሆን ማድረግ፤

1.2.3.1.2.3 በኢሕአዴግ መንግሥት አሠራር በአሁኑ ወቅት ያለው የግምሩክ ታሪፍ ፖሊሲ ይኸንን የኢሕአዴግ ኩባንያዎችና ደጋፊ ግለሰቦች በአቀባባይነት የሚሳተፉበትን አገር ገዳይ ውድድር ሆን ብሎ የሚያግዝ እንጂ የሚቋቋም ፖሊሲ አይደለም። የአገሬው አምራች ለኢንዱስትሪ ግብዓት ከውጭ የሚያስመጣቸው ጥሬ ዕቃዎች ላይና አልቆላቸው ወደ አገር በሚገቡ ምርቶች ላይ የሚጣለው ታሪፍ በጣም ተቀራራቢ ነው። በመሆኑም አገሬው ባለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃውን ወደ አለቀለት ምርት ለመቀየር ብዙ ወጭ አድርጎ ገበያ ሲያቀርብ በተመሳሳይ ታሪፍ ወደ አገር ከገባው የባዕዳን ሸቀጥ መወዳደር አይችልም። ይኸንን ማነቆ ለመቋቋም በአንድ በኩል ለፋብሪካ ዕቃዎች የሚሆን ጥሬ ዕቃ ላይ የሚጣለው ታሪፍ ዝቅ ብሎ ከውጭ በሚገቡ በአለቁ ምርቶች ላይ የሚጣለው በዚያኑ ያህል ከፍ እንዲል ማድረግ፤

1.2.3.1.2.4 ከዚሁ በተያያዘ ዛሬ በሃቅ እየሠራ ራሱንም አገሩንም ለመጥቀም የሚለፋው ጥሪት አፍሳሽ (ኢንቬስተር) እና ነጋዴ እንዲቀጭጭ ከሚያደርጉት ችግሮች አንዱ አሁንም በኢሕአዴግ ቸልተኝነትና አንዳንዴም በገዥው ፓርቲ አባላትና ካድሬዎች ተጠቃሚነት በሚካሄደው የጦፈ የኮንትሮባንድ ንግድ ወደ አገር እየገቡ ገበያውን በማጥለቅለቅ ላይ ያሉት ሸቀጣ ሸቀጦች እንደሆኑ ግልጽ ነው። ይኸንን ሁኔታ ለመቋቋም መንግሥት በኮንትሮባንድ ሕገ-ወጥ እንቅስቃሴና በአራማጆቹ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር የሚደረግበትን መንገድ ያመቻቻል፤

1.2.3.2 ሁለተኛ አቅሙም እውቀቱም ጉልበቱም እያላቸው በኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ውስጥ ለመግባት እየፈለጉ እስካሁን በተለያዩ ምክንያቶች ይኸንን እውን ለማድረግ ያልቻሉ ዜጎች እንቅስቃሴው ውስጥ በሙሉ ልብ እንዲገቡ ለማበረታታት፤

1.2.3.2.1 ሥራ ለመጀመር በቅድሚያ መሟላት ያለባቸውና የሚጠየቁ አስፈላጊ መተግብሮች (ፎርማሊቲዎች) አሁን ካሉበት ውስብስብነት ፀድተውና ከሁሉም በላይ ደግሞ ከቢሮክራሲ የሙሰኝነትና የዘፈቀደ አሠራር ተላቀው ግልጽ፥ ቀላልና ፈጣን እንዲሆን አግባብ ያላቸው የመንግሥት ተወካዮችና የግል-ይዞታው ክፍለ-ኢኮኖሚ ተጠሪዎች

መክረው ሕጋዊ የሥራ ፈቃድን አሰጣጥና አሰራረዝ፥ የንብረት ምዝገባን፥ የኢንቬስትመንት ዋስትናንና የውርስን ጉዳይ በተመለከተ አሁን ያሉትን አሠራሮች መርምረው፥ ከፍ ብለን ለጠቀስናቸው ዓላማዎች የሚታዘዙ ወይም የሚያገለግሉ መመሪያዎችና ሕግጋት አርቅቀው በፓርላማው እንዲጸድቁ ማድረግ፤

1.2.3.2.2 በተለያዩ የልማት ዘርፎች ለመሠማራት የሚሹ ዜጎች ለሚያቅዱት እንቅስቃሴ ካላቸውና ተጨማሪ ጥሪት (ካፒታል) የሚያስፈልጋቸው ሲሆን የብድር አሰጣጥ ዘዴ ከማንኛውም አድልዖ ነፃ ሆኖ በሚያቀርቡት እቅድ (ፕሮጀክት) ጠቃሚነት፥ አሳማኝነትና መስፈርትነት እንዲሆንና በሕግ የጸኑት የአበዳሪዎችና የተበዳሪዎች መብት ሙሉ በሙሉና ግልጽነት ባለው ሁኔታ እንዲከበሩ ይደረጋል፤

1.2.3.2.3 አቅም የሌላቸው ዜጎች በሥራ ፈጠራው ጥረት እንዲሳተፉና በገጠርም ሆነ በከተሞች በአሳሳቢ ሁኔታ እየተከማቸ የመጣውን ለመቦዘን የተገደደና ለድህነት የተዳረገ የሰው ኃይል (በተለይ የወጣቱን) ችግር ለመቅረፍ የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ ለማገዝ፤

1.2.3.2.3.1 ለአገር ልማት ሲባል ቅድሚያና ልዩ ትኩረት በሚሰጣቸው የምርትና የአገልግሎት እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሰማራት ለሚሹ ሥራ ፈጣሪዎች ለዚሁ ሆን ተብሎ በሚቋቋም የታዳጊ ኢንቬስተሮች ኮሚሽን አማካኝነት የመረጃ አቅርቦት፥ የቴክኒክ፥ የሕግ፥ የአስተዳደርና ሌሎች ምክርና አገልግሎቶች እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

1.2.3.2.3.2 በነዚህ ትኩረት በሚሰጣቸው መስኮች ለመሰማራት የሚሹ ሥራ ጀማሪ ዜጎች በተቻለ መጠን በራሳቸው ጥረት የሚሰበስቡት መነሻ ጥሪት (ካፒታል) በቂ በማይሆንበት ጊዜ ዜጎቹ በሚያዋጡት ካፒታል ላይ መንግሥት የተወሰነ እጅ (ፐርሰንት) በመጠነኛ ወለድ የብድር ዕርዳታ እንዲሰጥ የሚያስችል ፖሊሲ መቀየስ፤

1.2.3.2.3.3 በገጠርም ሆነ በከተማ ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች ሥራ ለመፍጠር የሚሹ ዜጎች መነሻ ጥሪት (ካፒታል) የሌላቸው ሲሆኑ፥ በሥራ-አጦች ማኅበር ተደራጅተውና ተደራድረው ሕጋዊ ሰውነት ሲያገኙ ኮሚሽኑ ከሚሰጣቸው የተለያዩ አገልግሎቶች በተጨማሪ በመጠነኛ ወለድ ብድር አግኝተው ዕቅዳቸውን በሥራ ለማዋል እንዲችሉ ማገዝ፤

1.2.32.3.4 ሥራ-አጦችና ሌሎች ታዳጊ ኢንቬስተሮች መነሻ ጥሪት (ካፒታል) ሲያስፈልጋቸውና ብድር ሲጠይቁ ለመሥራት ያሰቡትን እቅድ (ፕሮጀክታቸውን) አሳማኝነት፥ የኅብረተሰቡን ችግሮች ለመፍታት ሊኖራቸው የሚችለውን አስተዋጽዖ እንደዋስትና (ኮላቴራል) ቆጥሮ ይኸንን የብድር አገልግሎት የሚያቀርብ ለዚህም በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም-አቀፍ ደረጃ በአናሳና ጥቃቅን ብድር (በማይክሮ ክሬዲት) መስክ ከተሰማሩ ተቋሞችና መያዶች እንደዚሁም ከአበዳሪ ተቋማትና ለጋሽ አገሮች ተቀናጅቶ የሚሠራ አንድ <u>የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ባንክ</u> ተቋቁሞ ኅብረተሰቡን እንዲያገለግል ማድረግ፤

## 1.3 <u>የአካባቢን የውድመት ሂደት መቀልበስ፤</u>

የአካባቢ መዛባትና ውድመት ችግር ዛሬ በዓለም ደረጃ ከፍተኛ ትኩረት እያገኘ የሄደ ትልቅ ችግር ነው:: እየተከሰተ ያለውን ቀውስ ለመዋጋት ከፍተኛ ርብርቦሽ እየተደረገም ነው:: በኢትዮጵያና በተቀሩት የአፍሪቃ አገሮች የሚታየውን የአካባቢ ቀውስ በበለፀጉት አገሮች ከተከሰተው ጋር ስናነፃጽር ሦስት የተያያዙ ገጽታዎች የኛን ቀውስ አስከፊና አስደንጋጭ

ገጽታ ይሰጡታል::

አንደኛ በበለፀጉት አገሮች የአካባቢ ውድመት ጥያቄ የሚቀርበው የዛሬ ሃያ ሠላሳ ሃምሣ ዓመት እንዲያውም ከዚያም አልፎ በሚቀጥለው ክፍለ-ዘመን ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ከሚፈራው ችግር አንፃር ነው:: በኛ አገር ይኸ ቀውስ ነገ ተነገ-ወዲያ ሣይሆን ዛሬ ጉሮሯችንን አንቆ ይዞ ከዕለት ዕለት እየተባባሰ በመሄድ በቀጥታ የአገራችንንና የሕዝባችንን ኅልውና እየተፈታተነ ያለ ከባድ ቀውስ ነው:: ከግማሽ ክፍለ-ዘመን በፊት ከምድራችን አርባ በመቶው (40%) ደን የለበሰ ነበር:: ከየአቅጣጫው ከሚቀርቡ አሀዞች መካከል የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ይፋ የሚያደርጋቸውን ብንወስድ ዛሬ ከዚህ የቀረው ሁለት ነጥብ ሰባት በመቶ (2.7 %) ብቻ ሲሆን አገራችን በየዓመቱ 144ሺህ ሄክታር ደን ታጣለች:: በዚህም የተነሣ ከወዲሁ 2 ሚሊዮን ሄክታር መሬት መመለሻ በሌለው ሁኔታ ጠፍ ሆኗል:: የጫካ መመንጠር አንዱ መዘዝ በርሃማነትን ማስፋፋት ሲሆን ዝናብ ሲጥልም ሆነ ንፋስ ሲያይል ደግሞ የማይቀረው የአፈር መታጠብና መሸርሸር (ኢሮዥን) በመኖሩ አገራችን በየዓመቱ 1.9 ቢልየን ቶን አፈር ታጣለች:: በዚሁ ጫካ ውድመት ሳቢያ ከሁለት ዓመት በፊት ለተባበሩት <u>መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) የቀረበ ሪፖርት እንዳስጠነቀቀው ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ አገሪቱ በአሥር ዓመት ውስጥ ዋና ዋናና በኢትዮጵያ ብቻ አሉ የሚባሉትን ብርቅየ የዱር አራዊትና ዕፅዋት የምታጣበት አደጋ አለ::</u>

እነዚህን ቀውሶች የኢሕአዴግ መንግሥት አልፈጠራቸውም:: ነገር ግን በቸልተኝነት÷ በተሳሳቱ ፖሊሲዎችና ብዙውን ጊዜ ደግሞ በጥቅም በመገፋፋት እያባባሳቸው እንደሆነ የዚያኑ ያህል ግልጽ ነው:: የይስሙላ ሙከራዎች የሉም አንልም:: ነገር ግን ከሁለት ዓመት በፊት አንድ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የቀረበ ጥናት እንደሚያመለክተው እነዚህ ሙከራዎች "ብኩን (ፍሬቢስ)ና ያልተሳኩ" (futile & unsuccessful) ተብለው ተወግዘዋል:: ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ የኢሕአዴግ መንግሥት ይኸንን ለብሉይ ኪዳን ዘመን ርሃብና ድህነት የዳረገንን ቀውስ ከማባበስ አላቆመም:: አገራችንን ሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን እያመጣቸው ላሉ ዘመናዊ መቅሰፍቶችም እየዳረጋት ነው::

በድህነታችንና በርሃብተኛነታችን እየተሳበበ በማደበሪያና በፀረ-ተባይ ስም ያለአንጻች ቁጥጥር ለአገራችን አፈር ይስማሙ አይስማሙ ሳይጠና የሚገቡ ንጥረ-ነገሮች (ኬሚካሎች)÷ እንደ ፓዮኒየር ሃይብሪድ ኢንተርናሽናል ዓይነቶቹ ድንበር-ዘለል ኩባንያዎች ጋር በሚመሳጠሩ የኢሕአዴግ የንግድ ድርጅቶች አማካኝነት ወደ አገር እየገቡና ነባር የገበሬ ዘሮችን እየተኩ የአገራችንን የተፈጥሮ ዝንቅ (ባዮ ዳይቨርስቲ) በማውደም ላይ ያሉ በሰው ሠራሽ ዘዴ የተቀየሩና የማያስተማምኑ ዘሮች (ጂኤም ሲድስ) ገበሬው ነባር ዘሮቹን እየተወ እነዚህን አደገኛ ዘሮች እንዲዘራ የሚደረገው ግፊት . . . ይኸ ሁሉ ኢሕአዴግና ስግብግብ ኩባንያዎቹ እያመጡብን ያለ "ወያኔ/ኢሕአዴግ አመጣሽ" ዘመናዊ የአካባቢ ቀውስ ነው::

ከሦስት ዓመታት በፊት በመጋቢት 1994 በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የምግብና የእርሻ ድርጅት አዲስ አበባ ባደረገው ስብሰባ÷ በልዩ ልዩ ሰበቦች ወደ አገራችን የገቡ (አንዳንዴ በሌላው ዓለም የተከለከሉ) 3500 ቶን የሚሆኑ ኬሚካሎች ከአንድ ሺህ በላይ በሆኑ በተለያዩ ማከማቻ ቦታዎች <u>ያለ አንጻች ጥበቃና ጥንቃቄ</u> ተበትነው እንደሚገኙና ዛሬ ነገ ሳይባል በጥንቃቄ ተነስተው "አፍሪካን ስቶክ ፓይልስ ፕሮግራም" ተብሎ በተነደፈው ዕቅድ መሠረት በበለፀጉት አገሮች ወደተበጁ ልዩ ማከማቻዎች የሚወሰዱበት ዘዴ ካልተገኘ ይኸ "ጊዜውን ጠብቆ የሚፈነዳ የመርዝ ቦምብ" (ቶክሲክ ታይም ቦምብ) ከወዲሁ አፈሩን÷ ወንዞችንና ኩሬዎችን እየመረዘ ያለ ክምችት በሕዝቡ ጤናና በአካባቢው ላይ ይኸ ነው የማይባል ጥፋትና ውድመት ሊያስከትል እንደሚችል አስጠንቅቋል:: እስካሁን እንደሚታወቀው ከሆነ ከዚህ ክምር ውስጥ ወደ ፊንላንድ ተልኮ በሥነ-ሥርዓት እንዲወድም የተደረገው 113 ቶን ብቻ ነው::

ሁለተኛ ከበለፀጉት አገሮች ይበልጥ በአገራችን እየተከሰተ ያለው የአካባቢ ውድመት የተለየ

ገጽታ የሚኖረው ይኽ ቀውስ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የድህነት ውጤት መሆኑና የአካባቢ ውድመት ራሱ ደግሞ እዛው በዛው ለድህነት ምክንያት ሆኖ ሁለቱ ተያይዘው የሚያድጉበት አደገኛ ሁኔታ ውስጥ በመሆናችን ነው።
ይኽ ሁኔታ ደግሞ በኛ ኅብረተሰብ የሚያስከትለው መዘዝ ከበለፀጉት አገሮች የባሰ አስከፊ ሲያደርገው እናያለን።

የምድርና የአፈር መምከን የገበሬውን የማምረት ችሎታ በማምከን ርሃብን በማስፋፋት አያቆምም። በአንዳንድ አካባቢዎች እየታዘብን እንዳለነው ሌላው ቀርቶ በሆነ ባልሆነ የኬሚካል ማዳበሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶች መሬቱና አፈሩ ሲበከል በዚያ መሬትና አፈር ላይ ባዶ እግሩን የሚሄደው ገበሬና ቤተሰቡ ጤና ሳይቀር አደጋ ላይ እየወደቀ ነው።
ሌላም ችግር አለ። በበለፀጉት አገሮች የአካባቢን ቀውስ ለመቋቋም እያደገ የሚሄድ ግንዛቤና ከፍተኛ ጥንቃቄ ያለውን ያህል፥ በዚያው ልክ ደግሞ በነዚህ አገሮች የሆነ አደጋ ሲከሰት ያንን ለመቀልበስና ለመቋቋም መንግሥታዊ መዋቅሩም፥ እውቀቱም አስፈላጊ የሆነው ገንዘብም ሲኖር በእኛ አገር ይኽ ሁሉ ስለሌለ የቀውሱ ስፋት፥ ክፋትና መዘዝ የዚያኑ ያህል እንዲጨምር ያደርገዋል።

ከነዚህ ሃቆች ከተነሣን በአገራችን ምድር፥ አየር፥ ውሃና አዝርዕት ብሎም በሕዝባችን ላይ እየተፈጸመ ያለውን ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ ውድመት ለአጭርና ለረዥም ጊዜ በተነደፈ የተቀነባበረ አገርና ሕዝብ አድን ዕቅድ መዋጋት ምን ያህል አስፈላጊና አጣዳፊ እንደሆነ ለማንም ግልጽ ነው። በመሆኑም ኅብረታችን በዚህ ጉዳይ የሚከተሉትን ሀሳቦች እንደመመሪያ አርጎ ይንቀሳቀሳል።

## 1.3.1 የአካባቢን የውድመት ሂደት ለመቀልበስ መወሰድ ያለባቸው አጣዳፊ እርምጃዎች፤

1.3.1.1 በነባር ችግሮች ላይ አዳዲስ ችግሮች ተጨምሮ የውድመቱን ሂደት ላለማባባስ በ1984 ዓ.ም. በሪዮ ዲ ጃኔሮ በተፈረመው ዓለም-አቀፍ ስምምነት መሠረት ዛሬ በበርካታ አገሮች ተቀባይነት እያገኘ የሄደው "የጥንቃቄ መርኅ" (ፕሪኮሽነሪ ፕሪንስፐል) ሙሉ በሙሉና በፍጥነት በአገራችን በኢትዮጵያም በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ ያስፈልጋል። ይኸም ማለት በሌሎች አገሮች ጎጂ ነው ተብሎ የተከለከለ ማንኛውም ኬሚካል ወይም በሰው ሠራሽ ዘዴ የተቀየረ ዘር ወደ አገራችን እንዳይገባ ማገድ ብቻ አይደለም። በጥንቃቄ መርኅ መሠረት ጉዳት እንደማያደርሱ በውል ባለመረጋገጡ ለጊዜውም ቢሆን የታገዱ ኬሚካሎችና ዘሮችም ወደ አገር እንዳይገቡ ፈጽሞ የተከለከለ መሆን አለበት።

1.3.1.2 ማንኛውም ማዳበሪያ ሆነ ፀረ-ተባይ ኬሚካል ወደ አገር ከመግባቱ በፊት ለአየሩ ጠባይ፥ ለአፈሩ መስማማቱና ጠቃሚነቱ እንዲረጋገጥና ከዚህ ውጭ ሲሠሩ የሚገኙ አስመጭዎች በጥብቅ የሚቀጡበት ሕግ እንዲወጣና ተስማሚነታቸው የተረጋገጠላቸው ማዳበሪያዎችና ኬሚካሎች ከፍ ብለን በጠቆምነው መሠረት የትም ሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት ለተጠቃሚዎቹ አጠቃቀምን በተመለከተ በቅድሚያ አስፈላጊው ግንዛቤ እንዲሰጥ ማድረግ፤

1.3.1.3 ከፍ ተብሎ የተጠቀሰውን ከ3000 ቶን በላይ የሆነ አደገኛ ኬሚካል ክምችት በተመድ "አፍሪካን ስቶክ ፓይልስ ፕሮግራም" በመጠቀምና ሌሎች አግባብ ያላቸው ዓለም-አቀፍ ተቋማትና የአገር ውስጥ ጥረትን በማስተባበር ባስቸኳይ እንዲነሣ ማድረግ፤

1.3.1.4 በበለፀጉት አገሮች የተደነገጉትንና የሚሠራባቸውን ጥብቅ ቁጥጥር ለማምለጥ የሚሞክሩ ድንበር-ዘለል ኩባንያዎች የአዳዲስ ዕፅዋት ዘሮች፥ ማዳበሪያዎችና ሌሎች

ኬሚካሎች ለማምረት የሚያስፈልጓቸውን የሙከራ ሥራዎች በጉቦ በሚደለሉ ባለሥልጣኖች ትብብርና እገዛ ወደ ታዳጊ አገሮችና በተለይም በአፍሪቃ ውስጥ በኬንያ፥ ናይጄሪያ፥ ኢትዮጵያ፥ ደቡብ አፍሪቃና ጋና የማዛወር ዕቅዳቸውን በተግባር ላይ ለማዋል እየተንቀሳቀሱ በመሆኑ ይኸንን ሙከራ ማገድ፤

1.3.1.5 ለደን ውድመት ተጠያቂ ከሆኑት ምክንያቶች ያለ አንዳች ጥናት በግብታዊነት የሚደረጉ ሰፈራዎች መልክ በያዘ ሁኔታ እንዲካሄዱ፥ አንዳንድ ኢንቬስተሮች በየአካባቢው ባሉ ባለሥልጣናት ሙሰኝነት እየታገዙ ምንም የአካባቢ ጥናት በሌለበት ሁኔታ ለዘመናዊ እርሻ ደን መመንጠርና ብርቅየ እንስሳትን የማደን ሕገ-ወጥ ተግባር እንዲገታ እርምጃ መውሰድ፤

1.3.1.6 ለደን ምንጠራ አንዱ ሌላ ምክንያት ለሕዝቡ የማገዶ ፍጆታ መሆኑ ግልጽ ስለሆነ፥ በተለይ ከተሜው በእንጨት ማገዶ ከመጠቀም ይልቅ ወደ ኤሌክትሪክና ነጭ ጋዝ እንዲያተኩር በቅርቡ የተደረገውን የታሪፍ መጨመር ፖሊሲ ቀልብሶ ለተጠቃሚው ሕዝብ በተመጣጣኝና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በተደጎመ ዋጋ የአቅርቦት ፖሊሲ ማውጣት፤

## 1.3.2. <u>የአካባቢን የውድመት ሂደት ለመቀልበስ መወሰድ ያለባቸው የረዥም ጊዜ የፖሊሲ እርምጃዎች፤</u>

1.3.2.1 በደን ውድመትም ሆነ በበርሃማነት መስፋፋት፥ በኬሚካሎችም ሆነ በአፈር መሸርሸር፥ በእንስሳትና ዕፅዋት መጥፋትም ሆነ በሌላ መስክ እየተከሰተ ያለው ችግር ሁሉም የተያያዙ በመሆናቸው፥ በዚህ ሰፊ መስክ አንድ ሰፊና ቅንብር ያለው ፖሊሲ አውጭና አስፈጻሚ አካል ስለሚያስፈልግ፥ አሁን ያለውን የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የኃላፊነቱን መስክና ሥልጣኑን አስፍቶ <u>“የአካባቢ እንክብካቤ ሚኒስቴር” መሥሪያ ቤት ማቋቋም፤</u>

1.3.2.2 ይኸ ሚኒስቴር ከፍ ብለን በጠቀስናቸውና በሌሎች በተያያዙ መስኮች አገሪቱ መከተል ስላለባት ፖሊሲ እስካሁን በዓለም-አቀፍ ተቋማት፥ በራሱ በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፥ አግባብ ባላቸው አገር-በቀልና ዓለም-አቀፍ መያዶችና ሌሎች ማኅበራት የተጠቆሙ የመፍትሔ አሳቦችን በማካተትና እንዲሁም ከየአካባቢው ሕዝብ በመምከር አንድ “የአካባቢ መልሶ ማቋቋምና እንክብካቤ ስትራቴጂ” እንዲያወጣና የዚህንም ተግባራዊነት በኃላፊነት እንዲመራ ማድረግ፤

1.3.2.3 ለአካባቢ ውድመት ዋና መከላከያ ከላይና ከመሃል የሚወጡ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ሳይሆኑ፥ በየአካባቢው ዋና ባለጉዳይ የሆነው ኅብረተሰብ እንዲሁም በየደረጃው ይኸንን ክስተት ለመዋጋት የሚቋቋሙ የዜጎች ማኅበራት እንደመሆናቸው መጠን፥ በአጠቃላዩ የአካባቢ ጥበቃ አገራዊ ስትራቴጂ ማዕቀፍ ውስጥ ሁሉም ባልተማከለ ሁኔታ ኃላፊነቱን የሚወጣበት መንገድ ማዘጋጀትና ከዚህ አንፃር ሲታይ ቁልፍ ሚና ሊጫወቱ ለሚችሉ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ለተደራጁ መያዶች እገዛ ማድረግ፤

1.3.2.4 በዚሁ የሕዝብ ተሳትፎ ጉዳይ የአካባቢ እንክብካቤ ጥያቄ በኅብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ ያልተጨበጠበት በመሆኑና ያለዚህ ደግሞ ምንም እርምጃ ሊታሰብ ስለማይችል፥ በአጠቃላይ ሕዝቡም ሆነ በተለይ ደግሞ ገበሬው አካባቢ ከሚያወድሙ አሠራሮች እንዲቆጠብ ብቻ ሳይሆን አማራጭ መፍትሔዎችንም በመጠቆም ላይ ያተኮረ ሰፊና አገራዊ የግንዛቤ ዘመቻ ማካሄድ፤

1.3.2.5 እጅግ በሚያሳስብ መልኩ እየተፋጠነ ያለውን የበረሃ መስፋፋት ለመቋቋምና በተመሳሳይ ፍጥነት እየተራቆተ ያለውን የአገራችን ምድር በደኖች ለማልበስ ሰፊ የዛፍ

ተከላ ዘመቻ በተቀናበረ መልክና ሁኔታ ማካሄድ፤

1.3.2.6 በዚህ አገር-አድን ዘመቻ ሕዝቡ በሚሊዮን በሚቆጠር ደረጃ እንዲሳተፍ ከተፈለገ በዛፍ ተከላም ሆነ በጠቅላላው በአካባቢ ጥበቃው ጥረት በሙሉ ልብ እንዲገባበት የኢሕአዴግን የመሬት ይዞታ ሥሪት ቀይሮ ገበሬው በማሣው ላይ የባለቤትነት መብቱ መረጋገጡ ቁልፍ ጥያቄ ስለሆነ መሬት ከመንግሥት ቁጥጥር ወጥቶ ወደሕዝብ እጅ እንዲገባ ከፍ ብለን ባመለከትነው መልክ የመሬት ሥሪቱን ማስተካከል፤

## 1.4 ከአገር ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን በአገር ግንባታው ጥረት ማሳተፍ፤

የኢትዮጵያውያን በሰፊው ከአገር የመሰደድ ሂደት ከሠላሳ ዓመታት ወዲህ የመጣ የቅርብ ጊዜ ክስተት ቢሆንም፥ በአሁኑ ወቅት በብዙ መቶ ሽዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በመላው ዓለም ተበትነው ይገኛሉ። ሂደቱ ከአብዮቱ ጋር በተያያዘ አለመረጋጋትና በሱ ታኮ የመጣው የደርግ አገዛዝ አምባገነንነት፥ በዜጎች ላይ የጀመረው ጭፍጨፋና ጦርነቶች ተጋግዘው የቀሰቀሱት ቢሆንም የዴሞክራሲ መጥፋት፥ የሰላም አሁንም በቋፍ መሆን፥ የሕዝብ አመኔታና ተጠያቂነት የሌለውና ከሁሉም በላይ ደግሞ ብዙ ዜጎች እንደፀረ-አገር አድርገው የሚቆጥሩት መንግሥት መተከል ጋር ተደራርቦ የወጡት እንዳይመለሱ ብቻ ሳይሆን፥ አዲስ የስደት ማዕበል በመቀስቀሱ አሁን ያለንበት ደረጃ ላይ ደርሰናል።
ከዚህ ከስደት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሌላ የሚታየው ክስተት አገራችንን በማድማት ላይ ያለው የተማረ የሰው ኃይል ፍልሰት (ብሬይን ድሬይን) የተባለው አስከፊ ክስተት ነው። በዚህ ለአገራችን አዲስ የሆነ የምሁራን ፍልሰት የተነሣ፥ ዛሬ ኢትዮጵያ አስተምራ ለበለፀጉት አገሮች የምትገብረው የምሁራን ቁጥር ሲታይ በአፍሪቃ ከጋናና ከናይጄሪያ ቀጥሎ ሦስተኛ ቦታን እንድትይዝ አድርጓታል። ነገሩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ ለማሳየት በችካጎና አካባቢዋ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሃኪሞች ቁጥር ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ሃኪሞች ቁጥር እንደሚበልጥ መጠቆሙ ብቻ የሚበቃ ይመስለናል።

ይኸም ሁሉ ሆኖ ዛሬም ባለው ያልተመቻቸ ሁኔታም ቢሆን በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው የኢኮኖሚ፥ የፖለቲካና ማኅበራዊ ጉዳዮች ለመሳተፍ ለሕዝባችን የተሻለ ቀን ለማምጣት በአገርና በወገን ፍቅር እየተነሣሱ የተቻላቸውን አስተዋጽዖ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ። እነዚህ ወገኖቻችን በየዓመቱ ለወዳጅ ዘመድ የሚልኩት ገንዘብ ዛሬ ግማሽ ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር አልፎ አገራችን ከውጭ ንግድ ከምታገኘው ገንዘብ ከግማሽ በላይ ሆኖ ይታያል። ብዙ ወገኖቻችን በአገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ሂደት ለመሳተፍ ሙሰኝነትንና የቢሮክራሲ ውጣ ውረድን እየተቋቋሙ ጥሪታቸውን በአገር ውስጥ ለማዋልና ለማፍሰስ (ኢንቬስት ለማድረግ) ይሞክራሉ። ሌሎች 'አገሬ ዞሮ መግቢያዬ' ብለው ለጡረታ ዘመናቸውም ሆነ በአገራቸው ለልጆቻቸው ቅርስ ለመተው ቤት በመገንባት ጥረት ላይ ይገኛሉ። ምሁራን በየመስካቸው ባላቸው እውቀት ለመሥራት ወይም እውቀታቸውን ለታዳጊው ትውልድ ለማካፈል በዓመት ለተወሰኑ ወራትም ይሁን ሳምንታት በፈቃዳቸው ወደ አገር እየተመላለሱ አገልግሎት የማበርከት ሂደት ጀምረዋል። ሌሎች የአገሪቱ የፖለቲካና የሰብዓዊ መብት ሁኔታ ተሻሽሎ ኢትዮጵያ የተረጋጋ የሰላምና የልማት ጎዳና እንድትይዝ በያሉበት በመታገልና ለነዚህ ብሔራዊ ዓላማዎች በአገር ውስጥ የሚካሄደውን ትግል በአሳብም በአቅምም ከመደገፍ ያቋረጡበት ወቅት የለም። በአጭሩ በዚች በአገር ወዳዶች በተትረፈረፈች አገራችን ኢትዮጵያውያን በአካል እንጂ በመንፈስና በጭንቀት ከኢትዮጵያ ችግሮች ውጭ አይደሉም።

ጥያቄው በዓለም ዙሪያ ተበትነው ለአገራቸው ርምጃ ይኸ ነው የማይባል ከፍተኛ አስተዋጽዖ

በማድረግ ላይ ያሉትን የቻይና፥ የሕንድ፥ የአየርላንድ፥ የግሪክና የሌሎች ዜጎችን ምሳሌ ተከትለን ይኸ ዛሬ ገና በማቆጥቆጥ ላይ ያለው ዘርፈ ብዙ ተሳትፎ በኢትዮጵያም በምን ዘዴ ይጎልብት፥ በምን ዘዴ መልክ ይያዝና እንዴትስ ፍሬያማ ይሁን የሚለውን ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ወገኖቻችንን አስጨንቆ የያዘውን ጥያቄ አንስቶ ለዚህ ተገቢ መልስ የመስጠት ጉዳይ ነው።

ይኸንን ጥያቄ ለመመለስ የመጀመሪያ መጀመሪያ የሚሆነው ቅድመ ሁኔታ የዚህ ሁሉ ስደትና መፈናቀል፥ እንዲሁም በውጭ ያሉትን ዜጎች የተሳትፎ ፍላጎት አምቆ የያዘውንና ያኮላሸውን የፖለቲካ ሁኔታ ቀይሮ፥ ዴሞክራሲያዊና የሰብአዊ መብቶች ዋስትና ባለው ሁኔታ የሚከበሩበት የተረጋጋ ኅብረተሰብን እውን የማድረጉና በዚህ ኅብረተሰብ ውስጥ በአገር ፍቅሩና በኃላፊነት ስሜቱ በአርዓያነት የሚጠቀስ መንግሥት የማቋቋም ቅድመ ሁኔታ ነው።
ለኢትዮጵያውያን በአገር ጉዳይ ተሳተፉ ብሎ ጥሪ ሲደረግ፥ ለባዕዳን ባለሀብቶች ወጥታችሁ ኢንቬስት አድርጉ በሚለው መልክ የሚደረግ ጥሪ አይደለም። ወደዚህ ተሳትፎ የሚገፋፋቸው ሌላ ምንም ነገር ሣይሆን ለአገራቸው ያላቸው ፍቅር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በመሆኑም ይኸንን ጥሪ አድርጎ የመደመጥ ዕድል የሚኖረው ኃይል በጤናማ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኛነቱ አርአያነት ያለው መንግሥት እንጂ እንደ ኢሕአዴግ ኅልውናውን በጎሰኝነትና ኢትዮጵያውያንን በማናከስ ላይ አንጠልጥሎ የአንድነትና አገር ፍቅር ስሜትን በሚያኮስስ ኃይል እንዳይደለ ግልጽ ነው።

ይኸንን መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታ የሚያሟላ ኃይል ከዚህ ቀጥሎ በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያንን ተሳትፎ በተመለከተ ፖሊሲና ስትራቴጂ ለማውጣት ከፈለገ፥ አንደኛ ይኸንን ፖሊሲ ባለጉዳዮቹ ራሳቸው ጋር መክሮና ዘክሮ መንደፍ እንዳለበት ግልጽ ነው። ሁለተኛ ደግሞ ይኸ ፖሊሲ ዛሬ የኢሕአዴግ መንግሥት እንደሚሞክረው "ገንዘብ ላኩ፥ ኢንቬስት አድርጉ፥ ቤት ሥሩ፥ ፖለቲካውንም ሆነ ሌላውን ሁሉ ለኔ ተዉት" በሚል ጠባብ የኢኮኖሚ ጥሪ መወሰን የለበትም።
የሚነደፈው ፖሊሲ ከዚህ በጣም ሰፍቶ በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን በአገራችን የኢኮኖሚ፥ የፖለቲካ፥ የማኅበራዊ፥ የምሁራዊ፥ የሥነ-ጥበብ፥ የሳይንስ፥ የኪነትና የዓርት፥ የሙዚቃና የመሳሰሉ ዘርፎች "ይኸ ሁሉ ያገባናል ብላችሁ ግቡበት" ብሎ ለዚህ ዘርፈ-ብዙ ተሳትፎ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ፖሊሲ መሆን ይኖርበታል።

ሦስተኛ ይኸ ፖሊሲ ሲነደፍ በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን የአገር ፍቅር ስሜታቸውና የተሳትፎ ፍላጎታቸው የማይተናነስ ቢሆንም፥ ለአገር ግንባታ የሚያደርጉት አስተዋጽዖ በተለያየ ደረጃና መልክ ተግባራዊ እንደሚሆን መረዳት ያስፈልጋል።
ንብረቱን፥ እውቀቱንና ቤተሰቡን ይዞ ወደ አገር ተመልሶ ለመሳተፍ የሚፈልግ አለ። ጠቅልሎ ከመመለስ ይልቅ እየተመላለሰ አገሩን ለማገልገል የሚሻ ዜጋ አለ። በአካል በአገር ውስጥ የመገኘት አሳብ ሳይኖረው ባለበት ሆኖ የተሳትፎ መስክ እንዲመቻችለት የሚመኝ ዜጋም በርካታ ነው። ፖሊሲያችን ይኸንን የተሰበጣጠረ ሁኔታ ከቁጥር አስገብቶ መነደፍ ይኖርበታል ማለት ነው።
ከዚህ ተነስተን ዝቅ ብለን በመንጠቁመው መልክ "በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን አገራዊ ጉባዔ" ብለን በምንጠራው ስብሰባ የሚስፋፋና የሚዳብር ቢሆንም እነዚህን ሦስት የፖሊሲ አነዳደፍ መርኅዎች በመከተል በዚህ ጉዳይ የሚከተሉትን አማራጮች እንሰነዝራለን።

### 1.4.1. በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያንን ተሳትፎ መልክ ማስያዝ፤

1.4.1.1 በውጭ አገር የሚኖሩ ዜጎችን ሁኔታ የሚከታተል፥ መብታቸውን ለማስከበር የሚሠራ፥ ስለ ኢኮኖሚም ሆነ ሌላ ተሳትፏቸው ዕቅድ እያወጣ አሳብ የሚያቀርብ፥ ሴሚናሮች፥ ሲምፖዚዬሞችንና ኤክስፖዎች የሚያዘጋጅ፥ በየአህጉሩ የሚኖሩት

ኢትዮጵያውያን እንዲገናኙ መረብ የሚዘረጋ፣ የንግድ፣ የትምሕርት፣ የሥነ-ጥበብ፣ የምርምር ልውውጥ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን የሚያመቻች አንድ እራሱን የቻለ <u>"በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን"</u> ማቋቋም፤

1.4.1.2 በውጭ አገር የሚኖሩ ዜጎች በያሉበት እየተደራጁ በተወካዮቻቸው አማካኝነት ከዚህ ኮሚሽን ጋር እየተገናኙና እየመከሩ የተሳትፎ መስኮችን የሚመረምሩበትና እውን የሚያደርጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

1.4.2 <u>በውጭ ያሉ ዜጎችን የተሟላ የዜግነት መብትን ማረጋገጥ፤</u>

1.4.2.1 በውጭ ለሚኖሩና የሌላ አገር ዜግነት ለወሰዱ ኢትዮጵያውያን የጥምር ዜግነት መብት ማረጋገጥ፤

1.4.2..2 የነዚህን ዜጎች ሙሉ መብት ለማረጋገጥና በአገሪቱ የፖለቲካ ሂደት ተሳትፏቸውን ለማጎልበት የተሟላ የመምረጥና የመመረጥ መብት ማወቅና ይኸንን ተሳትፎ ተጨባጭ ለማድረግ በአገሪቱ ፓርላማ የተወሰነ መቀመጫ ሰጥቶ ተወካዮቻቸውን እንዲልኩ ማስቻል፤

1.4.3. <u>በውጭ ያሉ ዜጎችን የኢኮኖሚ ተሳትፎ ማጎልበት፤</u>

1.4.3.1 ከፍ ብለን የጠቀምነው ከፍተኛ ኮሚሽን በውጭ ካሉ ኢትዮጵያውያን ተወካዮችና በአገር ውስጥ ካሉ እንደ ንግድ ምክር ቤትና ሌሎች አግባብ ያላቸው ስብስቦች ጋር መክሮ ፍሴተ-ንዋይን (ኢንቬስትሜንትን) በተመለከተ ዋስትና የሚረጋገጥበትን፣ የተለያዩ የቢሮክራሲ ማነቆዎችና ሙሰኝነት የሚወገዱበትን፣ ውጭ ያሉት ሲፈልጉ ብቻቸውን ሲፈልጉ ደግሞ ከአገር-በቀል ኢንቬስተሮች ተጣምረው የሚሠሩበትን መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊነቱን እንዲከታተል ማድረግ፤

1.4.3.2 እነዚህ ዜጎች በአገር ውስጥ ያሉ ዘመዶችና ወዳጆች ለዕለት ኑሮ ማሸነፊያ ገንዘብ በተከታታይ ከመላክ ይልቅ፣ ወገኖቻቸውን በኢኮኖሚ ለማቋቋም ከፈለጉ ከፍተኛው ኮሚሽን የሚቀርበውን የምርት ወይም የአገልግሎት እንቅስቃሴ እቅድ (ፕሮጀክት) መርምሮ በውጭ ያሉ ዜጎች በውስጥ ላሉ ወገኖቻቸው ብድር የሚያስገኙበትን መንገድ መቀየስ፤

1.4.3.3 ከፍ ብለን በጠቀስናቸው ውጭ ባሉ ዜጎቻቸው ተሳትፎ የተጠቀሙ አገሮችን ምሳሌ በመከተል፣ በኛም አገር በውጭ የሚገኙ ዜጎች በአገር ውስጥ ባንኮች ገንዘባቸውን እንዲያስቀምጡ ተኣማኒነት ያለው ልዩ የወለድና የዋስትና ፖሊሲ ነድፎ በተግባር ማዋል፤

1.4.4 <u>በውጭ ያሉ ዜጎችን እውቀትና የሥራ ልምድ ለአገር ጥቅም ማዋል፤</u>

1.4.4.1 ዛሬ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በጤና፣ በትምሕርት፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በእርሻ፣ በንግድ፣ በአስተዳደር፣ ወዘተ.... ለያሉባቸው አገሮች ዕድገትና ልማት ከፍተኛ አስተዋጽዖ የማያደርጉበት መስክ የለም ማለት ይቻላል:: ከነዚህ ወገኖቻችን አንዳንዶች ሁኔታዎች ቢመቻቹ በሙያቸው አገር ተመልሰው ለማገልገል ዝግጁ ሲሆኑ፣ ሌሎች ደግሞ በቋሚነት በዛው ባሉበት ሆነው ነገር ግን አገራቸውንም ለማገልገል ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው ግልጽ ነው::
እነዚህን ዜጎች በአገር ግንባታው ጥረት ለማሳተፍ፤-

1.4.4.1.1 በውጭ ካሉ የባለሙያዎች ማኅበራት ጋር በመመካከር ሐኪሞች፣ ዩኒቨርስቲ መምህራንም ሆኑ ሌሎች ምሁራን የረዥምም ሆነ የአጭር ጊዜ እረፍት በመውሰድ ወደ

አገራቸው እየተመላለሱና ፈረቃ እየገቡ በሙያቸው አገልግሎት የሚያበረክቱበትን ዘዴ ማስፋፋትና ለዚህ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

1.4.4.1.2 በትምሕርትና በልምድ ከፍተኛ እውቀት ያካበቱ ዜጎች ይኽንን እውቀትና ልምድ በአገር ውስጥ ላሉ ወገኖቻቸው ለማካፈል እንዲችሉ በየሙያውና በየመስኩ ኮንፍረንሶች፥ አውደ-ጥናቶችና ትምሕርታዊ ጉባዔዎች ማሰናዳትና ሲቻል በአካል በመገኘት ይኽ ሳይቻል ደግሞ ጥናታዊ ጽሑፎች በመላክ የሚሳተፉበትን መንገድ ማበጀት፣

### 1.4.5 <u>በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አገር-አቀፍ ጉባዔ መጥራት፣</u>

1.4.5.1 በከፍተኛው ኮሚሽን አነሳሽነትና በውጭው ዓለም በያለበት በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተወካዮች ትብብር በአጠቃላይ እነዚህ ዜጎች አገራችንን መልሶ ለማቋቋምና የዴሞክራሲና የልማት አቅጣጫ ለማስያዝ በሚደረገው ጥረት ተሳትፏቸው የሚጎለብትበትን ሁኔታ መርምሮ የአጭርና የረዥም ጊዜ ዕቅድ የሚያወጣ አንድ ሰፊ ጉባዔ ማዘጋጀት፣

1.4.5.2 በዚህ አገር-አቀፍ ጉባዔ የሚነደፈውን ዕቅድ ተግባራዊነት ለመከታተል አስፈላጊ የሚሆኑት ተቋማትና የግንኙነት መረቦች የሚዘረጉበትን ዘዴዎች ማመቻቸት፣

## 1.5 <u>ማኅበራዊ ቀውሶችን መቋቋም፣</u>

ከርሃብ፥ ከመናጢ ያጣ የነጣ ድህነት፥ ከጅምላ ሥራ-አጥነት በተጨማሪና ከነሱም ጋር ተያይዞ ዛሬ በኢትዮጵያችን ላይ የሚጨፍሩት ከባድና ዘግናኝ ማኅበራዊ ቀውሶች ከራስ ጠጉር የበዙ ናቸው::
ኤች. አይ. ቪ. ኤድስ ሦስት ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎችን ለክፉ በየዓመቱ በመቶ ሽህ የሚቆጠሩ ዜጎችን ሕይወት እየቀጠፈ ነው:: ከዚህ ውስጥ ሁለት መቶ ሽህ ያህሉ ሕፃናት ናቸው:: በዚሁ መቅሰፍት ሳቢያ እስካሁን ቁጥራቸው ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ሕፃናት ወላጅና አሳዳጊ አልባ ሆነዋል::
በሽታው በተለይ የሚያጠቃው ከአሥራ አምስት እስከ አምሳ ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ዜጎችን ስለሆነ የአገሪቱ አምራች ኃይል እየወደመ ነው:: ይኽ የኤኮኖሚ ቀውስ ሳይበቃ በማኅበራዊው መስክ ዛሬ እየጎላ በመታየት ላይ ያለው ቀውስ የቲም ልጆች ቁጥር አስደንጋጭ በሆነ ፍጥነት መበራከታቸው ብቻ አይደለም:: አንድ ቀን ልጆቻችን አድገውና ሰው ሆነው ይጦሩናል እያሉ የእፎይታ ዘመን በጉጉት ሲጠብቁ የነበሩ አሮጊትና ሽማግሌዎች በአቅምም በገንዘብም ከደከሙ በኋላ በሕይዎታቸው ማምሻ ላይ የልጅ ልጅ ለማሳደግ በሌላ በኩል ደግሞ ለአቅም ያልደረሱ ልጆች በለጋ ትከሻቸው የቤተሰብ ሃላፊነት ተረክበው ለማስተዳደር የተገደዱባቸው ሁኔታዎች በጣም በርካታ ናቸው::
ከዚሁና ከሌሎች ቀውሶችም በተያያዘ ዛሬ በአገራችን የጎዳና ተዳዳሪ ልጆች ቁጥር የኢሕአዴግ መንግሥት እንደሚለው መቶ አምሳ ሽህ ብቻ አይደለም:: ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ መያዶች ይኽንን ቁጥር ስድስት መቶ ሽህ ያደርሱታል:: መንግሥት በአዲስ አበባ ስልሳ ሽህ ጎዳና ተዳዳሪ ልጆች የሚለውን እነዚሁ ወገኖች መቶ ሽህ እንደሆነ ይገልጻሉ:: በቅርቡ የዴንማርኩ የልጆች ደኅንነት ድርጅት (ሴቭ ዘ ችልድረን) ባወጣው ማስጠንቀቂያ በአገራችን አንዳንዴም አሥራ ሦስት ዓመት እንኳ ያልሞላቸው የልጆች ሴተኛ አዳሪ ቁጥር <u>"አስደንጋጭ"</u> በሆነ ፍጥነት እያደገ መሆኑን አስታውቋል::

ዛሬ ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ጋር ተያይዞ የደከመና መከላከያ የሌለውን ሰውነት በማጥቃት ላይ ያለው የሳምባ ነቀርሳ ሌላ መቅሰፍት እየሆነ በመምጣቱ ሰዎች በሽታውን ከሚፈጥረው

ተውሳክ (ከቫይረሱ) "ተሸካሚነት"/"ማደሪያነት" ወደ በሽተኛነት እየተሸጋገሩ በወራት ውስጥ የሚቀጠፉበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። በአፍሪቃ የተውሳኩ (የቫይረሱ) ተሸካሚ ከሚባሉት ከሃያ አምስት ሚሊዮን ሕዝብ ውስጥ ስምንት ሚሊዮን የሳምባ ነቀርሳ የተጨመረባቸው ፋታ በማይሰጥ ሁኔታ እየተቀጠፉ ነው። በአገራችን በዚህ ዓይነት ሁለቱ መቅሰፍቶች የተደራረቡባቸው ዜጎች ወደ ስምንት መቶ ሽህ ይጠጋሉ። በቅርቡ በባንኮክ (ታይላንድ) በተደረገ ዓለም-አቀፍ ስብሰባ የቀድሞው የደቡብ አፍሪቃ ፕሬዝደንት ክቡር አቶ ኔልሰን ማንዴላ "ኤች.አይ.ቪ. በተለከፉ ዜጎች ላይ የሳምባ ነቀርሳ ሲጨመር የሞት ፍርድ ማለት ስለሆነ ይኽንንም በሽታ ሳንዋጋ ኤች. አይ.ቪ.ኤድስን መዋጋት አንችልም" በማለት የሁለቱን መቅሰፍቶች ቁርኝት ጠቁመዋል።

በዚህ ሁሉ ላይ ደግሞ በዚች የመከራ ቋት እየሆነች በሄደችው አገራችን ከሃያ ዓመታት በፊት በቁጥጥር ሥር ዋለ ተብሎለት የነበረው የወባ በሽታ ቀደም ሲል በተወሰኑ አካባቢዎች ተገድቦ ቆይቶ አሁን እጅግ አሳሳቢ በሆነ ሁኔታ ለዚህ ተውሳክ ተጋልጠው ቀደም ሲል በሽታው ደርሶበት በማያውቅ አካባቢዎችና ሌላው ቀርቶ ወደ ከተሞችም እየዘለቀና እየተዛመተ ከፍተኛ ውድመት በማድረስ ላይ ይገኛል። በዚህ መስክ የተሰማራ "ፀረ-ወባ ድርጅት" የተባለ መያድ ባቀረበው ዘገባ በጎጃም አንዳንድ አካባቢዎች በበሽታው ፅናትና ስፋት የተነሳ ቤተሰብ እንዳለ እያለቀ ቤቶች ወና የሆኑባቸው ዘግናኝ ሁኔታዎች መከሰታቸውን ዘግቧል።

እንደማንኛውም አመራር-አልባ የሆነ ኅብረተሰብ ከፍተኛ ቀውሶች በተከሰቱ ቁጥር የዚህ ገፈት ዋና ቀማሽና የቀውሱ ሰለባ የሚሆኑት ሴቶችና ሕፃናት እንደመሆናቸው መጠን በእኛም አገር በዚህ በኩል ያለው ሁኔታ እጅግ አስከፊ ነው።

ዛሬ ኢትዮጵያ ከዓለም አገሮች በሙሉ እናት መሆን ከሁሉም በላይ አስከፊ የሆነባት አገር ተብላ ተፈርጃለች። ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ቢባል በበሽታው ከተለከፉት ዜጎች መኻል ስድሳ በመቶ (60 %) ሴቶች ናቸው። ዛሬ በአገራችን ከሳንባ ነቀርሳ ጀምሮ የወጣት ሴቶችን ሕይዎት የሚቀስፈው ሕገ-ወጥ ማስወረድ ሲሆን በአሜሪካን አገር ከመቶ ሽህ ሴቶች አንድን ሴት የሚገድለው በኛ አገር ማስወረድ ከሚሞክሩ በ16 እና በ20 ዕድሜ ክልል ውስጥ ካሉ መቶ ሽህ ወጣት ሴቶች አንድ ሽህ ሁለት መቶ አሥር (1210) ይሞታሉ። በአገራችን የሴቶች ቁጥር ከወንዱ ቢበዛም የትምሕርት ዕድል ከሚያገኙት ውስጥ የወንዶቹ ቁጥር ከሴቶቹ ቁጥር ሃያ በመቶ (20%) ይበልጣል።

ተዘርዝሮ የማያልቀውን የእናቶቻችንን፥ የእህቶቻችንንና የሴት ልጆቻችንን ሁኔታ ባለፈው ጥቅምት ወር አገራችንን የጎበኙት የዓለም ባንክ ዋና ዲሬክተር ጥቅምት 7 ቀን 1997 ዓ/ም በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ በዚች አገር ድህነት፥ የጤና አገልግሎት፥ የትምሕርት ዕድል፥ ወዘተ... ችግር አለ ቢባል የዚህ ሁሉ ገፈት ቀማሽ ሴቶች መሆናቸውን ጠቁመው በኢትዮጵያ ሴቶች የሚገኙበትን ሁኔታ ሲያጠቃልሉ "ብሔራዊ ሃፍረት" (ናሽናል ዲስግሬስ) ብለው ጠርተውታል።

**ዛሬ ጉሮሮችንን አንቀው የያዙትን ቀውሶች ለመቅረፍ ምንም ብቃት የሌለው አገዛዝ መጭውንም ለማዘጋጀት ፍላጎቱም ራዕዩም የለውም። እከተለዋለሁ የሚለው የትምሕርት ፖሊሲም ወይ ሥራ ፈጣሪ ወይ ደግሞ ለሥራ ተፈላጊ የሆነ በአገሩና በታሪኩ ኩራት የተሰማው የወደፊቱን የትውልድ ድርሻውን ለመወጣት የሚችል ወጣት በማነፅ ላይ የተገነባ አይደለም።**

በብዙ ባለሙያዎች "ትውልድ ገዳይ" ተብሎ የተኮነነው የትምሕርት ፖሊሲ ታዳጊውን ትውልድ "ተምሮ" ሲጨርስ በየቀኑ እየደለበ ያለውን የሥራ አጡን ሠራዊት ከመደባለቅ ሌላ ምንም አድማስ የሌለው ቀቢጸ-ተስፋ ዜጋ የሚያደርግ ሆኖ ይታያል።

ይኽ ቀቢጸ-ተስፋነት ደግሞ ወጣቱን የወደፊት ዕድሉን ይበልጥ ወደሚያጨልሙ እንደ ጫት እና አልኮል፥ እንደ ዝሙትና ወንጀል የመሳሰሉ ጎጂ አዝማሚያዎች በሚያስደነግጥ ፍጥነት እንዲያዘነብል እያደረገው ነው።

የትምሕርት ፖሊሲው ኢሕአዴግ ለተለከፈበት የጎሳና የአገር መከፋፈል መርዝ እንዲያገለግል ሆኖ የተነደፈ በመሆኑ ይኽንን ዓላማውን የሚቃወሙ መምሕራንን አፍኖ፥ አንጋፋ ማኅበራቸውን ኢ-መማን አዳክሞ፥ የትምሕርት ባለሙያዎችንና ሊቆችን

(ኤክስፐርቶችን) በትኖ፥ ትምሕርት ሚኒስቴርንና በየደረጃው ያሉትን መዋቅሮቹን በስልጡን ካድሬዎች በመሙላት የታዳጊውን ትውልድ የወደፊት ዕድል ለፖለቲካ ዓላማው ለማንበርከክ በመውገርገር ላይ ይገኛል።

በእኛ እምነት እነዚህ ዙሪያ ገጠም ቀውሶች የጤና፥ የኤኮኖሚ፥ የማኅበራዊ፥ የሞራል፥ ወዘተ... ቀውሶች ብቻ አይደሉም። በዋና ገጽታቸው የፖለቲካ ቀውሶች ናቸው። እንደዚህም በመሆኑ ችግሮቹን ለመቅረፍም ሆነ በዘላቂነት ለማስወገድ የሚቻለው የፖለቲካውን ሁኔታ ቀይሮና ዴሞክራሲና ተጠያቂነት በሰፈኑበት ሁኔታ አማራጭ ፖሊሲዎችን በተግባር ላይ በማዋል ስለሆነ በየመልኩ የቀውሶቹ ሰለባ የሆኑት በሚሊዮን የሚቆጠሩት ወገኖቻችን በአንድነት መንቀሳቀሳቸው ቁልፍ ተግባር ነው እንላለን።
ከዚህም በመነሳት ሕዝባችን ከኢሕአዴግ ምንም በጎና አዎንታዊ ነገር ሊጠብቅ እንደማይችል ተገንዝቦ ከዳር እስከ ዳር በሚከተሉት አማራጮች ዙሪያ በአንድነት እንዲታገል አገራዊና ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

## 1.5.1 <u>ኤች.አይ.ቪ. ኤድስንና የሣንባ ነቀርሣን መዋጋት፤</u>

1.5.1.1 መቅሰፍቱ ከጤና ችግርም አልፎ እጅግ የሰፋ ቀውስ እንደመሆኑ መጠን መከላከልን ማስተማር ያስፈልጋል። ይኸንንም ለማድረግ ኑሯቸው የተናጋ ዜጎችን መንከባከብንና ሌሎች ጠንቆቹንም መቋቋምን የሚያካትት ሁለገብ ብሔራዊ ስትራቴጂ ያስፈልገዋል።
የኢሕአዴግ አገዛዝ እንደ ሌሎቹ ቀውሶች እዚህም ላይ ከተጠያቂነት ለማምለጥ፥ ሁሉንም በካድሬዎቹ ቁጥጥር ሥር ለማዋል፥ ከውጭ የሚገባውን የእርዳታ ገንዘብ በዝርክርክነትና ሙሰኝነት ማባከኑን ለመቀጠል ሲል፥ በአጠቃላይ ኅብረተሰቡን በተለይ ደግሞ ስንት አስተዋጽዖ የሚጠበቅባቸውን ፀረ-ኤች.አይ.ቪ ኤድስ መያዶች ከዚህ አገራዊ ትግል ለማግለል ሲንቀሳቀስ ይታያል። በዚህም መሠረት በቅርቡ ይፋ ባወጣው ፀረ-ኤድስ ስትራቴጂ ቀደም ሲል በአዋጅ እውቅና ተሰጥቶ የነበረውን ብሔራዊ ኤች.አይ.ቪ. መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ቁጥጥር ሥር እንዲወድቅ አድርጎታል። ይኸንን አካሄድ ከመቶ በላይ የሚሆኑ መያዶችን ያቀፈው የኤች.አይ.ቪ. ፎረም <u>"ያለበቂ ጥናትና ምክንያት የተወሰደ ፖሊሲ"</u> በማለት ተቃውሞታል። ስለሆነም ይኸ ፀረ-ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ከባድ ብሔራዊ ችግር በሚጠይቀው ትኩረት መሠረት ሙሉ ነፃነት ያለውና የተጠናከረ ብሔራዊ አካል ማቋቋም አንገብጋቢ ጥያቄ በመሆኑ አንድ <u>"ብሔራዊ ፀረ-ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ኮሚሽን"</u> በአስቸኳይ እንዲመሠረት ማድረግ፤

1.5.1.2 ኮሚሽኑ አግባብ ካለቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፥ ከተለያዩ ሕዝባዊ ድርጅቶች (ሴቶች፥ ወጣቶች፥ ሐኪሞች፥ የማኅበራዊ አገልግሎት ተቋማት፥ ወዘተ....) በሽታውንም ሆነ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጠንቆቹን ለመቋቋም ከተደራጁ መያዶች፥ ከምሁራንና ሌሎች ባለሙያዎች በተውጣጣ መልክ ተዋቅሮ አንድ የአጭርና የረዥም ጊዜ ብሔራዊ ስትራቴጂ እንዲነድፍና የዚህንም ተግባራዊነት እንዲከታተል ማድረግ፤

1.5.1.3 በጥር ወር 1997 ዓ.ም. ይፋ የሆነው የኢሕአዴግ ፀረ-ኤድስ ስትራቴጂ ሦስት ሚሊዮን የሚገመት በተውሳኩ የተለከፈ ሕዝብ ባለበት አገር ዕድሜ ቀጣይ የሆነው ኤአርቲ (ART) በዚህ ዓመት ለአሥራ አምስት ሺህ ሰው፥ እስከ ሦስት ዓመት ድረስ ደግሞ ለሁለት መቶ አሥር ሺህ ዜጎች በነፃ አደርሳለሁ የሚል ቁንጽል ስትራቴጂ ነው። በበሽታው ከተለከፉት ዜጎች መሃል ለተቆነጠረ ክፍል ብቻ የሚለው ይኸ አካሄድ ዜጎች ለዚህ ዕደላ የሚመረጡበትና የሚገለሉበት መሥፈርት ምን እንደሆነ የማያስቀምጥና ለተለመደው ሙሰኝነት በሩን በርግዶ በመክፈት በኅብረተሰቡም ውስጥ ከፍተኛ አለመግባባትን የሚፈጥር አጉል አካሄድ ነው።

በመሆኑም በቅርቡ በናይጀሪያ እንደተደረገው በኢትዮጵያም ባስቸኳይ <u>መድኃኒቱ በአገር ውስጥ ተመርቶ የቻለ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚገዛበትና አቅም የሌለው ደግሞ በነፃ የሚያገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት የግድ ነው፡፡</u>
የስትራቴጂው ሌላው ድክመት በሣንባ ነቀርሣ ሕክምና ጉዳይ በቂ ትኩረት አለመስጠቱ ስለሆነ የሣንባ ነቀርሣን ጉዳይ ከፀረ-ኤች.አይ.ቪ. ኤድሱ ትግል አቆራኝቶ መንቀሳቀስ፤

1.5.1.4 ከዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን ለመዋጋት የሚሰጠው በደርዘን ሚሊዮን የሚቆጠር ብር ዓላማው በዚህ መቅሰፍት ምክንያት የተከሰቱትን ቀውሶች ለመቅረፍም እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ከዚህ ገንዘብና ኅብረተሰቡ ተንቀሳቅሶ ከሚያደርገው እገዛ የተወሰነውን ክፍል ልጆቻቸውን አጥተው በደከመ ጉልበትና የገንዘብ አቅም የልጅ ልጅ ለማሳደግ ለተገደዱ አዛውንት፥ አሥራ ስምንት ዓመት እንኳን ሳይሞላቸው አምስት ስድስት ልጆች ከሚች እናት አባት ለመረከብ ለተገደዱ የቤተሰብ ኃላፊ ለሆኑ ልጆች፥ ከምንምና ከማንም ዕርዳታ ተነፍገው ጎዳና ተዳዳሪ ለሆኑ ልጆችና ለመሳሰሉ ይኸ መቅሰፍት ከፉኛ ለጎዳቸው ወገኖች ችግር ለመቅረፍ እንዲውል ማድረግ፤

1.5.1.5 ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን ለማዳን የሚችል መድኃኒት እስካሁን ባለመገኘቱ ከዚህ መቅሰፍት ጋር የሚካሄደው ጦርነት ዋና ገጽታ መስፋፋቱን ለመከላከል የሚደረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፍልሚያ ነው፡፡ በመሆኑም ከዓለም-አቀፍ ኅብረተሰብም ሆነ ከአገር ውስጥ በሚገኘው የገንዘብ አቅም ለዚህ ዘመቻ የተኩረት ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ይኸ ተግባር በመንግሥት ቢሮክራቶችና ተአማኒነት በሌላቸው የገዥው ፓርቲ ካድሬዎች መካሄዱ ዘመቻውን ከፉኛ አፍዝዞ ውጤት እንዳይሰጥ አድርጎታል፡፡ በመሆኑም በዚህ ዘመቻ የተሻለ የፈጠራ ችሎታና በየአካባቢው የሕዝብ አመኔታ ባላቸው ለዚህም ተግባር አስፈላጊው ስልጠና የሚሰጣቸው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያዶች) ከፍተኛ ሚና እንዲኖራቸው ማገዝ፤

## 1.5.2 <u>የወባ ወረርሽኝን ለመከላከልና ለማስወገድ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ፤</u>

1.5.2.1 ከፍ ብለን በጠቀስነው መሠረት የወባ ወረርሽኝ አሳሳቢ ደረጃ የደረሰውን ያህል በኢሕአዴግ በኩል ተውሳኩን በመከላከልና በማስወገድ ደረጃ የሚደረገው ጥረት የፈዘዘና የደበዘዘ ነው፡፡
እዚህም ላይ ከመንግሥት ይልቅ በኃላፊነት ስሜት በመንቀሳቀስ ላይ ያሉት አገር-በቀልና ዓለም-አቀፍ መያዶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ይኸንን ቀውስ ለመቋቋም ከፍ ብለን ለኤች. አይ. ቪ. ኤድስና ለሣንባ ነቀርሣ ባቀረብነው አሳብ መሠረት አግባብ ያላቸውና በየደረጃው ያሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ መስክ ከተሰማሩ ስብስቦች በመተባበር አንድ <u>አገር-አቀፍ የወባ መከላከያና ማጥፊያ ስትራቴጂ</u> እንዲነደፍ መጣርና በያለበት ፀረ-ወባ ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ማገዝ፤

1.5.2.2 ይኸ ስትራቴጂ እስኪነደፍ ድረስ እስካሁን ጉዳዩን በቅርብ ከሚከታተሉ ወገኖች በተሰነዘሩት አሳቦች ላይ በመመርኮዝ አስፈላጊውን መድኃኒት በሰፊው ገዝቶ በተጠቁ ወይም ጥቃት ሊደርስባቸው ይችላሉ በሚባሉ አካባቢዎች ማከማቸት፥ ይኸንን እውን ለማድረግ አሁን በማዕከላዊ፥ በክልልና በግምሩክ ደረጃ የሚንፀባረቁትን የቢሮክራሲ ማነቆዎች ማንሳት፤

1.5.2.3. እስካሁን ካለው ልምድ ተውሳኩ ውሎ አድሮ ባዳበረው የመከላከል ችሎታ የተነሣ አንዳንድ ቀደም ሲል ውጤታማ የነበሩ መድኃኒቶች ከጥቅም ውጭ እየሆኑ የሚመጡበትና ነፍስ የማያድኑበት ሁኔታ ስለሚከሰት፥ በየደረጃው ያሉ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሙያዎችም ሆኑ ኃላፊዎች ስለ መድኃኒቶቹ ሁነኛነት ወይም ውጤት

አልባነት በፍጥነት መረጃ የሚቀያየሩበት የመገናኛ መረብ መዘርጋት፤

1.5.2.4 የወባ ተውሳክ መስፋፋት ዋና ምክንያት በሕዝቡ ዘንድ ስለ መከላከያ በቂ ግንዛቤ አለመኖር በመሆኑ፥ በአንድ በኩል የሕክምና ባለሙያዎች በቦታው እየተገኙ አገልግሎት የሚሰጡበትና በሌላ በኩል ደግሞ እነዚሁ ባለሙያዎች በየደረሱበት ተውሳኩን ስለ መከላከል ለወጣቶችና ለተማሪዎች የተቀነባበረ ትምሕርትና ስልጠና እንዲሰጡና በነዚህ አማካኝነት ሰፊ <u>ብሔራዊ የግንዛቤ ዘመቻ</u> የሚካሄድበትን መንገድ ማመቻቸት፤

## 1.5.3 <u>ለጎዳና ተዳዳሪ ልጆችና ወጣቶች መድረስ፤</u>

1.5.3.1 የኢሕአዴግ መንግሥት ከከተሞች ሕፃናትንና ጨቅላ ልጆችን እያፈሰ ጫካ ወስዶ በመጣል የሚፈጽመውን አስፀያፊና ኢሰብአዊ ተግባር ማስቆምና ከእንግዲህ ይኽ ግፍ በማንኛውም መልኩ እንዳይደገም ማድረግና "በፀጥታ ምክንያት" በሚል ሰበብ ሥርዓቱ ለጎዳና ወይም ደግሞ ለአስከፊ ድህነት የዳረጋቸውን ወጣቶች መቆሚያ መቀመጫ ለማሳጣት የተደነገገውን <u>"ፀረ-አደገኛ ቦዘኔ" ተብየ ሕግ መሻር፤</u>

1.5.3.2 የኢሕአዴግ መንግሥት ጨርሶ በማይጨነቅለት በዚህ የጎዳና ተዳዳሪዎች ጉዳይ ችግሩን ለመቅረፍ የሚሠሩ ብዙ አገር-በቀልና የውጭ መያዶች፥ እንዲሁም የተለያዩ ዓለም-አቀፍ ተቋማት በመኖራቸው እነዚህና አግባብ ያላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተካተቱበት ሰፊ ጉባዔ ተጠርቶ አንድ አገር-አቀፍ ስትራቴጂ እንዲነደፍና ይኽንንም በኃላፊነት እንዲከታተል ዝቅ ብለን በምንጠቁመው ሚኒስቴር ሥር አንድ ኮሚሽን እንዲቋቋም ማድረግ፤

1.5.3.3 በአስደንጋጭ ሁኔታ በመስፋፋት ላይ ያለውን የልጆች ሴተኛ አዳሪነት ግፉ በሚጠይቀው ቁርጠኝነት ለመዋጋት፥ አንደኛ እነዚህን ልጆች ወደዚህ የገፋቸውን የቤተሰብ መፍረስ፥ ከገጠር የመፍለስ፥ የከፋ ድህነትና አንዳንዴም በእናት አባት መሞት በትከሻቸው ላይ የሚጫነው የቤተሰብ ኃላፊነት የመሳሰሉትን ምክንያቶች መርምሮ፥ እነዚህን ልጆች ከዚህ ተግባር ለማራቅና በሙያም ሆነ በቀለም ትምሕርት እንደዚሁም ደግሞ በሥራ ለመሰማራት ለሚሹና ለሚችሉ የሥራ ዕድል በመፍጠር መልሶ ለማቋቋም የሚያስችል ፖሊሲ አግባብ ካላቸው የመንግሥት ተቋማትና ሌሎች ስብስቦችና ባለሙያዎች መክሮ መንደፍና ማስፈጸም።

1.5.3.4 ይኽ ልጆቻችንን ለወሲብ ባርነት የሚዳርግ አስጸያፊ ተግባር፥ ስግብግብ ፈንጋዮች የሚጠቀሙበት የንግድ ሥራ በመሆኑ በተደራጀ መልክም ሆነ በግለሰብ ደረጃ በዚህ ንግድ የተሰማሩ ወንጀለኞችንም ሆነ የዚህ ግፍ ተጠቃሚ ግለሰቦችን የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን አጠናክሮ በማያወላዳ ሁኔታ መቅጣት፥ እንደዚሁም በጉዳዩ ኅብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ ሰፊ ትምሕርታዊ ዘመቻ ማካሄድ፤

1.5.3.5 ጎዳና ተዳዳሪዎችም ሆኑ ልጆች ሴተኛ አዳሪዎች፥ ኃላፊነት የጎደለው መንግሥት ባወጣ ያውጣችሁ ብሎ ሜዳ የበተናቸው ዜጎች እንጂ ፈልገውና ፈቅደው ከሞቀ ቤት የወጡ ልጆች አይደሉም። ይኽን በመሰለ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ልጆች ዘወር ብሎ ያላያቸውንና የማያያቸውን ኅብረተሰብ ሥርዓቱን፥ እሴቱን፥ ሕጉንና ወጉን እንኳን ሊያከብሩት ቀርቶ ጨርሶ አያውቁትም። ይኽ ክስተት ዛሬ በአጠቃላይ በዓለም ደረጃ የታመነበት በመሆኑ በበለፀጉትም ሆነ በበርካታ የአፍሪቃ አገሮች ሳይቀር ለአቅም ያልደረሱ ዜጎች ወንጀልም ሆነ ጥፋት ሲያደርሱ ጉዳያቸው የሚታይበት "የወጣቶች ፍርድ" (ጁቨናይል ጀስቲስ) የሚካሄድባቸው ልዩ ተቋማትና በየፖሊስ ቢሮው ለዚሁ ጉዳይ ስልጠና የተሰጠው የሰው ኃይል ተመድቦ የሚሠራበት፥ ዞሮ ዞሮ ደግሞ ቅጣት ላይ ሳይሆን

ማስተማርና መልሶ ማቋቋም ላይ ያተኮረ ውሳኔ የሚሰጥበት ሥርዓት ማበጀት። የኢሕአዴግ መንግሥት በጭካኔና በእውርነት አጥፊ ልጆችን እንደ አዋቂ አስሮ፥ እንደ አዋቂ ጥፋታቸውን መርምሮ፥ እንደ አዋቂ "ፍርድ" ሰጥቶ እንደ አዋቂ አዋቂዎች ጋር አደባልቆ የሚያስር በመሆኑ ይኸ ኢሰብአዊ አሠራር ተሸሮ የወጣቶችና የታዳጊዎች ፍትኅ (የጁቨናይል ጀስቲስ) አሠራር የሚጀመርበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

1.5.3.6 ከዚህ አስከፊ ችግር አልፎ በአጠቃላይ የአገራችን ወጣቶች የሚገኙበት አስከፊ ሁኔታ ዋና ምንጭ በአገሪቱ የተስፋፋው ድህነት በመሆኑ፥ ይኸንን ሁኔታ ለማሸነፍ ከፍ ብለን የጠቀስናቸው የመፍትሄ አሳቦች እንዳሉ ሆነው ይኸንን የሕፃናትና የወጣቶች ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶ መፍትሔ ለመሻት በበቂ በጀት፥ የሰው ኃይልና በአጠቃላይም በተቋማዊ ጥንካሬና አቅም የተገነባ ራሱን የቻለ <u>"የሕፃናት የወጣቶችና የቤተሰብ ሚኒስቴር"</u> መሥሪያ ቤት ተቋቁሞ ባፋጣኝ ሥራ እንዲጀምር ማድረግ፤

1.5.3.7 ሚኒስትሩ የቤተሰብና ሕፃናት ጥበቃና እንክብካቤ፥ የወጣቶችን ጥቅምና መብት በሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ ኃላፊነት እንዲሰጠውና በአስቸኳይ ግን የወጣት ሴቶችን ሕይወት በመቅጠፍ ላይ ስላለው ሕገ-ወጥ የፅንስ ማስወረድ ተግባር፥ በአጠቃላይ የወጣቱን የወደፊት ዕድል በማጨለም ላይ ስላሉት እንደ ጫትና ሌሎች አደገኛ ሱስ-አስያዥ ዕፆች (ድረግስ) ቁጥጥር፥ ስለ ጎጂ ባሕሎች መወገድና ስለመሳሰሉት ችግሮች የሕግ ረቂቅ ለፓርላማ አቅርቦ እንዲያስጸድቅና የዚህንም ተግባራዊነት እንዲከታተል ማድረግ።

## 1.5.4 <u>የሴቶችን መብት ለማስከበር የሚደረገውን ትግል ማበረታታትና ማገዝ፤</u>

1.5.4.1 የሴቶችን መብት ጉዳይ በተመለከተ የኢሕአዴግ መንግሥት በየደረጃው ያቋቋማቸው የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤቶችና ጉዳይ ተከታታይ ክፍሎች፥ የፖለቲካ ሥርዓቱን ጥቅም የሚያራምዱና በኢሕአዴግ ካድሬዎች ቁጥጥር ሥር በመሆናቸውና በገጠር ቀበሌዎች የሴት ማኅበራትን የማደራጀት እንቅስቃሴ በትዕዛዝና ከቀበሌ መስተዳድሮች ጋር በጥብቅ በተቆራኘ መንገድ በመሆኑ እነዚህ ተቋማት የሴቶች አመኔታ የላቸውም። በመሆኑም የአገራችን ሴቶች የሚያጋጥሟቸውን ዘርፈ-ብዙ ችግሮች ራሳቸው መክረውና ዘክረው እንዲፈቱ ከሁሉም በፊት በነፃ የመደራጀት መብታቸው እንዲረጋገጥ ማድረግ፤

1.5.4.2 በዚህ መስክ በሚደረገው ጥረት የመንግሥት ድርሻ ሴቶች ያለ አንዳች ተጽዕኖ ራሳቸውን ችለው እንዲንቀሳቀሱ የሚያስችሏቸውን የትምሕርትና የስልጠና፥ የአቅም ግንባታ፥ የሕጋዊ እውቅና እገዛዎችና ማበረታቻዎችን በማቅረብ ብቻ እንዲወሰን ማድረግ፤

1.5.4.3 ሴቶች ራሳቸው በራሳቸው ታግለው ችግሮቻቸውን ለመወጣት የሚያደርጉትን ጥረት ለማገዝና ለማበረታታት በተለያዩ ችግሮች (በምጣኔ ሃብት፥ ቤተሰብ፥ በጎጂ ባሕሎች፥ በወላዶችና በሕፃናት ጤና፥ በልጃገረዶች የትምሕርት ዕድል መስፋፋት፥ ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ፥ ወዘተ.... ) ዙሪያ ከወዲሁ ተደራጅተው በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ የሴቶች መያዶችን ሆነ ለመደራጀት የሚፈልጉ ዜጎችን ከማግለል ይልቅ እንደ ሁነኛ አጋዥ በመቁጠር በፖሊሲ፥ በገንዘብና በአስፈላጊ ቁሳቁስ ሁሉ መርዳትና ማበረታታት፤

1.5.4.4 የሴቶች ጭቆና አንዱ ገጽታና ይኸንን ሁኔታ እንዲቀጥል የሚያግዘው ለሴት ወጣቶች እኩል የትምሕርት ዕድል መነፈጉ የሆነውን ያህል፥ ለዚህ ችግር አስፈላጊውን ትኩረት በመስጠት <u>"ሴቶችን ማስተማር ቤተሰብንና አገርን ማስተማር ነው"</u> በሚባለው መርሆ መሠረት ወላጆች ሴቶች ልጆቻቸውን ያለ ዕድሜ መዳር አቁመው እንዲያስተምሩ፥ በየተማሪ ቤቱ የሴቶችን ጉዳይ የሚከታተሉ መምሕራን እንዲመደቡ፥

በከፍተኛ የትምሕርት ተቋማት የሴቶችን ቁጥር ለመጨመር የሚያስችል ልዩ መመሪያና የግል ትምሕርት ቤቶች የተወሰነ ቦታ ለችግረኛ ሴቶች ልጆች በነፃ የመማር ዕድል እንዲከፍቱ ማድረግ፤

1.5.4.5 በነዚህ መያዶችም ሆነ ባለጉዳይ በሆኑ ሴቶች አማካኝነት በሴት ነክ ችግሮችና ጉዳዮች ላይ ሙሉ በሙሉ ያተኮሩ የማኅበረሰባዊና ኤኮኖሚያዊ እቅዶች እንዲስፋፉ ፖሊሲዎች መንደፍና ተግባራዊነታቸውን ለማረጋገጥ እርምጃዎች መውሰድ፤

1.5.4.6 ችግረኛ ሴቶች በማኅበሮቻቸው አማካኝነት የገቢ ማስገኛ ሥራዎችን እንዲሠሩ ከፍ ብለን ከጠቀስነው የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ባንክ በአነስተኛ ወለድ በግልም ሆነ በቡድን ብድር ሊያገኙ የሚችሉበት አሠራር መዘርጋት።

## 1.5.5 ታዳጊውን ትውልድ የሚንከባከብ የትምሕርት ፖሊሲ መከተል፤

1.5.5.1 የአገራችን ወጣቶች ከተዘፈቁበት ለቀበጸ-ተስፋነት የሚዳርግ የትምሕርት ፖሊሲ የሚላቀቁበት ብሔራዊ መመሪያ ለማውጣት የሚቻለው፥ ከሁሉ በፊት ማንኛውም ፖሊሲ ሲወጣ ዋናዎቹ ባለጉዳዮችና በሙያው አስፈላጊ የሆነው እውቀት ያላቸው ዴሞክራትና አገር ወዳድ ጠበብት (ኤክስፐርቶች) ሲሳተፉበት ብቻ ነው። በመሆኑም ያለንበትን ችግር ለመፍታት የባለሙያዎችን፥ የወላጆችንና በሁለተኛ ደረጃም ሆነ በከፍተኛ ተቋማት ያሉ ወጣቶችን በነፃ የመደራጀት መብት ማወቅና በፖሊሲ ማውጣቱ ጉዳይ እንደዋና ባለጉዳይነታቸው የእነዚህ ወገኖች ተወካዮችና እንደዚሁም የሲቪክ ማኅበራት፥ የሃይማኖት ድርጅቶችና የመሳሰሉት ስብስቦች ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ፤

1.5.5.2 የሚቀየሰው የትምሕርት ፖሊሲ ዓላማው ኢሕአዴግ እንደሚያልመው መፈክር አንጋቢ ትውልድ ለመፍጠር ሳይሆን፥ ሁለንተናዊ ስብዕናው የተሟላ፥ በእኩልነትና በሰው ልጆች መብት መከበር የሚያምን፥ ለኢትዮጵያውያን ወንድማማችነትና እህትማማችነት የሚቆም፥ በራሱ የሚተማመንና በአገሩ ታሪክና ባሕል የሚኮራ፥ በዘመናዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ታንፆና ለ21ኛው ክፍለ-ዘመን ብቁ ሆኖ ራሱንም ወገኑንም አገሩንም ለመጥቀም የሚችል ጤናማ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት የተላበሰ ዜጋ ለመፍጠር መሆኑን ማረጋገጥ፤

1.5.5.3 ይኽ እስኪሆን ድረስ በጣም አደጋ ላይ የወደቀውን የትምሕርት ጥራት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲለወጥ ለመምህራን ስልጠና ተገቢ ትኩረት መስጠት፥ የመምህራን ደመወዝ ካለው የኑሮ ውድነት ጋር እንዲመጣጠን፥ የመምህራንና የተማሪዎች ቁጥር እንዲመጣጠን፥ ለትምሕርት ጥራት አስተዋጽዖ የሚያደርጉ እንደ መጽሐፍት አቅርቦትና የምርምር (የላቦራቶሪ) መሣሪያዎች እንዲሟሉ ማድረግ፤

1.5.5.4 የኢሕአዴግ መንግሥት የአገራችንን ወጣቶች እንደ ቤተ ሙከራ በመቁጠር በውል ባልተጠና ፖሊሲ፥ የአንደኛ ደረጃ ትምሕርትን ከአንደኛ ክፍል እስከ አራተኛ ክፍል ድረስ አንድ አስተማሪ ሁሉንም ትምሕርት ያስተምር የሚለው አህዳዊ የማስተማር ዘዴ አንድ አስተማሪ በሁሉም ትምሕርቶች እኩል እውቀት ይኖረዋል ተብሎ እንደማይጠበቅ፥ ስንፍናና የሥነ-ምግባር ጉድለት ያለው መምህር ያጋጠማቸው ልጆች በጅምላ እንደሚጎዱ፥ አንድ መምህር ቢታመም ትምሕርት ሙሉ በሙሉ የሚቋረጥበት ሁኔታ እንደሚፈጠርና ቀኑን ሙሉ አንድ አስተማሪ የሚለው አሠራር በተማሪዎቹ በኩል የመሰላቸት ስሜት እንደሚፈጥር ጥናቶች ያረጋገጡ ስለሆነ ይኽ አሠራር ተሰርዞ ተማሪዎች በተለያዩ መምህራን የመማር ዕድል እንዲያገኙ ማስቻል፤

ፖሊሲ ማውጣት ፤ ሆኖም በራዲዮም ሆነ በቴሌቪዥን የሚሰጡ "የሩቅ እርቀት" ትምሕርት አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ጉልህ ስለሆነ ወደፊት ሁኔታዎች ተስተካክለው በተለይ መደበኛ ክፍል ውስጥ ትምሕርት መገብየት ለማይችሉ ወገኖች አገልግሎቶቹ እንዲደርሱ የሚደረግበትን በባለሙያዎች ማስጠናት፤

1.5.5.10 መሰናዶ (preparatory) የተባለው አዲሱ የኢሕአዴግ ፖሊሲ የትምሕርት ጥራት ቁልቁል በሄደበት ዘመን፥ ይባስ ብሎ የሦስት ዓመታት ትምሕርትን በሁለት ዓመታት እንዲሰጥ ስለሚያደርግ፥ ተማሪዎችን በብቃት ለዩኒቨርስቲ እያዘጋጀ ባለመሆኑና ፖሊሲው የአገሪቱን ሀብት ከማባከን አልፎ የአንድ ትውልድ ሕይወት እያበላሸ በመሆኑ በአፋጣኝ እንዲቋረጥ ማድረግ፤

1.5.5.11 የከፍተኛ ትምሕርት ተቋማት በስም ብቻ ሳይሆን በተግባር ከፍተኛ እውቀት የሚገበይባቸው፥ አገሪቱ ላሉባት ችግሮች ተገቢ መፍትሄዎችን የሚጠቁሙ ጥናትና ምርምር የሚካሄዱባቸው ማዕከላት ሊሆኑ የሚችሉት አካዳሚክ ነፃነት ሲረጋገጥና ዩኒቨርስቲዎች የራሳቸው ነፃ የውስጥ አስተዳደር ሲኖራቸው ስለሆነ በቻርተር እንዲተዳደሩ ማድረግ፤

1.5.5.12 አሁን በመከሰት ላይ ያለውን አስደንጋጭ የቁልቁለት ጉዞ ለመቀልበስና ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች ደረጃቸውን የጠበቁ የጥራት ማዕከላት እንዲሆኑ የመምህራንና የተማሪዎች ቁጥር እንዲመጣጠን፥ የመምህራን እጥረት ለመቋቋም አንድ ኢትዮጵያዊ መምህር ከሚከፈለው አምስት እጥፍ እየከፈሉ ባዕዳንን ከመቅጠር ይልቅ የዜጎችን ደመወዝ ከፍ በማድረግ የምሁራንን ፍልሰት መቀልበስ፥ እንደዚሁም ተማሪዎች በተረጋጋና በተመቻቸ ሁኔታ ትምሕርታቸው ላይ እንዲያተኩሩ ለማስቻል የማስተማሪያ መሣሪያዎች በበቂ እንዲቀርቡ፥ የመማሪያና የተማሪዎች የመኖሪያ ሕንፃዎች እንዲገነቡ ማድረግ፤

1.5.5.13 የአራት ዓመት ትምሕርትን በሦስት ዓመት፥ የአምስት ዓመት ትምሕርትን በአራት ዓመት ማድረግ፥ በትምህርት ጥራት ላይ በገሀድ የሚታይ ችግር እየፈጠረ ስለሚገኝና የምሩቃኑን የውጭ የከፍተኛ ትምሕርት ዕድል ስለሚያበላሽ በአስቸኳይ ዓለም-አቀፍ መመዘኛዎችን ወደሚያሟላው የአራትና የአምስት ዓመት ፕሮግራም መመለስ፤

1.5.5.14 በደርግ ዘመን በተደረገው መሃይምነትን የማጥፋት ዘመቻ ምክንያት የመሻሻል ሁኔታ አሳይቶ የነበረው የጎልማሶችና የአዋቂዎች መሃይምነትን የማስወገድ ጥረት ከ1990 ዓ/ም (እ.አ.አ.) ጀምሮ አቅጣጫው ተቀልብሶ በአሁኑ ጊዜ የመሃይሙ ቁጥር ጨምሮ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በ2002 ዓ/ም (እ.አ.አ.) ከ15 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ ያሉ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ጎልማሶችና አዋቂዎች ቁጥር የሴቶች 34 በመቶ (34%) የወንዶች 49 በመቶ (49%) ሆኗል፡፡ ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪቃ አገሮች ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ዜጎች ቁጥር በአማካይ የሴቶች 55 በመቶ፥ የወንዶች 75 በመቶ ሲሆን ይኸም አገራችን ኢትዮጵያን ማንበብና መፃፍ በሚችሉ ሰዎች ቁጥር አነስተኛ ደረጃ ላይ እንድትገኝ አድርጓታል፡፡ ይኸንን የተሳሳተ አቅጣጫ በአፋጣኝ ለመቀየርና ከአገሪቱ ሁኔታ ጋር የተጣጣመና የሕዝቡን የእውቀት ጥሜት ለማርካት እንዲቻል ከትምሕርት፥ ከጤና፥ ከእርሻ (ግብርና) እና ከሥራ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የተውጣጡ አባላትን የጨመረና በትምሕርት ሚኒቴር ግንባር ቀደም አስተባባስሪነት የሚመራ አንድ የጎልማሶችና አዋቂዎች ትምሕርት ይዘትና ጥራት የሚያጠና ኮሚሽን ማቋቋም፤ በዚህ ረገድ በማእከል የሚወጣውን አጠቃላይ መመሪያ እያንዳንዱ አካባቢ እንደየአካቢው ሁኔታና አስፈላጊነት በተግባር ላይ ያውላል፡፡ በዚህ የጎልማሶችና የአዋቂዎች ትምሕርት ላይ የሚሰማሩ መምህራንን ማሰልጠንና ማዘጋጀት የእቅዱ አንዱ ዋና ዘርፍ ይሆናል፡፡

1.5.5.15 የአገሪቱ ኢኮኖሚ በቂ ሥራ መፍጠር ባልቻለበት ሁኔታ ወጭ መጋራት

(cost sharing) የተባለው አሠራር በተማሪው ላይ ብዙ ጫና ስለሚያመጣ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ እስኪቀየር ድረስ እንዲሰረዝ ማድረግ፤

1.5.5.16 በአገሪቱ የሚሠራበትን የከፍተኛ ትምሕርት የመግቢያ መስፈርት ሳያሟሉ ገዥውን ፓርቲ ለማገልገል ለዚሁ ፓርቲ ቅርበት ላላቸው ዜጎች የተቋቋሙ እንደ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ዓይነት ተቋማት በአንድ በኩል ደረጃቸውን እንዲጠብቁና በሌላ በኩል ደግሞ መስፈርት ለሚያሟሉ ዜጎች በሙሉ ያለ አድልዖ ክፍት እንዲሆኑ ማድረግ፤ እንዲሁም ከፓርቲ ፖለቲካ ገለልተኛ በሆነ መልክ ብቃትና ጥራት ያላቸው ሙያተኛ (ፕሮፌሽናልስ) የሕዝብ አገልጋዮችን ማሰልጠን፤

## III. ክፍል ሁለት ፡

## 2. ወደ ዴሞክራሲያዊና የተረጋጋ ኅብረተሰብ የሽግግር ሂደታችን፤

እንደ ርሀብና ድህነት በሰላምና በዴሞክራሲም ጉዳይ ኢትዮጵያ ለክፍለ-ዘመናት የጭቆና የግጭትና ያለመረጋጋት አዙሪት ውስጥ ያለች አገር ነች፡፡ ኅብረተሰባችን አንዳንዴ በገዥዎች የጥቅም ግጭት፥ ሌላ ጊዜ በብሔር/ብሔሮችና በጠቅላላው ሕዝብ ለመብቱና ወግ ላለው ኑሮ በሚያደርገው ተጋድሎ፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ የውጭ ወራሪዎችን ጥቃት ለመመከት በተካሄዱና ባልተቋረጡ የጦር ግጭቶች ሰላም ተነፍጎ፥ ዴሞክራሲያዊ ባሕልን አዳብሮ በተረጋጋ ሁኔታ የዕድገትና የብልጽግና ጎዳና እንዳይይዝ ፋታ ተነስቶ ሲዋከብ ለዘመናት የኖረ፥ ጊዜና ታሪክ ተጋግዘው የጎዱት ኅብረተሰብ ነው፡፡
በዚህ የወከባና የፍዳ ታሪክ በተለይ ለፖለቲካ ሥልጣን በተደጋጋሚ የተደረጉ ግጭቶች ሳቢያ፥ ላለፉት ሦስት ክፍለ-ዘመናት የአሥር ዓመታት እድሜ በተከታታይ ሰላም ያላገኘው ሕዝባችን ያሳለፋቸውም የሰላም ወቅቶች ቢኖሩ፥ ተቀናቃኞቻቸውን በጦር ሜዳ አሸንፈው ሥልጣን የያዙ ኃይሎች ኅብረተሰቡን በሙሉ ያሸነፉ እየመሰላቸው፥ እነሱም በተራው ወደ ታሪክ ትቢያነት እስኪወርዱ ድረስ ኅብረተሰባችን ያገኘው ሰላም ሁልጊዜ አሸናፊዎች በተሸናፊዎች ላይ የጫኑት እርቀ-አልባ ሰላም እንጂ በድርድርና በመግባባት ለሁሉም የሚሆን የእፎይታ ዘመን የሰፈነበት ወቅት በታሪካችን የለም፡፡

ይኸ ያልተቋረጠ የሁከት ሂደት ያስከተለው ዛሬ ሁላችንም የምንቆጭበትን የኢኮኖሚና የሶሻል ድቀትና ውርደት ብቻ አይደለም፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በተለይ በፖለቲካው መስክ አመጽን እንደ መደበኛና ልዩነትን ለመፍታት እንደ መጀመሪያ አማራጭ አርጎ የሚያይ አስከፊ ባሕል በኅብረተሰባችን እንዲገን አድርጎታል፡፡ ኅብረተሰቡ ውስጥ ለሚከሰቱ የፖለቲካ ልዩነቶች ሁሉ ሌላ አማራጭ መፍትሔ ለማቅረብ አስፈላጊውን ጥረት ሳያደርጉ አመጽን ብቻ መጋበዝ፥ ተቃዋሚን እንደ ደመኛ ጠላት መፈረጅ፥ በአመለካከቱ ትንሽ ለየት ያለን እንደለየለት ተቃዋሚ መመልከት፥ ልዩነት ማስማትን ከጦር ክተት አዋጅ ለይቶ የማየት ችግር፥ ወዘተ... እነዚህ ሁሉ የዚህ አስከፊ ቅርስ ነፀብራቆች ናቸው፡፡

እኛ የኢትዮጵያ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ይኸንን አስከፊ ቅርስ ለማስወገድ አስፈላጊ የሆነውን የባሕልና የዕይታ አብዮት በራሳችን ላይ አድርገን፥ ሰላም ስንል በትጥቅ ድል የተገኘ የአሸናፊዎች ሰላም ሳይሆን፥ ኅብረተሰባችን በሙሉ በአሸናፊነት የሚወጣበት በድርድር፥ በመግባባትና በውይይት እርቀ-ሰላም የሚሆንበት ሁኔታ እንዲፈጠር እንታገላለን፡፡ ይኸንንም በትጥቅ ትግል ሳይሆን በሰላማዊ ሕዝባዊ የትግል ሂደት በማምጣት፥ ለዘመናት አገራችን ያለችበትን አዙሪት ለመስበር ቆርጠን ብንነሣም፥ ይኸን ዓይነት በጎ አብዮት ካላካሄዱ ኋላ ቀር ኃይሎች ጋር ከባድና ውስብስብ ትግል

እንደሚጠብቀን አናጣውም::

በተለይ ደግሞ ዛሬ ይኽንን አዙሪት የመስበሩን ሂደት ለመቀስቀስ፥ ለማገዝና ለማስተባበር ብዙ የሚጠበቅበትና ኃላፊነት መውሰድ ይገባው የነበረው መንግሥት፥ በዚያው ባረጀ ባፈጀው ዘዴ በአመጽ ሥልጣን የተቆጣጠረ፥ በዚያው ኅብረተሰባችንን የደም ዕንባ ባስለቀሰ የአሸናፊዎች ሰላም አፍኖ የያዘ፥ በአመጽ የተጨበጠን ሥልጣን ለመጠበቅ ደግሞ አስፈላጊ በሆነ ቁጥር በአመጽና በዚያው የሕዝባችንን ጀርባ በላጠ የአፈናና የግድያ ሥልት የሚጠቀም፥ ባጭሩ ለዚህ አስከፊ አዙሪት ሾተል አቀባይ እንጂ ለታሪክም ሆነ ለመጭው ትውልድ ዕጣ ፈንታ የማይጨነቅ አገዛዝ ሥር በመውደቃችን ይኽንን አገራዊ ራእይ እውን ለማድረግ የምናደርገውን ትግል የባሰ ውስብስብ አድርጎታል::

ሕዝባችን ይኽንን አጥፊ ባሕል አሸንፎ ወደተረጋጋ ኅብረተሰብ እንዳይሸጋገርና ጥረቱን ሁሉ የረሀብና የድህነትን ሰንሰለት ሰብሮ፥ የበለፀገ ኑሮ ለመኖርና የገዛ ዕጣ ፈንታውን ለመወሰን እንዳይችል፥ በዴሞክራሲ መጥፋት እግር ከወርች የታሰረ ሕዝብ ነው:: ጥረታችን ሁሉ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት አስፍነን በዚህ ክልልና መሣሪያነት ወደተረጋጋ ኅብረተሰብ ለመሸጋገር መሆን ይገባዋል::
ይኽንን አገራዊ ዓላማ እውን ለማድረግ ኅብረታችን በአንድ በኩል ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሽግግር ስለምናደርገው ሕዝባዊና ሰላማዊ ሂደት፥ በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ በተጓዳኝ በብሔራዊ እርቅ፥ በመቻቻልና በወንድማማችነት መንፈስ አገራችንን መልሶ ለመገንባት ስለሚጠብቁን ተግባራት የሚከተለውን አማራጭ ያቀርባል::

## 2.1 የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ተግባራት፤

### 2.1.1 ወደ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት፤

ዛሬ በአገራችን የተተከለው ሕገ-መንግሥት በአንድ አናሣ ኃይል ተረቆ፥ ሰባት ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎችን በቋንቋና በፖለቲካ መነሾ የመምረጥ መመረጥ መብት ነፍጎ፥ የነፃ ምርጫ መሥፈርቶችን ረግጦ በተካሄደ ሂደት በተሰየመ ወገናዊ አካል የፀደቀና የዚህን አናሣ ኃይል የፖለቲካና ኢኮኖሚ ፕሮግራም እንዲሁም የርዕዮተ-ዓለም ምርጫ የአገሪቱ የበላይ ሕግ አድርጎ የደነገገ፥ ኅብረተሰቡ የኔ የማይለው ወገናዊ ሰነድ ነው::

በዚህም የተነሣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የማንኛውም ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት የማዕዘን ድንጋይ የሆነውን የሥልጣን ክፍፍል መርኅ በመፃረር፥ የመንግሥት ሥልጣን አንድ ወጥነት በሚል ፅንሰ-ሃሳብ (ቴዎሪ) አገሪቱን ለአንድ ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን አካል ብሎም ለአንድ ገዥ ፓርቲ ለዳረገ፥ የዳኝነት ነፃነትን መርኅ ባለመቀበል፥ ይኽንኑ ገዥ ፓርቲ እዛው በዛው ዳኛም ቀማኛም እንዲሆን ለፈቀደ፥ የሕግ የበላይነትን መሠረታዊ ዋስትና አግልሎና ነፃና ገለልተኛ የሆነ የሕገ-መንግሥት ቁጥጥርን ተቃውሞ፥ የዚህኑ ገዥ ፓርቲ መሪዎች ከሕግ በላይ ላስቀመጠ፥ በዚህ መልክ በአንድ አናሣ ኃይል ተተክሎ በብዙኃኑ ፈቃድ እንዳይሻር ወይም እንዳይሻሻል ሆኖ ለተቆላለፈ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ሰነድ ተዳርጓል:: በመሆኑም ይኽንን ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ቀይሮ ከአንድ ፓርቲ ሕገ-መንግሥት ወደ መድብለ ፓርቲ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት መሸጋገር ስለሚያስፈልግ በዚህ ጉዳይ ኅብረቱ በሚከተለው መልክ ይንቀሳቀሳል፤

#### 2.1.1.1 የዴሞክራሲያዊው ሕገ-መንግሥት መሠረታዊ ይዘቶች፤

2.1.1.1.1 በአፍሪቃም ሆነ በዓለም-አቀፍ ደረጃ በሰብአዊ፥ በፖለቲካና በማኅበራዊ መብቶች ጉዳይ የተደነገጉትንና ኢትዮጵያም የፈረመቻቸውን ስምምነቶች ሙሉ በሙሉ የተቀበለና ለመከበራቸውም ሙሉ ዋስትና የሚሰጥ፤

2.1.1.1.2 ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን የሚለው ፅንሰ-ሀሳብ ተሽሮ፥ ሥልጣን ለሕገ-መንግሥቱ ታዛዥ ሆኖ ሕግ ለሚያወጣ ሕግ አውጭ አካል፥ ለዚህ ሕግ ታዛዥ ሆኖ ለሚሠራ ሥራ አስፈጻሚ የመንግሥት ዘርፍና ለዚህ ሕግ ታዛዥ ሆኖ ሕግ ለሚተረጉም ነፃ የዳኝነት ዘርፍ ተደልድሎና ተከፋፍሎ የሚሰጥበት፤

2.1.1.1.3 የተለያዩ የመንግሥት ዘርፎች የሚወስዷቸው ውሳኔዎችም ሆኑ ርምጃዎች፥ ለሁሉም የበላይ የሆነውን ሕገ-መንግሥት መጣስ አለመጣሱን የሚቆጣጠር ከሦስቱም ዘርፎች ቁጥጥር ውጭ ለሥልጣኑም፥ ለኀልውናውም በሕገ-መንግሥቱ የተደነገገ የሕገ-መንግሥት ቁጥጥር (ጁዲሻል ሪቪው) የተረጋገጠበት፤

2.1.1.1.4 የኢትዮጵያውያን በመላ የጋራ እንጂ የአንድን ድርጅት የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚና የርዕዮተ-ዓለም ምርጫዎችን የሚያንግሥ ሰነድ መሆን ስለሌለበት ከኢሕአዴግም ሆነ ከሌላ ማንም የፖለቲካ ድርጅት ወገናዊ ፕሮግራሞች ይዘት የፀዳ፤

2.1.1.1.5 ሰፊ የኅብረተሰብ ድጋፍና ስምምነት ላይ የተገነባ የጋራ ሰነድ ቢሆንም አንዳንድ አንቀጾች በኅብረተሰቡ ውስጥ ከሚከሰቱ ለውጦች ጋር አብረው መራመድ ያስፈልጋቸዋል። በመሆኑም የማሻሻሉ ሂደት የተቀላጠፈ ሆኖ ሕገ-መንግሥቱ የለውጥም ሆነ የዴሞክራሲ ፀር እንዳይሆን የውሳኔ-ሕዝብ (የሬፈረንደም) አማራጭንም የሚያረጋግጥ ሥርዓት የሚያፀድቅ ሕገ-መንግሥት እንዲሆን ይደረጋል።

2.1.1.2 <u>ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥትን እውን ለማድረግ የምንከተለው ሂደት፥</u>

2.1.1.2.1 የኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥት ፀረ-ዴሞክራሲያዊነት ለሕዝባችን ሰላም፥ ለአገራችን አንድነት፥ ለምንመኘውና የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሚሻው የተረጋጋ የልማትና የብልጽግና ሂደት ምን ያህል አደገኛ እንደሆነ፥ ዛሬ የዚህ ሕገ-መንግሥት የፍልስፍና መሠረት በዓለም ታልፎ የሄደና እፍኝ በማይሞሉ አገሮች ብቻ የሚሠራበት እንደሆነ፥ ሰፊ የማብራራትና በዲፕሎማሲው መስክ የማጋለጥ ዘመቻና ከዚህ ሁሉ አንፃር እኛ ያለን ዴሞክራሲያዊ ራእይ እንዴትና ለምን እንደሚሻል የሚያሳይ ትምሕርታዊ ቅስቀሳ ይካሄዳል፤

2.1.1.2.2 ለአገራችን የሚያስፈልጋት ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት በኅብረተሰባችን ውስጥ ያሉ የተሰበጣጠሩ የፖለቲካና የርዕዮተ-ዓለም ኃይሎች፥ የጥቅም፥ የሙያ፥ የባሕልና ሌሎች ስብስቦች በአንድ ብሔራዊ የውይይትና የድርድር መድረክ አማካኝነት ተወያይተውና ተደራድረው ሰፊ ስምምነት ላይ የሚደረስበት ሰነድ መሆን ስለሚገባው በጉዳዩ እነዚህ ሁሉ ኃይሎች በሕዝብ ፊት የሚወያዩበት ብሔራዊ የውይይት መድረክ ማዘጋጀት፤

2.1.1.2.3 ከፍ ብለን የጠቀስናቸውን ዴሞክራሲያዊ መርኆዎችና የዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት መስፈርቶችን እንዲሁም በዓለም ደረጃ የፀኑና ኢትዮጵያም የፈረመቻቸውን የሰብአዊ፥ የፖለቲካና ማኅበራዊ መብቶችን አስመልክቶ ለሚደረገው ትምሕርታዊ ዘመቻ አግባብ ለአላቸው የሥነ-ዜግነት ትምሕርትና የሰብዓዊ መብቶች ተሚጋች መያዶች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ የፋይናንስ፥ የማቴሪያልና የሞራል ድጋፍ መስጠት፤

2.1.1.2.4 ከዚህ ዘመቻ በተጓዳኝ ሕገ-መንግሥቱ ስለሚሻሻልበት ሁኔታ የዚህኑ

ሰነድ አንቀጽ 54/4፥ አንቀጽ 103ና 104፥ አንቀጽ 60/1 እና አንቀጽ 60/3ን ሕጋዊ፥ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ ሂደት በማቀናጀት በሚከተለው መልክ መንቀሳቀስ፡-

2.1.1.2.4.1 የኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 103ና 104 በሕገ-መንግሥት መሻሻል ጉዳይ ወይ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይ የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ወይ ደግሞ ከክልል ምክር ቤቶች ሢሶው የማሻሻያ ሀሳብ ካቀረቡ ሕዝቡ በዚህ ጥያቄ የመወያየት መብት እንዳለው ይደነግጋሉ፤

ምንም እንኳን አንቀጽ 103 ውይይቱ የሚቻለው የተጠቀሱት አካላት የማሻሻያ ሀሳብ ሲያቀርቡ ነው ቢልም፥ ዕጣ ፈንታውን በሚመለከት መሠረታዊ ጉዳይ፥ ሕዝባችን ሉዓላዊነቴን ተጠቅሜ ልወያይ ካለ ማንም ቢሆን ይኽንን መብት ሊነፍገው አይችልም። ከዚህ በተጨማሪ አንቀጽ 104 በሕዝቡ የመወያየት መብት ላይ ይኽንን እንቅፋት ቢጋርጥም፥ ይኸው ሕገ-መንግሥት በአንቀጽ 54/4 የፓርላማው አባላት "ተገዥነታቸው ለሕገ-መንግሥቱ፥ <u>ለሕዝቡ ፈቃድና</u> ለሕሊናቸው ብቻ ይሆናል" ስለሚል ሕዝቡ በዚህ አንቀጽ ተጠቅሞ በመወያየትና በዚህ ጉዳይ ያለውን "ፈቃድ" ለመግለጽ የሚከለክለው ምንም ሕገ-መንግሥታዊም ሆነ የፖለቲካ እንቅፋት ሊኖር አይችልም።

2.1.1.2.4.2 በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ፈቃዱን ለተመራጮቹ ለመግለጽ ባለው መብት ተጠቅሞ ሕገ-መንግሥቱ እንዳለ እንዲቀጥል ወይም ደግሞ ከፍ ብለን በዘረዘርነው መልክ እንዲሻሻል ይፈልግ እንደሆነ ተወያይቶ ይኽንን ውይይት ለመቋጠርና አሳቡን ለመግለጽ የሚያስችለው ሕዝበ-ውሳኔ (ሬፌረንደም) ይካሄዳል፤

2.1.1.2.5 የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ሬፌራንደም አማካኝነት በምንም በማያሻማና በማያወላዳ ሁኔታ የኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥት ከፍ ብለው የተጠቀሱትን ዴሞክራሲያዊ እሴቶች በሚያካትት መንገድ እንዲቀየር ከወሰነ፥ በአገሪቱ ያሉ የፖለቲካ ኃይሎች፥ የሲቪክ ማኅበረሰቡ አባላት፥ የሙያ ድርጅቶች፥ የሴቶች፥ የወጣቶችና ሌሎችም ሕዝባዊ ማኅበራትና ምሁራን መላውን ሕዝብ ባካተተ መልክ ከነዚህ ሁሉም ከሚስማማባቸው ዴሞክራሲያዊ እሴቶች በተጨማሪ፥ ሕገ-መንግሥቱ ማካተት ስለሚኖርበት ሌሎች ጉዳዮች አሀዳዊ ወይስ ፌዴራል ሥርዓት? ፌዴራል ሥርዓት ከተባለ ምን ዓይነት አወቃቀር? ፕሬዚዳንታዊ፥ ፓርላሜንታዊ ወይስ ሌላ ሥርዓት? ወዘተ... በሚሉት ዝርዝር ጥያቄዎች ሁለተኛ ዙር ብሔራዊ ውይይት ይካሄዳል፤

2.1.1.2.6 ከዚህ ሰፊ ብሔራዊ ውይይት በኋላ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 60/1 በሚፈቅደው መሠረት አዲስ ምርጫ ለማካሄድ ምክር ቤቱ ይበተናል። ከዚያም ከሥልጣን ዘመኑ ማብቃት በፊት ምክር ቤቱ ከተበተነ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ አዲስ ምርጫ እንዲደረግ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 60/3 በተደነገገው መሠረት የተለያዩ አስተሳሰቦች ያላቸው ኃይሎች በሙሉ እንደ ዕምነታቸውና አቋማቸው ለሕዝብ ምርጫ ቀርበው ሕዝቡ እንደሚሰጣቸው ክብደት እየታየ የሚወከሉበት ከመደበኛው ሕግ ማውጣት ተግባር በተጨማሪ በሕዝቡ ፈቃድ መሠረት ሕገ-መንግሥቱን የማሻሻል ተልዕኮ ያለው ምክር ቤት ይሰየማል፤

2.1.1.2.7 ይኽ ምክር ቤት የሚስማማበት ረቂቅ ለሕዝበ-ውሳኔ ቀርቦ ከፀደቀ በኋላ በዚህ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት መሠረት መድብለ-ፓርቲ ምርጫ ይካሄዳል።

### 2.1.2 <u>በኅብረተሰባችን ዘንድ ዴሞክራሲን ማስፈንና ሕዝባዊ ተሳትፎን ማኅልበት፤</u>

ዴሞክራሲያዊና የተረጋጋ ኅብረተሰብ ብለን ስንነሣ፥ ይኽንን እውን ለማድረግ በመላ

ዓለም የፀኑትን የሰብአዊ መብቶችን፥ የመደራጀት፥ የፕሬስ፥ የአሳብ፥ የሃይማኖት፥ የመማር፥ ጤናን የመንከባከብ፥ ሠርቶ የማደር፥ የፆታ አድልኦን የማስወገድና የመሳሰሉትን እሴቶች ያለአንዳች ፖለቲካዊና ወገናዊ አጀንዳና ገደብ የማረጋገጥ ሂደት እንከተላለን ማለት ነው፡፡

**መድረኩ ከተመቻቸለት ኅብረተሰባችን ከአብራኩ በሚፈልቁና ራሱ በሚቆጣጠራቸው ተቋማት አማካኝነት ከዳር እስከዳር ተንቀሳቅሶ ራሱን በራሱ ወደ ተሟላ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማሸጋገር ብቃት እንዳለው አንጠራጠርም፡፡ እነዚህን ሁሉ እሴቶች እውን ለማድረግ ዴሞክራሲያዊ የሆነ መንግሥት ያለአንዳች ወገናዊነት ለሁሉም ሕጋዊና አስተዳደራዊ መንገዶችንና ሁኔታዎችን በማመቻቸት፥ ያለአንዳች ወገናዊነት ዴሞክራሲን ለማስፈን ለሚጥሩ ኃይሎች ሁሉ እገዛ በማድረግ ቁልፍ ሚና ሊጫወት እንደሚችል እናምናለን፡፡**

የኢሕአዴግ መንግሥት በርካታ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በልፈፋ ደረጃ አወቅሁ ቢልም፥ በተጨባጭ ነፃ ፕሬስ ብሎ ፕሬሱን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሲያፍን፥ የመደራጀት መብት ብሎ ከሱ ቁጥጥር ውጭ ኅብረተሰባችን እንዳይደራጅ ሲከላከልና “ሕዝባዊ” የሚላቸውን ድርጅቶች በካድሬዎቹ መዳፍ ለመክተት ሲሠራ እንደቆየ ሁላችንም የምናውቀው ነው፡፡ ከዚህ በመነሣት በኅብረተሰባችን ዴሞክራሲ ለማስፈንና ለማንኛውም የወደፊት እርምጃ ወሳኝ የሆነውን ነፃ የሕዝብ ተሳትፎ ለማጎልበት ኢ.ዴ.ኃ.ኅ የሚከተሉትን የማበረታቻ እርምጃዎች ይወስዳል፡፡

2.1.2.1 ዜጎች በሙያ፥ በጥቅም፥ በሕዝብና በወገን ተቆርቋሪነትና በሌሎች ምክንያቶች አነሳሽነት ተደራጅተው ለምንቀሳቀስ የሚያደርጉትን ጥረት በጥርጣሬ ዓይን ሳያይ ወይም ለወገናዊ ዓላማ ሲል ለመቆጣጠር ሳይሞክር ለሁሉም በነፃ የመደራጀት መብትን የሚያረጋግጥ ሕግ ማውጣት፤

2.1.2.2 ይኸንን መሠረታዊ መብት ለማረጋገጥ በአሁኑ ወቅት በኢሕአዴግ ፍርድ ሚኒስቴር አቅራቢነት በመያዶች ላይ ሊጫን የታሰበውን “የአገር ፀጥታ”፥ “የሕዝብ ጥቅም”፥ “የአገር አንድነት”፥ ወዘተ... በሚሉ አሻሚና እንደልብ ሊተረጎሙ በሚችሉ ሐረጎች የመደራጀት መብትን የሚነፍግ፥ ለመንግሥት ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ አንድን ድርጅት ለማገድ ወይም የባንክ ሂሳቡን ለመዝጋት የሚያስችል መብት የሚሰጥ፥ መንግሥት የመያዶችን ቢሮ ባሻውና በፈለገው ጊዜ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲበረበርና ሰነዶችንና ተዛማች ንብረቶችን እንዲወርስ የሚፈቅዱ አንቀጾች ያካተተውን ረቂቅ አስወግዶ የመያዶች ተወካዮችን ጉዳዩን አስመልክተው ባለፈው ዓመት ባቀረቡት አማራጭ ሰነድ ላይ በተመረኮዘ ውይይት የመደራጀት መብትን የሚያጎብት ሕግ እንዲወጣ ማድረግ፤

2.1.2.3 የፕሬስን ነፃነት በተመለከተ እንደዚሁ በመንግሥት ተረቅቆ የቀረበው በአገርም ሆነ በዓለም-አቀፍ ደረጃ በባለሙያዎችና በሰብአዊ መብቶች ተቆርቋሪ ኃይሎች ከፍተኛ ውግዘት ያጋጠመው የፕሬስ ሕግ ረቂቅ ታግዶ በጉዳዩ ዓለም-አቀፍ መስፈርቶችን የሚያሟላና ከሁሉም በላይ ደግሞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጉዳዩ የሚያገባቸውን ባለሙያዎች ባሳተፈ ሁኔታ በሚረቅ ዴሞክራሲያዊ የፕሬስ ሕግ እንዲተካ ማድረግ፤

2.1.2.4 መገናኛ ብዙኃን በተለይ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ሲሆኑ ለዚያ መንግሥት ዓላማ ማራማጃ ሲባል አድልዖአዊ እንዳይሆንኑና ለመላው ኅብረተሰብ በማገልገል የዴሞክራሲውን ሂደት እንዲያጎለብቱ፥ እንደዚሁም ደግሞ አገሪቱ ካለችበት ችግር እንድትወጣ ለሚያስፈልጉት ውይይቶችም ሆኑ ትምሕርታዊ ዝግጅቶች ክፍት ሆነው የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲጫወቱ ከማንኛውም መንግሥትም ሆነ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ኃይል ነፃ የሚሆኑበትን ዘዴ የሚቀይስና ተግባራዊነቱን የሚከታተል አንድ ገለልተኛ “የመገናኛ ብዙኃን ከፍተኛ ጉባዔ” ማቋቋም፤

2.1.2.5 ከፍ ብለን አገራችንን ካለችበት የቀውስ አዙሪት ለማውጣት በሚል ያቀረብናቸው የፖሊሲ ለውጦች በሙሉ ዋና ባለጉዳይ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ ፖሊሲዎቹ በቀጥታ የሚመለከቷቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች በየዘርፉና በየደረጃው ተደራጅተው የሚሳተፉበት መድረክ ካልተበጃጀ ማንኛቸውም በተግባር ለመተርጎማቸው ምንም ዋስትና አይኖርም። ከዚህ በመነሣት የገበሬውን ችግር ለመቅረፍ ከካድሬዎች ቁጥጥር ውጭ ገበሬው በየደረጃው በነፃ እንዲደራጅ፥ ሴቶችን ካሉበት ቀውስ ለማውጣት ለዚህ ዓላማ ራሳቸው ተደራጅተው እንዲታገሉ ማገዝ፥ የትምሕርት ፖሊሲ ሲቀየስ መምህራን፥ ወጣቱና ወላጆች ተደራጅተው በፖሊሲ ውሳኔና በፖሊሲ አፈጻጸም ጫና እንዲኖራቸው ማስቻል፤ ለወጣቱም ሆነ ለሌላው ሥራ አጥ ሥራ ስንል ወጣቱና ሥራ-አጦች በጥረቱ ውስጥ ተደራጅተው እንዲገቡበት ማድረግ ያስፈልጋል። በመሆኑም ከፍ ብለን የፖሊሲ ለውጥ አሳቦች ላይ የመሰላቸውን የእርማት ማስተካከያዎች ለማቅረብም ሆነ አብረው የነደፏቸውን ፖሊሲዎች ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ለሚጠበቅባቸው የነዚህ ኅብረተሰብ ክፍሎች ድርጅቶችና እንደዚሁም በነዚህ መስኮች አገርንና ወገንን ለማገዝ በመያድ መልክ ለተደራጁ ለምሁራን፥ ለአካባቢ እንክብካቤ ተቆርቋሪ፥ ለሲቪክ ትምሕርት፥ ለሰብአዊ መብቶችና ለመሳሰሉ አገራዊ አጀንዳዎች በመቆርቆር ለተደራጁ ዜጎች በመንግሥት በኩል አስፈላጊውን የማቴሪያል፥ የፋይናንስና የሞራል እገዛ ማድረግ።

## 2.2. በብሔራዊ እርቅ ወደ ተረጋጋ ኅብረተሰብ፤

አገራችን ለክፍለ-ዘመናት ሲፈታተናት በቆየው የአመጽና የትርምስ ባሕል ከፈሰሰው ደምና ዕንባ በተጨማሪ፥ ባለፉት ሠላሳ ዓመታት የዘግናኝ ግፎች ቋት ሆና ቆይታለች። በእነዚህ ዓመታት አገራችን በልዩ ልዩ አስከፊ ሽብሮችና በአብዮት ግርግር እስከተፈጸሙ ግለሰባዊ የቂም በቀል ግድያዎች፥ በደርግ በወያኔና በሻዕቢያ ከተፈጸመ የጦር ሜዳ ወንጀሎች እስከ ቡድኖች የእርስ በርስ ፍጅት፥ ከባዕድ ወረራ እስከ ተገንጣዮችና አስገንጣዮች አመጽ ሲፈራረቁባት የተንገላታች የደም ዕንባ ያነባችና ጀርባዋ የተላጠ አገር ነች።

ብሔራዊ እርቅ ስንል ይኽ ሁሉ እንዳልነበረ ተቆጥሮ፥ የተፈጸመው ግፍ ሁሉ ፍትኃዊ መቋጠሪያ ሳያገኝ ዶሴው ተዘግቶ ወደ ሌላ ነገር እንለፍ ማለት አይደለም። ያለፈው የሩቅም ሆነ የቅርቡ እንዲሁም የዛሬውም የአመጽ ታሪካችን ፋይል ሙሉ በሙሉ ተከፍቶ መጀመሪያ ከግለሰቦችና ከድርጅቶች ባሻገር ኅብረተሰባችንን ለዚህ ያበቁትን መሠረታዊ ጠንቆች ለዚሁ ኅብረተሰብ ትምሕርት በሚሰጥና እነዚህ ጠንቆች ተመልሰው የማይመጡበትን ሁኔታ ለመፍጠር የሚረዳን ሰፊ አገረ-አቀፍ ውይይት እናድርግ ለማለት ነው።

ብሔራዊ እርቅ ስንል ለወንጀለኞች ፍትሐዊ ቅጣት፥ ለተበደሉ ዜጎች ጽናት የሚሰጥ የፍርድ ሂደት አንከተል ለማለት አይደለም። ከልማዳዊውና አስጸያፊው አሸናፊ ወደቤተ-መንግሥት፥ ተሸናፊ ወደ ወህኒ የሚወርድበት የአሸናፊዎች "ፍትኅ" ሳይሆን፥ ሁሉም በእኩልነት ታይቶ አንዱ ወንጀለኛ ተጠያቂ ሆኖ ሌላው ወንጀለኛ ደግሞ ከሕግ በላይ የሚሆንበት፥ ከሰለባዎቹም አንፃር የአንዱ ኢትዮጵያዊ ንጹሕ ደም ከዚያኛው ኢትዮጵያዊ ደም ይበልጣል ሳይባል፥ ማንም ተጠርጣሪ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ ሙሉ በሙሉ በተረጋገጡበት ሁኔታ ፍርድ ቀርቦ ማንም ተበዳይ ደግሞ ፍትሕ የመጠየቅ መብቱ ታውቆለት ለሁለቱም ወገኖች ብሔራዊ እርቅንና ኅብረተሰባችን በሕግ የበላይነት ሊኖረው የሚገባውን ዕምነት በሚያጎለብት መልክ ጉዳዩ እንዲታይ የሚያስችል መድረክ እናመቻች ማለት ነው።

ከነዚህ መሠረታዊ አሳቦች በመነሣት ካለፈው አጥፊ አካሄድ ተላቀን ኢትዮጵያን

የተረጋጋችና ካለፈው ትምሕርት ቀስሞ የወደፊቱን ዕጣ ፈንታዋን በልበ-ሙሉነት እንድታይ ለማድረግ የሚጠብቁን ሁለት መሠረታዊ ተግባራት ናቸው:: በአንድ በኩል የዚህ አስከፊ ሂደታችን ማረሚያ ሳይሆን ማካሄጃ መሣሪያ የሆነውን የኢሕአዴግን ሕገ-ወጥ "ልዩ አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት" ማፍረስ ያስፈልጋል:: በሌላ በኩል ደግሞ የብሔራዊ እርቅ ፈር የሚያስይዝን ልዩ ኮሚሽን የማቋቋም ተግባር ይጠብቀናል::

### 2.2.1 <u>ልዩ አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት የተባለውን ሕገ-ወጥ የፖለቲካ መሥሪያ ቤት ማፍረስ፤</u>

#### 2.2.1.1 <u>ስለ መሥሪያ ቤቱ ሕገ-ወጥነት፤</u>

*መሥሪያ ቤቱ በዜጎች ላይ "የዘር ማጥፋት ወንጀል" እያለ ክስ የሚሰነዝርበት የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት መንግሥት የ1949 ዓ.ም. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 281 ከዓለም-አቀፍ ሕግም ሆነ ከአገራችን ሕገ-መንግሥት አንፃር ሕገ-ወጥ አንቀጽ ነው::*

ይኸ አንቀጽ ለዘር ማጥፋት ወንጀል የሚሰጠው ትርጓሜ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ቁጥር 260A ዲሴምበር 9 ቀን 1949 ዓ.ም. /እ.ኤ.አ/ ጸድቆ ጃንዋሪ 1951 ዓ.ም. ተፈጻሚ የሆነውን "የዘር ማጥፋት (ጄኖሳይድ) ዓለም-አቀፍ ስምምነት" የሚፃረር ትርጓሜ ነው:: በስምምነቱ አንቀጽ 2 መሠረት የዘር ማጥፋት ወንጀል አንድን ብሔር፥ ዘር፥ ጎሳ ወይም የሃይማኖት ስብስብ ሆን ተብሎ በሙሉ ወይም በከፊል ለማጥፋት የሚፈጸም ዓለም-አቀፍ ወንጀል ነው:: የንጉሠ-ነገሥቱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 281 ዘር ማጥፋትን ከነዚህ መሥፈርቶች በተጨማሪ "በፖለቲካ ተሳስሮ የተቋቋመ" ስብስብንም በሙሉ ወይም በከፊል ለማጥፋት የሚፈጸም ድርጊት በማለት ይገልጸዋል:: ማለትም በዓለም-አቀፉ ስምምነት ላይ የሌለን 'የፖለቲካ መስፈርት' ያካትታል:: በዚህም የተነሣ አንቀጽ 281 በስምምነቱ ላይ የሌለ ባዕድ ፅንሰ-ሀሳብ አካትቶ ዓለም-አቀፍ ስምምነቱን በመፃረሩ ከሕግ አንፃር ገና ከፅንሱ ፍርስ እና የሕግ ተፈጻሚነት የሌለው አንቀጽ ነው::

የዛሬው የኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥት እንደሚያደርገው ሁሉ የነጉሡም ሕገ-መንግሥት በአንቀጽ 122 *"ይኸ የተሻሻለው ሕገ-መንግሥት ኢትዮጵያ ተካፋይ ከምትሆንባቸው ከኢንተርናሲዮናል ውሎች፥ ከዓለም ስምምነቶችና ግዴታዎች ጋር በአንድነት ሆኖ የነጉሠ-ነገሥቱ መንግሥት የበላይ ሕግ ይሆናል:: ወደፊትም የሚሠሩ ሕጎች፥ ድንጋጌዎች፥ ፍርዶች፥ ውሳኔዎች ሁሉ ከዚህ ሕገ-መንግሥት ጋር የማይስማሙ ሲሆኑ ዋጋ የሌላቸውና የማያገለግሉ ይሆናሉ"* በማለት ኢትዮጵያ ለተፈራረመቻቸው ዓለም-አቀፍ ስምምነቶች የሕገ-መንግሥት ደረጃ (constitutional status) ያጎናጽፋል:: ይኸም ማለት የዘር ማጥፋት ዓለም-አቀፍ ስምምነትን የሚቃረነው አንቀጽ 281 እዛው በዛው የአገሪቱንም ሕገ-መንግሥት የሚቃረን ስለሆነ የኢሕአዴግ መሥሪያ ቤት በሁሉም መስፈርት በሕገ-ወጥ አንቀጽ ተመርኩዞ የሚሠራ ሕገ-ወጥ መሥሪያ ቤት ነው ማለት ነው::

ይኸ ሕገ-ወጥነት እንደ ቀላል ነገር እንዳይታለፍ የሚያደርገው ሌላም ቁም ነገር አለ:: አንቀጽ 281 በዘር ማጥፋት ወንጀል የፖለቲካ መስፈርትን ሲጨምር ይኸንን ጉዳይ ዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብ "ረስቶት" ንጉሡ "ስላስታወሱት" አልነበረም:: እንዲያውም ስምምነቱ በረቀቀበት ወቅት የዚህ መስፈርት መግባት ወይም አለመግባት ጉዳይ በተለይ በሶሻሊስቱ ሰፈርና በምዕራብ አገሮች ተወካዮች መካከል ብዙ ውዝግብ የፈጠረ ጉዳይ ነበር:: በመጨረሻም የዚህ መስፈርት መካተት ለተለያዩ ሕግ-መተላለፎች (እልፊቶች -abuses) በር ይከፍታል ተብሎ ስለተሰጋ ከስምምነቱ እንዲወጣ ተደርጓል:: "የፊውዳሉን ሥርዓት" ደንቦችና ሕግጋት ለማጥላላት ሲሆን ዓይኑን የማያሸው የኢሕአዴግ መንግሥት ይኸንን ሕገ-ወጥ አንቀጽ 281 ከማሻሻል ይልቅ የሙጥኝ ቢልም ምክንያቱ ግልጽ

ነው:: ዝቅ ብለን እንደምናየው ኢሕአዴግ የፖለቲካ መስፈርትን በሚያስወግድ መልክ አንቀጹ እንዲሻሻል ያላደረገው በመደበኛው የዘር ማጥፋት ወንጀል ትርጉም ቢወሰን የደርግ መንግሥት የትኛውን ዘር፥ የትኛውን ብሔር፥ የትኛውን የሃይማኖት ስብስብ ለማጥፋት ተንቀሳቀሰ ለሚለው ጥያቄ መልስ ስለሚቸግረውና ዘር ማጥፋት (ጀኖሳይድ) በሚለው ከባድ ውንጀላ የመነገዱና የፖለቲካ አጀንዳ የማራመዱ ዕድል እንደሚያከትም ጠንቅቆ በማወቁ ነው::

### 2.2.1.2 <u>ስለ መሥሪያ ቤቱ የፖለቲካ መሣሪያነት፤</u>

አንደኛ መሥሪያ ቤቱን ያቋቋመው አዋጅ ቁ. 22/1984 ዓ.ም. ገና ከመንደርደሪያው በጥንቱና ባረጀ ባፈጀው የአሸናፊዎች የቂም በቀል ጥማት ላይ የተመረኮዘ ነው:: በመሆኑም የአሸናፊው ወገን መሪዎች የጦር ሜዳ ወንጀሎች እንዳልፈጸሙ፥ በገዛ አባሎቻቸው ላይ የአንጃ ለአንጃ ፍጅት እንዳላካሄዱ፥ የደርግ ተባባሪ በሚል ሰበብ በየደረሱበት የገበሬ ልጆችን እንዳልጨፈጨፉ ባጭሩ አሥራ ሰባት ዓመት በአበባ ምንጣፍ ላይ እየተራመዱ አዲስ አበባ የገቡ ይመስል፥ ከዚያም አልፈው ተርፈው አገሪቱን ከተቆጣጠሩ ወዲህ በሕዝባችን ላይ ይኸ ነው የማይባል ግፍ፥ አፈና የጅምላም ሆነ የግለሰብ ግድያ ያላካሄዱ ይመስል፥ መሥሪያ ቤታቸው የነሱን ወንጀሎች የመመርመር ተልዕኮ የለውም:: ይኸ መሥሪያ ቤት "ለመቅጣት" የተነሣው በአጠቃላይ በሕዝባችን ላይ ትላንትም ግፍ የፈጸሙትንና ዛሬም በመፈጸም ላይ ያሉትን ወንጀለኞች በሙሉ ሳይሆን ድል የተመቱትን "የደርግ/ኢሠፓ መንግሥት ባለሥልጣኖች፥ የደህንነትና የጦር ኃይሎች አባሎች፥ የመንግሥት ባለሥልጣኖች፥ እንዲሁም በወንጀሉ አፈጻጸም በከተማ ነዋሪዎችና በገበሬ ማኅበሮች ስምና በግለሰብ ደረጃ ተባባሪዎች የነበሩ" ዜጎችን ብቻ ነው:: ከዚህ አንፃር በደቡብ አፍሪካ በሚካሄደው "ያለፈውን የማወራረድ" ሂደት የሚመረመሩት ወንጀሎችም ሆኑ ለምርመራና ለፍርድ የሚቀርቡት ግለሰቦች የተሸነፈው የአፓርታይድ ፓርቲ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ በሥልጣን ላይ ያለውም የአፍሪቃ ብሔራዊ ኮንግረስ (ANC) አባላትም መሆናቸውን መጥቀስ ብቻ በሁለቱ አካሄዶች መኻከል ያለውን እንደ ሰማይና ምድር የተራራቀ አሠራር ያሳየናል::

ሁለተኛ የዳኝነት ነፃነት በሌለባት አገራችን ይባስ ተብሎ ይኸ መሥሪያ ቤት ለሌሎቹ የፍርድ ተቋማት የተሰጠው የይስሙላ ነፃነት እንኳን ስለሌለውና በተቋቋመበት አዋጅ አንቀጽ 2/2 መሠረት ተጠሪነቱ ለማንም ለማንም ሳይሆን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው:: ስለሆነም ይኸ አሠራር ገና ከጥንስሱ አንዱ ወገን እዛው በዛው ከሳሽም ዳኛም (Audi Alter am par tem) መሆን የለበትም የሚለውን መሠረታዊ የፍትኅ መርኅ በመጣስ የሚሠራ ጽሕፈት ቤት ነው::

ሦስተኛ መሥሪያ ቤቱ የተቋቋመው የቂም በቀል ጥማት ለማርካት ብቻ ሳይሆን ከሱም ይልቅ ዛሬ ማንኛውንም ተቃውሞ ለማኮላሸትና ለማስፈራራት እንደሆነ ግልጽ ነው:: ማንኛው ዜጋ ቢሆን በሁለትም፥ በአምስትም፥ በአሥርም ዓመት ሆነ ከዚያም በላይ በእስራት ለመቀጣት በዚህ የፖለቲካ መሥሪያ ቤት "መጠርጠር" ብቻ ይበቃዋል:: የዚህን ዓይነት አሠራር ግፈኛነትና በኅብረተሰቡ ውስጥ የፈጠረውን ከመንግሥታዊ ሽብር የሚዋሰን የዜጎች የኑሮ ዋስትና ማጣት መላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ ስለሚያውቀው ዝርዝር ውስጥ መግባት አያስፈልግም::
ግልጽ ከሆነው ከሕገ-ወጥነቱና ከፖለቲካ መሣሪያነቱ አንፃር ዓይተውና መዝነው፥ ከሁሉም በላይ ደግሞ አገራችን ለሚያስፈልጋት ብሔራዊ እርቅ ሂደት እንቅፋት ነው ብለው ይኸ መሥሪያ ቤት እንዲፈርስ እንደኛ ጥሪ ባያደርጉም በመፈጸም ላይ ያለውን ግፍ እውቅ የሆኑ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች በተደጋጋሚ እንዳወገዙት የአደባባይ ምስጢር ነው:: "የዘፈቀደ እስራቶች ተከታታይ ቡድን" (Working Group on Arbitrary Detentions) በ1988 ዓ.ም. ባወጣው ሪፖርት የልዩ አቃቤ ሕጉ ጽ/ቤት በዓለም-አቀፍ ደረጃ ከፀኑ ስምምነቶች

አንፃር ስፍር ቁጥር የሌላቸው አንቀጾችን እንደሚፃረር ሲዘረዝር የመሥሪያ ቤቱ አካሄድ ከታኅሣሡ 1942 ዓ.ም. ዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች አዋጅ አንፃር አንቀጽ 9 እና አንቀጽ 10ን፥ ከታኅሣሥ 1958 ዓ.ም. የዜግነትና የፖለቲካ መብቶች ዓለም-አቀፍ ስምምነት አንፃር አንቀጽ 9 እና አንቀጽ 14ን፥ ከሚያዝያ 1969 ዓ.ም. የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሶሻልና የኢኮኖሚ ም/ቤት እስረኞችን ለመንከባከብ በውሳኔ ቁ. 207(62) ከወጡት ዝቅተኛ ደረጃ ደንቦች አንፃር አንቀጽ 2, 4, 9, 10, 32, 37, እና 38ን የሚጥስ አሠራር መሆኑን አጋልጧል።

2.2.1.3 <u>***አገራችን ለሚያስፈልጋት የብሔራዊ እርቅ ሂደት እንቅፋት ስለመሆኑ፤***</u>

ከጥንስሱ ሕገ-ወጥ የሆነው የፖለቲካ መሥሪያ ቤት ይኸንን ሁሉ መብት ረገጣ የሚያካሂደው በአንድ በኩል በተለይ የውጭውን ዓለም የፖለቲካ፥ የማቴሪያልና የዲፕሎማሲ ድጋፍ ብቻ ሳይሆን የሚካሄደውን መብት ረገጣ በቸልታ እንዲያዩለት በአገራችን የተፈጸመውን ግፍ ''ዘር-ማጥፋት'' (ጄኖሳይድ) ብሎ ጠርቶታል። ሆኖም ብሔር፥ ያታ፥ ዘር፥ ሃይማኖት፥ እድሜ ሳይል በሕዝባችን ላይ ደርግ ባወረደው መዓት የትኛውን ብሔር፥ ዘር፥ የሃይማኖት ስብስብ "በሙሉ ወይም በከፊል ለማጥፋት" እንደተሞከረ መጠቆም ስለማይችል ይኸንን ቁልፍ ጥያቄ እስካሁን አንስቶት አያውቅም።

በአገራችን የተፈጸመው ይኸ ነው የማይባል ግፍ በራሱ በበቂ አሰቃቂ፥ በራሱ በበቂ በአገርና በሕዝብ ላይ የተፈጸመ ከባድ ወንጀል በመሆኑ፥ ለፖለቲካ ጥቅምና የሕዝባችንን የሰቆቃ ዘመን ለማራዘም ካልሆነ በስተቀር ''ዘር-ማጥፋት'' (ጄኖሳይድ) በሚል መጠሪያ መጋነን አያስፈልገውም።
በኢትዮጵያውያን ዘንድ ይኸ የሰው ዘር ማጥፋት በሚል የተመሠረተው ክስ መሠረታዊ ፍትሐዊና ሚዛናዊ አመለካከት የጎደለውና ለቂም በቀል ያለ ጥማትን ለማርካት ሲባል የተሰነዘረ ተደርጎ ነው የሚታየው። የአውሮጳና የአሜሪካ መንግሥታት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ተታለውም ሆነ አውቀው በጭፍን የኢሕአዴግን አካሄድ በገንዘብ፥ በማቴሪያልና በዲፕሎማሲውም ዘርፍ በማገዛቸውና በተለይም በደቡብ አፍሪቃ በነበረው የአፓርታይድ ሥርዓት የተፈጸሙ ግፎች ከዘር-ማጥፋትና በሰው ልጅ ላይ ከተፈጸሙ ወንጀሎች ጋር የሚዛመዱ መሆናቸው እየታወቀ በዚያ አገር እርቅና ሰላምን እንዳልሰበኩ አሁን በኢትዮጵያ ያለው አገዛዝ የሚያካሂደውን የመብት ረገጣ በግልጽ አለመቃወማቸው ኢትዮጵያውያንን አሳዝኗል። የደቡብ አፍሪቃ ሕዝቦች የእርቅን መንገድ ይዘው ለጋራ ጥቅም በአንድ ላይ ለመሥራት ወስነው ብዙ ምስቅልቅል ችግሮችን ማስወገድ በመቻላቸው ለብዙ አውገሮች ምሳሌ ሆነዋል።

ልዩ አቃቤ ሕግ የተባለ የፖለቲካ መሥሪያ ቤት በተቋቋመበት አዋጅ የሂደቱ ዋና ዓላማ ለመጭው ትውልድ *"ይኸ ዓይነት ሥርዓት እንዳይደገም ማስገንዘብና ማስተማሩ ትክክለኛ ታሪካዊ ግዳጅ መሆኑን በማመን"* ይኸንን ተልዕኮ ለማራመድ እንደሆነ ተገልጿል። ነገር ግን አሥራ ሰባት ዓመት በትጥቅ ትግል ከፖለቲካ ተቀናቃኞቹ ከታገለ በኋላ ኢሕአዴግ በትላንት፥ በዛሬና በነገ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ብሎም በጠቅላላው በኅብረተሰቡ ላይ ይኸንኑ ጦርነት ሕጋዊ ሽፋን ሰጥቶ ለመቀጠል ባቋቋመው መሥሪያ ቤት ይኸ በጎ ተልዕኮ ተግባራዊ ይሆናል ማለት ዘበት ነው።

ዛሬ በብሔራዊ እርቅ ፖለቲካ መንፈስ እየተመራን በእኩልነትና በሕግ የበላይነት ላይ የተገነባ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ለኢትዮጵያችን ኅልውና እንደ ሕይወት እስትንፋስ አስፈላጊና አንገብጋቢ ተግባር ነው። ይኸ ባለፈው "የተፈጸሙ" ወንጀሎች ቢልም አሸናፊዎቹንም ለፈጸሟቸው ወንጀሎች ተጠያቂ የማድረግ ተልዕኮ የሌለው፥ ይኸ ባለፈው "የተፈጸሙ" ወንጀሎች ሲል ዛሬ በሕዝባችን ላይ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች ተጠያቂዎችን ለፍርድ ለማቅረብ ምንም ሥልጣን የሌለው አካል ብሔራዊ እርቅን

ለማስፈንና ለእነዚህ እሴቶች እውንነት ሲባል መፍረስ ይኖርበታል እንላለን፡፡

## 2.2.2 <u>የብሔራዊ እርቅ ኮሚሽን ማቋቋም፤</u>

ባለፉት ሠላሳ ዓመታት በዓለም ዙሪያ በርካታ አገሮች ከጦርነትና ከአስከፊ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዞች እየተላቀቁ ወደ ሰላምና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመሸጋገር ጥረት አድርገዋል፡፡ አንዳንዶቹ ለምሳሌ እንደ ደቡብ አፍሪቃ፥ ቺሊ፥ ካምቦዲያ፥ ስፔይን የመሳሰሉት ይኸ ጥረታቸው ተሳክቶላቸው ሃያም፥ ሠላሳም፥ አርባም ዓመታት ከተካሄዱ ግጭቶችና ከሰፈኑ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዞች ተላቀው የብሔራዊ እርቅ ጎዳናን በመከተል የሰላም፥ የዴሞክራሲና የአገር ግንባታ ምዕራፍ ለመክፈት በቅተዋል፡፡ ሌሎች ደግሞ ለምሳሌ እንደ ኢትዮጵያና ሩዋንዳ ያሉ አገሮች እስካሁን ይኸ ጥረት ያልተሳካላቸው አሉ፡፡ እርግጥ በነዚህም አገሮች ግጭቶችና ጦርነቶች በርደው አንፃራዊና በቋፍ የቆመ ሰላም ተገኝቷል፡፡ ነገር ግን ይኸ ሰላም ከነዚህ ግጭቶች በአሸናፊነት የወጡት ኃይሎች ባካሄዱት ትግል የከፈሉትን መስዋዕትነት የወደቀው ጠላት ብቻ ሳይሆን መላ ኅብረተሰቡም ብድሩን ከነወለዱ እንዲከፍላቸው የሚጠይቁበት እርቅ አልባ ሰላም ነው፡፡ በመሆኑም ሽግግር እንደተሳካባቸው አገሮች ተረጋግቶ ያለፈውን እየጠገነ የወደፊቱን በተስፋና በሙሉ ልብነት የሚመለከት ኅብረተሰብ መፍጠር ገና አልቻሉም፡፡

ብሔራዊ እርቅና የተረጋጋ ኅብረተሰብ ሲባል የዴሞክራሲን መስፈን ስለሚጠይቅና እነዚህ ኃይሎች ደግሞ ፀረ-ዴሞክራሲ በመሆናቸው፥ ብሔራዊ እርቅና የተረጋጋ ኅብረተሰብ ሲባል በሕግ የበላይነት የሚተዳደር አገር ሲሆን፥ እነዚህ ኃይሎች ደግሞ በሆነ የታሪክ አጋጣሚ አሸንፈው የተጎናፀፉትን የበላይነት ዘላቂ ለማድረግ ለሚጥሩ፥ ብሔራዊ እርቅና የተረጋጋ ኅብረተሰብ ሲባል የወንድማማችነትና የአንድነት መንፈስ እንዲሰፍን መሥራት ሲሆን፥ እነዚህ ኃይሎች ኅልውናቸውን ለማስረገጥ የሚጥሩት በተለያዩ ዘዴዎችና ምክንያቶች ያለፈውን መነካከስ በመቀጠል ላይ በመሆኑ፥ በነዚህ አገሮች ለብሔራዊ እርቅ የሚደረገው ትግል ለዴሞክራሲና ለሕግ የበላይነትና ለሕዝቦች ወንድማማችነት ከሚደረገው ትግል ተለይቶ ሊታይ አይችልም፡፡ በመሆኑም እኛ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ኃይሎች የብሔራዊ እርቅ ፖለቲካ ማካሄድ ለአገራችን ዴሞክራሲ ቁልፍ አስተዋጽዖ ይኖረዋል ብለን በማመናችን ይኸንን የተቀደሰ ዓላማ ከግብ ለማድረስ እንዲረዳ አንድ <u>የብሔራዊ እርቅ ኮሚሽን እንዲቋቋም ጥረት እናደርጋለን፡፡</u>

### 2.2.2.1 <u>የብሔራዊ እርቅ ኮሚሽን ተግባራት፤</u>

2.2.2.1.1 በመላ አገሪቱ በደርግ ዘመን በመንግሥት ተቋማት፥ በሌሎች ስብስቦችና በተለያዩ ግለሰቦች ወንጀሎችና በጦርነቶች ሳቢያ በመንግሥት ሠራዊትም ሆነ በተቃዋሚ ተዋጊዎች የተፈጸሙ የጦር ሜዳ ወንጀሎችንና እንደዚሁም በኢሕአዴግ አገዛዝ ዘመን በመንግሥት ተቋማት፥ በሌሎች ስብስቦችና በተለያዩ ግለሰቦች የተፈጸሙ ወንጀሎችን ሰብስቦ ይመዘግባል፤

2.2.2.1.2 ኮሚሽኑ እነዚህን ወንጀሎች ከአራማጆቹም ሆነ ከሰለባዎቹ በሚገኙ መረጃዎች አማካኝነት ከመሰብሰብ አልፎ ኅብረተሰባችንን ለዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ያጋለጡትን መሠረታዊ የሆኑ የታሪክ፥ የባሕል፥ የፖለቲካና ሌሎች ምክንያቶች በሰፊው መርምሮ እነዚህ ጠንቆች ተወግደው በአገራችን ዘላቂ ሰላም የሚወርድበትን የብሔራዊ እርቅ ስትራቴጂ በመንደፍ ግኝቱን ለብሔራዊ ውይይት ያቀርባል፤

2.2.2.1.3 በአገራችን በሁሉም ብሔረሰቦች አካባቢ ችግሮችን በእርቅና በሽምግልና አማካኝነት የማስወገድ ባሕል ያለና ተጨባጭ እውነታ በመሆኑ የተነሣ ዛሬ ብዙ ጥናቶች

እንደሚያሳዩት በፍርድ ቤት መፍትሔ ከሚያገኙት አለመግባባቶች ይልቅ በሽምግልናና በእርቅ የሚፈቱት አለመግባባቶች በቁጥር እጅግ የላቁ ሆነው የሚታዩበት ሁኔታ አለ። በመሆኑም ኮሚሽኑ በየአካባቢው ጥናት በማካሄድ ይኸ የብሔራዊ እርቅ ስትራቴጂ በተቻለ መጠን በዚህ አገር-በቀልና ነባር ባሕል ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ያደርጋል፤

2.2.2.1.4 ይኸንኑ ዓላማ ለማራመድ በዓለም ደረጃ ከተሳኩም ካልተሳኩም የሽግግርና የብሔራዊ እርቅ ሂደቶች ለአገራችን የሚጠቅሙ ትምሕርቶች መቅሰም ስለሚቻል ኮሚሽኑ የብሔራዊ እርቅ ስትራቴጂውን ሲነድፍ ከነዚህ ልምዶችና ተመክሮዎች በመነሣት ይሆናል፤

2.2.2.1.5 ኮሚሽኑ የዚህን ሰነድ መነደፍ ሳይጠብቅ በኢሕአዴግ ልዩ አቃቤ ሕግ የፈጠራ ክስ ተመሥርቶባቸው ስምንትም ዘጠኝም አሥርም ዓመታትና ከዚያም በላይ ታስረው ቤታቸው ከፈረሰ፥ ስብዕናቸውና ቅስማቸው ከተሰበረ በኋላ ንጽሕናቸው ተረጋግጦ ነፃ የተለቀቁ ዜጎችን መልሶ ለማቋቋም የሚቻልበትን ዘዴ አጥንቶ በዚህ ጉዳይ ለመንግሥት አሳብ ያቀርባል፤

2.2.2.1.6 በጠቅላላ የምሕረት ጉዳይ በዝርዝር ተጠንቶና ኅብረተሰቡ በሰፊው ተወያይቶበት እልባት እስኪያገኝ ድረስ ዛሬ ተፈርዶባቸውም ሆነ ሳይፈረድባቸው በእስር ከሚገኙት ዜጎች መኻከል መታሰራቸው በግልጽ በፖለቲካ ምክንያት የሆነ ዜጎች፥ የተያዙበትን ወንጀል ፈጽመዋል በተባሉበት ወቅት ለአቅመ-አዳም ወይም ለአቅመ-ሔዋን ደርሰው ያልነበሩ ዜጎች፥ በእርጅናም ሆነ በጤና መታወክ የተነሣ ያሉበት ሁኔታ ከእስረኛነት ጋር የማይጣጣም ወይም ደግሞ አልተፈረደባቸውም እንደሆነ ፍርድ ቤት ቆመው ራሳቸውን ለመከላከል የማይችሉ ዜጎች ሁሉ በአስቸኳይ የሚፈቱበትን ሁኔታ ለመንግሥት አሳብ ያቀርባል፤

2.2.2.1.7 የኢሕአዴግ መንግሥት በቂም በቀል ፖለቲካው፥ ዜጎችን በጅምላ የኢሠፓ አባል፥ የቀድሞው የኢትዮጵያ ሠራዊት፥ የፖሊስና የደኅንነት አባል እያለ የዜግነት መብት የነፈጋቸውና ከሥራ በማፈናቀልም ሆነ የሚገባቸውን የጡረታ መብት በመንፈግ ለከፍተኛ ችግር የዳረገው ዜጎች ሁኔታ ፍትኃዊ መፍትሔ እንዲያገኝና እንዲህ ዓይነቱ የግፍ ድርጊት ለወደፊቱም ዛሬ በሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ላይ የማይደገምበትን መንገድ አጥንቶ አሳብ ያቀርባል፤

2.2.2.1.8 የብሔራዊ እርቅ ሂደት በአንድ ገጽታው ወንጀል የፈጸሙ ዜጎችን አስመልክቶ የሚደረገውን የምኅረት ፖሊሲ የሚመለከት እንደሆነ ግልጽ ነው። የዚያኑ ያህል ደግሞ ምኅረት በእርግጥ ለአገራችን ሰላምና መረጋጋት እንዲያመጣ ከተፈለገ በመንግሥት፥ በፓርላማም ሆነ በማንም ኃይል በኅብረተሰቡ ላይ ከመጫኑ በፊት ዋና ባለጉዳዮች የነዚህ ወንጀሎች ሰለባ የሆኑት ዜጎች መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል። እነዚህ ዜጎች ያላመኑበት የምኅረት ፖሊሲ አገራችን የሚያስፈልጋትን የፍትኃዊነትና የእርቅ ስሜት የሚሸረሽር ስለሆነና በዚህ በኩል ማንኛውም ውሳኔ ከሁሉም በፊት ሰለባዎቹን ባካተተ ብሔራዊ ውይይት መውሰድ ስለሚኖርበት በዚህም መንፈስ ውይይት የሚካሄድበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

## 2.2.2.2 <u>የብሔራዊ እርቅ ኮሚሽኑ አባላት፤</u>

ይኸ ኮሚሽን ተልዕኮውን በሚገባ ለመፈጸም እንዲችል በአገሪቱ ያሉ የተለያዩ የፖለቲካና የሲቪክ ስብስቦችን፥ ለዚህ ተግባር ብቃት ያላቸው ባለሙያዎችንና ምሁራንን፥ በየአካባቢው ተቀባይነት ያላቸው የአገር ሽማግሌዎችና ሌሎች አስተዋጽዖ ሊያደርጉ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ዜጎችን ማካተት ስለሚኖርበት በሂደት ሌሎችም

የመጨመራቸው ዕድል እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን ወገኖች ማለትም፡-

1. የጠበቆች ማኅበር ተወካዮችና ከሕግ ፋኩልቲ መምህራን መኻከል የተመረጡ ምሁራን፥
2. ከአገሪቱ ዩኒቨርስቲዎችና የምርምር ተቋማት በፖለቲካ፥ በታሪክ፥ በሰላምና በመሳሰሉት ተዛማጅ መስኮች ጥናት ያካሄዱ ዜጎች፥
3. ከሠራተኞች፥ ከገበሬዎች፥ ከመምህራንና ከሌሎች የሙያ ማኅበራት የሚወከሉ ዜጎች፥
4. ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባዔና (ኢሰመጉ) ከሌሎች የሰብአዊ መብት ተሟጋች መያዶች፥
5. ከሴቶች፥ ከወጣቶችና ከሌሎች ሕዝባዊ ድርጅቶች፥
6. ከንግድ ምክር ቤት፥
7. ከተለያዩ የሃይማኖት ተቋማት፥
8. ከየአካባቢው ተመርጠው ከሚሰየሙ የአገር ሽማግሌዎች፥
9. ከጥንታዊት ኢትዮጵያ አርበኞች ማኅበር፥
10. ኢሕአዴግን ጨምሮ ከተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች፥

የሚወከሉ ዜጎችን የሚያካትት ይሆናል።

## IV. ክፍል ሦስት ፤

## 3. መደምደሚያና የትግል ጥሪ፤

### 3.1 አማራጭ ስንል ልዩነቱ፤

የምናቀርባቸውን አማራጮች ኢሕአዴግ አንዳንዶቹን በአሸበረቁ ቃላት አንዳንዴም በወፍራፍራም ጥራዞች ሊያስቀምጣቸው ይችላል። ይኸ ስለ ሰላም፥ ስለ ዴሞክራሲና ስለ አገር አንድነት፥ ስለ ብሔራዊ ክብርና ጥቅም ሲለፈፍ በሕዝባችን ፊት ቅንጣት ተኣማኒነት የሌለው ኃይል ርሃብን የማጥፋቱ፥ ድህነትን የመቅረፉ፥ ትምሕርትን የማስፋፋቱ፥ ሥራ-አጥነትን የመዋጋቱ፥ ለብሔራዊ ኤኮኖሚ ልማት ጠንካራ መሠረት የመጣሉ ጉዳይም ቢሆን ያመንኩበት፥ የምለፋበት ዓላማዬ ነው ሊለን ይችላል። ነገር ግን እነዚህን እውን ለማድረግ አንዳንዴ በመቶ ገጾች የሚቆጠሩ ሰነዶች በምሁሮቹ እያስረቀቀ፥ በባእዳን አሳዳሪዎቹ እያስፀደቀ ለትውልድ የሚተላለፍ ብቻ ሳይሆን ዛሬ ማንኛውንም የእድገት ጥረታችንን የሚያኮላሽ እዳ ውስጥ እየተነከረልን ባልሆነ አቅጣጫ ስንኳትን እነሆ አሥራ አምስት ዓመታት አስቆጠርን።
በነዚህ ዓመታት አንዴ ነፃ ገበያና ፕራይቬታይዜሽን፥ ሌላ ጊዜ የመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም፥ ቀጠል አድርጎ ደግሞ የድህነት ቅነሳና ስትራቴጂ፥ ከዚያ ደግሞ ግብርና ልማት-መር ኢንዳስትሪያላይዜሽን፥ ወዘተ... እየተባለ ለሕዝባችን የኑሮ ሰቆቃ መፍትሔ እየተባለ ያልተለፈፈ ነገር የለም። ይኸ ሁሉ ሆኖ ግን ዛሬ አገራችን ያለችበትን አሳፋሪ የድህነትና የመራቆት ብቻ ሳይሆን የተያያዘችውን የቁልቁለት ጉዞ ምንም ስታቲስቲክስ፥ ምንም 'ዲስኩር' ሊሸፍነው አይችልም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዛሬ ሃያ ዓመት ዛሬ ይበልጥ ጎስቋላና ድሃ ሕዝብ ነው። ከሁለት ዓመታት በፊት የዓለም ባንክ ባወጣው ዘገባ ከሃያ ዓመታት በፊት በአማካኝ መቶ ዘጠና የአሜሪካ ዶላር ($190.00) የነበረው የነፍስ-ወከፍ ገቢ የዛሬ ሁለት ዓመት ወደ መቶ ዘጠኝ ዶላር ($109.00) ወርዶ ነበር። ዛሬ ደግሞ ዘጠና ዶላር ($90.00) ደርሷል። የኢትዮጵያ

ሕዝብ ከዛሬ ሃያ ዓመት ዛሬ መጭው ጊዜ እንዲጨልምበት የተደረገ ሕዝብ ነው:: ሴቭ ዘ ችልድረን የተባለ የሕፃናት ጉዳይ ተከታታይ ግብረሰናይ ድርጅት ባቀረበው ዘገባ መሠረት ከአሥር ዓመታት በፊት በአገራችን የከፋ ማጣት ያጠቃቸውና ለጎልውናቸው ከዚያው ከአካባቢውም ሆነ ከዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብ በሚገኝ ምፅዋት የሚተዳደሩ ዜጎች ከሕዝቡ አምስት ነጥብ አምስት ከመቶ (5.5%) ነበሩ:: ዛሬ አሥራ አራት ነጥብ ስድስት ከመቶ (14.6%) ሆነዋል:: በዚሁ ጥናት መሠረት አገራችን በኢሕአዴግ ፖሊሲ ከቀጠለች በአሥር ዓመታት ውስጥ የነዚህ ድሆች ቁጥር ሃያ አንድ ከመቶ (21%) ይደርሳል ተብሎ ይጠበቃል:: ይኸም ማለት ከሕዝባችን ከአንድ አምስተኛው በላይ ምፅዋተኛ ይሆናል ማለት ነው::

በአጭሩ የኢሕአዴግ ፖሊሲ አልሠራም:: ወደፊትም አይሠራም:: እኛም እነሱም ድህነት ቅነሳ÷ ነፃ ገበያ÷ ልማት÷ ብልጽግና÷ ወዘተ... ስንል በእኛና በነሱ መኻል ያለው ልዩነት እኛም እነሱም ዴሞክራሲ÷ ነፃ ምርጫ÷ የአገር አንድነትና ክብር ስንል ያለውን ልዩነት የሚያክል ነው:: እባብ ያዬ በልጥ በረዬ (ልጥ ይፈራል) ነውና ለአሥራ አራት ዓመታት በነዚህ ሁሉ እሴቶች አንፃር ያለ የሌለ ቃል የተገባላቸው ነገሩ ሁሉ የውሃ ሽታ የሆነባቸው ዜጎች የእናንተስ አማራጭ ለተግባራዊነቱ ምን ዋስትና አለው? ብለው ሊጠይቁ ይችላሉ:: ለዚህ መልስ ለመስጠት በኛ በኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር-ወዳዶች በአንድ በኩል÷ በኢሕአዴግ አካሄድ በሌላ በኩል ከአሉት መሠረታዊ ልዩነቶች ሦስቱን ብቻ አቅርበን ሰነዳችንን እንደመድማለን::

የመጀመሪያው መሠረታዊ ልዩነት ኢትዮጵያዊ የሆነ ራእይ መኖር አለመኖርና መላውን ሕዝባችንንና ችግሮቹን በአንድ ዓይን የማየት ወይም ያለማየትን የሚመለከት ልዩነት ነው:: ኢሕአዴግ በፖለቲካው መስክ ሕዝባችንን በብሔር/ብሔረሰብ ከፋፍሎና አናክሶ ዕድሜውን ለማራዘም የሚጥረውን ያህል በርእዮተ-ዓለም ምርጫውና በተራ ፖለቲካ ስትራቴጂው የተነሳ ላሉት ቀውሶች የሚጠቁማቸው "መፍትሄዎች" ሕዝባችንንና ትግሉን ከፋፍሎ በማዳከም ላይ ያነጣጠሩ ናቸው:: ይኸ የኢሕአዴግ ስትራቴጂ ዛሬ የድሃውን ገበሬ ችግር ቀርፌ÷ ነገ የሥራ አጡን ወጣት ጉዳይ ተያይዤ÷ ከነገ ወዲያ ደግሞ በሴቶች ጭቆና ላይ አተኩሬ÷ ወዘተ.... እያለ የሚውገረገረውን ያህል የእኛ ስትራቴጂ ደግሞ ከፍ ብለን ለማብራራት እንደሞከርነው ገና ከመነሻው ዛሬ በአገራችንንና በሕዝባችን ፊት የተደቀኑትና "አንዱ የሌላው መነሾም መዘዝም እየሆኑ" ተጋግዘው የሚባባሱ ቀውሶች መሆናቸውን የተቀበለና "ተራ በተራ" የሚለውን የወያኔ/ኢሕአዴግ አካሄድ ተቃውሞ <u>"ለሁለገብ ቀውስ ሁለገብ መፍትሔ"</u> የሚል ስትራቴጂ ነው:: የዚህ አቋማችን የፖለቲካ ትርጉም ግልጽ ነው:: እነዚህን ዋና ዋና የሆኑትን ቀውሶች በአንድ ሂደት ሁሉንም ግንባር ለግንባር እንግጠማቸው የምንለው ያለን ምርጫ ወይ ተደጋግፎ ማለፍ ወይ ደግሞ ተያይዞ መውደቅ ስለሆነ ብቻ አይደለም:: ሥራ-አጡ ከተሜ ወጣት ረሃብ ካጠቃው ድሃ ገበሬ÷ ሙስና ያንገፈገፈው ነጋዴ ከጎዳና ተዳዳሪው÷ እራሱን ጠቅሞ አገር እንዳያለማ አድልዖአዊ ፖሊሱ እጅ ተወርች ያሰረው ኢንቬስተር በኑሮ ጠርዝ ላይ ከተንጠለጠለው ስራተኛ ጋር ተጋግዞ በአንድነት እንዲታገል የሚያስችለውን ሁኔታ ለማመቻቸትም ነው::

ሁለተኛው መሠረታዊ ልዩነት በዴሞክራሲና በሕዝብ ተሳትፎ ላይ ያለው ልዩነትር ነው:: የኢሕአዴግ አጋዛዝ ድህነትን እዋጋለሁ የሚለው ትግሉን በዚህ መልክ ከፋፍሎና ሕዝባችንን የመብት ድሃ አድርጎ እጅ እግሩን አስሮ በያዘበት ሁኔታ ነው:: የሕዝብ ተሳትፎ የሚለው ልፈፋ በየደረጃው ይኸንን ተሳትፎ በካድሬዎቹ ሙሉ ቁጥጥር ሥር አድርጎ በሚያኮላሽበት ሁኔታ ነው:: የእኛ አካሄድ ለሕዝባችን ይኸንን እናደርግልሃለን÷ ያንን እንፈጽምልሃለን እመነን የሚል አካሄድ አይደለም:: ከአለው ችግር የሚወጣበትን አማራጭ በግንባር ቀደምነት እየጠቆመ ለዚህ ተግባራዊነት ሕዝቡ እራሱ ተደራጅቶና ተጋግዞ እንዲታገል የሚጠራ አካሄድ ነው:: በአዲስ አበባ ብቻ ተምሮም ሳይማርም በሥራ-አጥነት ቀኑ የጨለመበት ግማሽ ሚሊዮን ወጣት አለ:: አማራጫችንን ስናቀርብ ለዚህ ቀቢጸ-ተስፋ ለሆነ ትውልድ የምንለው "በገዛ አገርህ ሠርቶ የመኖር መብት አለህ÷ ለዚህ ተደራጅተህ ለዚህ ሁለገብና ቀጣይ መከራ የዳረገህን ሥርዓት ሰልፍም እየወጣህ ሆነ በሌላ ሰላማዊ ዘዴ

አስወግደህ ለራስህ የተሻለ ቀን አምጣ'' የሚል የገዛ ዕድሉን እጁ ውስጥ እንዲያስገባ የሚጠራ፥ በመላ አገሪቱ ከሚደረገው ሰላማዊ ትግል ጋር ትግልህን አስተጋግዝ እያለ የሚቀሰቅስ ከወጣቱም ሆነ ከጠቅላላው ሕዝብ አንድነትና የመብት ትግል ምንም የሚፈራው ነገር የሌለው አማራጭ ነው።

ሦስተኛው መሠረታዊ ልዩነት በአገርና በሕዝብ ፊት ተጠያቂነት መቀበልን ወይም አለመቀበልን የሚመለከት ልዩነት ነው። ዴሞክራሲ በታፈነበት ሁኔታ ምንም ተጠያቂነት ስለሌለ የኢሕአዴግ አመራር ለአሥራ አራት ዓመታት ባሸበረቁ ቃላት ለሕዝባችን የሚሰጣቸው ተስፋዎች ተግባራዊ ሆኑ አልሆኑ የሚጨነቅባቸው አይደሉም። የእኛ የኢትዮጵያ አገር-ወዳዶችና ዴሞክራቶች መነሻ ነጥባችንንና የትግል ዓላማችን ዴሞክራሲና ተጠያቂነት ነው። የዴሞክራሲ መስፈንና የተጠያቂነት መኖር በራሱ በመሠረታዊ እሴትነቱ የምንታገልለት ዓላማ ብቻ አይደለም። የዴሞክራሲ መስፈን ሕዝባችን ላሉበት ችግሮች ከሚቀርቡለት አማራጮች መኻል ይሆነኛል የሚለውን እንዲመርጥ ያስችለዋል። ተጠያቂነት ከሌለ የመረጣቸው አማራጮች ተግባራዊ ለመሆናቸው ተግባራዊ ለመሆናቸው ምንም ዋስትና አይኖርም። በመሆኑም ማንኛውም የምናቀርበው አማራጭ ለዴሞክራሲ መስፈን ከሚደረገው ትግል ውጭ የሚታሰብ አይደለም።

ትግላችን ለሁላችን የሚበጅ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት እንጅ የተወሰውን ክፍል ጎድቶ ሌላውን ለመጥቀም ወይም መተካትና መለወጥ አለበት በምንለው አገዛዝ ሥር ያሉ ማናቸውንም ቢሆን በግልም ሆነ በቡድን ለመጉዳት ወይም ከሥራ ገበታቸው ሕገ-ወጥ መፈናቀል እንዲደርስባቸው ለማድረግ አይደለም። አገራችንንና ሕዝቧን የግድ ወደ ጎጂና አደገኛ አለመረጋጋትና የሥርዓትና የሰላም መፋለስ ይዟት እየተጓዘ የሚገኘው የኢሕአዴግ አገዛዝ በሰላማዊ ሂደት በዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ይተካ ስንል ሁሉም ተጠቃሚ የሚሆንበት የሰከነ ሽግግር ለማድረግና ብዙ አገሮች የተጓዙበትን አደገኛ ትርምስና አሰቃቂ ቀውስ ለማስወገድ እንዲቻል ብቻ ነው።
ውድ አገራችን ኢትዮጵያን ከምትገኝበት አሳፋሪና አሳዛኝ ዝቅጠት ለማውጣትና መልሶ ለማቋቋም የሁሉንም ልጆቿን የጋራ ርብርቦሽ የምትፈልግ ስለሆነ የአገሩን ዳር ድንበር በሕይወቱ የሚያስከብረው የጦር ኃይል አባልም ይሁን በየቀኑ ሕዝባዊ አገልግሎት ሰጭው የመሥሪያ ቤት ሠራተኛ፥ አስተማሪውም ሆነ ነጋዴው፥ ዝንታለም የሚንገላታው ገበሬም ሆነ እንዲቦዝን የተደረገው ወጣት፥ የጤና ባለሙያውም ሆነ ከብት አርቢው ዜጋ፥ ወዘተ... የሁሉም ዜጋና ብሔር/ብሔረሰብ እኩልነት ለሚረጋግረጡባት፥ አድልዖ ለሌለባት፥ የሕግ የበላይነትና ሰብአዊ መብቶች በውን ለተከበሩባት የጋራ አገር በጋራ እንድንቆም አደራችን የጠበቀ ነው። በመሆኑም ይኽንን ጉዳይ የትኩረት ትኩረት ሰጥተን ለዴሞክራሲና ለሕዝባችን ሉኣላዊነት ለመዋደቅ ስንነሳ ለዚህ ክቡር ዓላማና ለዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት በሚደረገው የጋራ ትግል ሌሎች ዴሞክራሲያዊና አገር-ወዳድ ኃይሎች እንዲደባለቁን፥ከሁሉምና ከማንም በላይ ደግሞ ዋናው ባለጉዳይ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኢሕአዴግም ሆነ ከማንናውም ከፋፋይ ኃይል ወጥመድ እራሱን ጠብቆ ከዳር እስከ ዳር ብሔር/ብሔረሰብ፥ ዕድሜ፥ ፆታ፥ ወዘተ.... ሳይል በአንድነት እንዲነሳ አገራዊና ወገናዊ ጥሪ በአክብሮት እናስተላልፋለን።

ድል በኅብረት!
ኅብረት ለአስተማማኝ የጋራ ድል!!
የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነቱና በኅብረቱ መብቶቹን ያስከብራል!!!